
# ንተቅዋ ተሰነቑ




ፀሓፊ፡- ዑስማን ኑሪ ቶፕባሽ
Osman Nuri Topbash

ትርጉም ኣማሓርኛ፡- ኣህመድ ሑሴን (አቡ ቢላል)
ኣቀናባሪ፡- ሓሰን ታጁ
ትርጉም ትግርኛ፡- ዓብዱልጀሊል(ኣቡ ዓብዱላህ)



መሐተማይ ኣልበያን ሊሚትድ

# ተቅዋን ተሰነቁ

## በኡስማን ኑሪ ቶፕባስ


ትርጉም ፦ አህመድ ሁሴን (አቡ ቢላል)

አርታዒ ፦ሐሰን ታጁ



*አሳታሚ፦ አልበያን ሊሚትድ*

*ስልክ ቁጥር ፦ 0913878788 ወይም 0911051025*

*<u>አዲስ አበባ ኢትዮጵያ</u>*

የአሳታሚው መብት በሕግ
የተጠበቀ ነው።

All rights are reserved

አንደኛ እትም ጥር 2003

AFKAD 3

*Addis Ababa Ethiopia*

First Edition Jan.2011

# ማውጫ

ርእስ ገጽ


መቅድም ........ 6

ምዕራፍ አንድ ........ 15

በፈተናዎች የተሞላች ሕይወት ........ 15

ተቅዋ ምንድን ነው? ........ 17

ምዕራፍ ሁለት ........ 23

ሕይወት ዓላማ አለውን? ከሆነስ ምን? ........ 23

ምዕራፍ ሦስት ........ 37

በሁሉም ጉዳዮችህ ውስጠ ተቅዋ (የአላህ ፍራቻ) ይኑርህ ........ 37

ወደ አላህ የመቃረቢያ መንገዶች ........ 38

ምዕራፍ አራት ........ 40

ወደ መድህን የሚያቃርቡን ምስጢራት ........ 40

ወደ ተሳሳተው ጉዳና አትዘናበል ........ 41

ሁልጊዜም ከእውነተኞች ጋር ሁኑ ........ 44

ፍም እሳትን እንደመጨበጥ ........ 47

በአምልኮት በተለይም በሶላት ውስጥ የተቅዋ አስፈላጊነት ........ 47

በፆም ወቅት የተቅዋ አስፈላጊነት ........ 49

ምጽዋት (ሰደቃ) ስንሰጥ የሚኖረን ተቅዋ ........ 51

ተቅዋ በሐጅ ፀሎት አፈጻጸም ላይ ........ 54

**ርእስ** **ገጽ**


ምዕራፍ አምስት ........................................ 55

በተቅዋ መንገድ ላይ የተደቀኑ ደንቃራዎች ........................ 55

1) ኩራት ........................................ 55

2) ስስታምነት ........................................ 56

3. ችላ ባይነትና ሞኝነት ........................................ 57

'ፍቅረ ንዋይ' በተቅዋ መንገድ ላይ የተቀመጠ ደንቃራ ............ 59

የገንዘብ ሌላ ገጽታ ........................................ 62

ምዕራፍ ስድስት ........................................ 66

ፀባያችንን በማሳመር በኩል ተቅዋ የሚጫወተው ሚና ............ 66

ተቅዋ በኢእሣር ላይ ሲንፀባረቅ ........................ 69

ተቅዋ በአል - ኢህሳን (በማሳመር) ሲገለጽ ........................ 72

ምዕራፍ ሰባት ........................................ 74

ባለን ነገር ከመርካት (ሪዷ) አንፃር ተቅዋ የሚኖረው ሚና ............ 74

1. ውስጣቸውም ውጪአቸውም መልካም የሆኑ ሰዎች ......... 74

2. ውስጣቸውም ሆነ ውጪያቸው የተበላሹ ሰዎች ............... 74

3. ላይ ላዩን ሲታዩ መልካም የሚመስሉ ሆኖም ግን ውስጣቸው
መጥፎ የሆኑ ክስተቶች ........................................ 74

4. ላይ ላዩን ሲታዩ መጥፎ የሚመስሉ ነገር ግን ውስጣቸው
መልካም የሆኑ ነገሮች፡- ........................................ 75

ተውበት አድርጎ ወደ አላህ ለመመለስ የተቅዋ አስፈላጊነት ........ 76

ርእስ ገጽ


በበጎ ነገር ለማዘዝና ከእኩይ ድርጊትም ለመከልከል የተቅዋ አስፈላጊነት ........ 78

ታማኝ ለመሆንም ተቅዋ ያስፈልጋል ........ 81

ተቅዋ በፍቅር ሲገለጽ ........ 83

ምዕራፍ ስምንት ........ 88

የተቅዋ ልዩ ልዩ ገጽታዎች ........ 88

ተቅዋ በኢኽላስ (ፍጹምነት) ላይ ያለው ድርሻ ........ 88

ተቅዋ አደራን በመጠበቅ ላይ ስለሚጫወተው ሚናስ ምን እንበል? 88

ተቅዋ በኃላፊነት ላይ ያለው ሚና ........ 89

ተቅዋ ያለውን ሰው አላህ መውጫ ያደርግለታል ........ 90

የሰው መመዘኛው ተቅዋ ነው ........ 90

የተቅዋ መገለጫው ምንድን ነው? ........ 91

የተቅዋን ፈተና ማለፍ ........ 91

ተቅዋን ልበሱት ........ 92

ከስንቅም ሁሉ በላጩ ተቅዋ ነው ........ 93

# መቅድም

ምስጋናና ውዳሴ ለኃያሉ አላህ የተገባው ነው። ይህን ፍጥረተ ዓለም አስገኝቷል። ሰውንም በመፍጠር ከፍተኛ ጥበቡን አሳይቷል። ይመራበትና ወደርሱ ይቃረብበት ዘንድም ኃይማኖት ቀምሮለታል። ኢኽላስን (ፍጹም ለእርሱ ብቻ ብሎ መስራትን) እና ተቅዋንም (ፍራቻን) አሳውቆታል።

የአላህ ሰላምና እዝነት የፍጥረታት ሁሉ ዓይነታ እንዲሁም አብሪና አንፀባራቂም በሆኑት መልእክተኛ ሙሐመድ ኢብኑ አብዱላህ (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ ይውረድ። እርሳቸው በእርግጥም የኢኽላስና የተቅዋ ታላቅ ምሳሌ ነበሩና።

የሰው ልጅ ሕይወት በአንዱ ወይም በሌላው መንገድ እንደዘበት ማለቁና የእድሜውም ፀሐይ ማሽቆልቆሏ አይቀርም። ዋናውና ጠቃሚው ጉዳይ ይህች ሕይወት እንዴት ነው ማለፍ ያለባት? አላህን በመፍራትና ለእርሱ ብቻ ብሎ (በኢኽላስ) በጐ ምግባራትን በማከናወን ነው ወይስ በድንቁርናና እንዲሁ ባፈተተው ከኖሩ በኋላ ማለፍ? የሚለው ነው።

ሰብዓዊዉ ፍጡር በዚህች ዓለም ላይ ተፈጥሮ መንቀሳቀስ ከጀመረና ዙሪያውን እያማተረ ማስተዋል ካመጣ በኋላ ምንድን ነው የታዘበው ነገር? እውነት ሕይወት ያለ ታላቅ ግብና ዓላማ የተፈጠረች ናት? ይህች ዓለምስ? ለመሆኑ ከእርሱ የሚፈለግበት ነገር ምንድን ነው? እዚህም እዚያም ሲባዝን ኖሮ ከሁለት ክንድ መሬት ውስጥ በመተኛት የእርሱ ጉዳይ ያበቃልን? የሕይወት ዓላማና ግብስ ይኸው ነውን?

አዎ፣ በዚህች ዓለም ላይ የሰው ዘር ሕይወቱ ትርጉም ያላትና ምልዓት የተላበሰች እንድትሆን ከሻ በመጀመሪያ ከፈጣሪው አላህ ጋር መተዋወቅ አለበት። ከዚያም እርሱን ብቻ ማምለክና ለእርሱ ብቻ ፍጹምነትን (ኢኽላስን) በማሳደር በጎ ምግባራትን መፈጸም እንዲሁም ተቅዋን

መላበስ አለበት፡፡  ለመሆኑ ተቅዋ ማለት ምንድን ነው? ተቅዋ ማለት በሰውና በፈጣሪው መካከል ግርዶሽን የሚጥሉ የሆኑ ሥጋዊና ደመነፍሳዊ ዝንባሌዎችን ወዲያ በማራገፍ በምትኩ ወደ ፈጣሪው አላህ የሚያቃርቡትን መልካም ሥራዎችና  አምልኮትን መፈፀምና በዚህም ላይ መዘውተር ነው፡፡

እንግዲህ ተቅዋ (አላህን መፍራት) ብለን የምንጠራው የአንድ ወቅት ክንውን ወይም በተወሰነ የአምልኮ ቦታ ላይ ብቻ ተተግብሮ በሌላ ጊዜ ወደጎን የሚደረግ ሳይሆን በእምነት፣ በአምልኮት፣ ከሌሎች ጋር ባለን ማኅበራዊ ተራክቦና በአጠቃላይ በሕይወት አውድ ውስጥ ሆነን በምናሳልፋት በእያንዳንዷ የጊዜ ሽርፍራፊ የሚገለጽና የሚተገበርም ነው። አንድ ሰው ተቅዋ አለው ስንል  የዓለማት ፈጣሪና አስተዳዳሪ ከሆነው ኃያሉ አላህ ጋር ዘውታሪ የሆነ መልካም ግንኙነት ያለውና የእርሱም ወዳጅ ነው ማለታችን እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

በሌላ አገላለጽ ኢኽላስ (ፍጹማዊነት) እና ተቅዋ (የአላህ ፍራቻ) ማለት ውስጣዊ ስብእናችንን ከተለያዩ መንፈሳዊ በሽታዎች በማጽዳት፣ በመለከታዊው ኃይል ፈቃድ ሥር መልካም ሥራዎችን በመስራትና አምልኮትን በመፈጸም ሐሴትን የራሷ የምታደርግ ቀልብ (ልብ) ባለቤት መሆን ማለት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት መንፈሳዊ ማማ ላይ የወጣች ቀልብ በሚቀጥለው የቁርአን አንቀጽ ከተገለጸው አባባል ጋር ስምምነት አላት፡-

﴿أَفَمَن شَرَحَ ٱللَّهُ صَدۡرَهُۥ لِلۡإِسۡلَٰمِ فَهُوَ عَلَىٰ نُورٖ مِّن رَّبِّهِۦۚ فَوَيۡلٞ لِّلۡقَٰسِيَةِ قُلُوبُهُم مِّن ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ أُوْلَٰٓئِكَ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٍ ٢٢﴾ الزمر: ٢٢

*“አላህ ደረቱን ለእስልምና ያሰፋለትና እርሱም ከጌታው ዘንድ በብርሃን ላይ የሆነ ሰው (ልቡ እንደደረቀ ሰው ነው?) ልቦቻቸው ከአላህ መወሳት*

*ለደረቁ ሰዎች ወዮላቸው። እነዚያ በግልጽ መሳሳት ውስጥ ናቸው።" (አዝ-ዙመር :22)*

እርግጥ ነው ይህን የመሰለ ቀልብ (ልብ) ባለቤት ለመሆን ከእርኩስ ምኞትና መንፈሳዊ ጨለማን ከሚያላብስ ሥጋዊ ጉምዠታ (carnal desire) የሰው ልጅ ይላቀቅ ዘንድ ግድ ነው። ኃያሉ አላህ ራሱ የዚህን መንፈሳዊ ጦርነት አስቸጋሪነት በማውሳት የኋላ ኋላ አሸናፊ ለሚሆን ሰው ግን በዚህችም ሆነ በመጪው ዓለም የድል አክሊል እንደሚደፋለትና ተሸናፊ (ተንበርካኪ) ሆኖ ለሚቀር ደግሞ ኪሳራ እንደሚያከናንበው እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

﴿وَٱلشَّمۡسِ وَضُحَىٰهَا ١ وَٱلۡقَمَرِ إِذَا تَلَىٰهَا ٢ وَٱلنَّهَارِ إِذَا جَلَّىٰهَا ٣ وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَغۡشَىٰهَا ٤ وَٱلسَّمَآءِ وَمَا بَنَىٰهَا ٥ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا طَحَىٰهَا ٦ وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ٧ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ٨ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ٩ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ١٠﴾ الشمس: ١ - ١٠

*"በፀሐይና በብርሃኗ እምላለሁ። በጨረቃውም በተከተላት ጊዜ በቀኑም (ፀሐይን) በገለጻት ጊዜ በሌሊቱም በሸፈናት ጊዜ በሰማይቱም በገነባት (ጌታ) በምድሪቱም በዘረጋትም በነፍስም ባስተካከላትም፣ አመጽዋንና ፍርሃቷንም ባሳወቃት (አምላክ እምላለሁ)። (ከኀጢአት) ያጠራት ሰው ፍላጐቱን በእርግጥ አገኘ። (በኃጢአት) የሸፈናትም ሰው በእውነት አፈረ።" (አሽ-ሽምስ:1-10)*

ጀላሉዲን ሩሚ የተባሉ መንፈሳዊና ባለቅኔ ሰው እንዲህ ይሉናል፡-

*"አንተ እውነትን ፍለጋ የምትቃትት ሆይ! ሃቁን ለማወቅ ከሻህ ፈርኦንም ሆነ ሙሳ አልሞቱም፤ በአካልህ ውስጥ ነፍስ ዘርተው እየተላወሱ ይገኛሉ። ራሳቸውን በአንተነትህ ሥጋና ደም ውስጥ አስርገው አድፍጠዋል። በልብህ ውስጥ የማያባራውን ፍትጊያና ጦርነት እያደረጉ*

*ይገኛሉ፡፡ የእነዚህን ሁለት ባላንጣዎች ፍትጊያ በቅጡ ማድመጥና ፈርኦንን ማዳከም ያንተ ፋንታ ነው፡፡”*

አቡ ዘር (ረ.ዐ.) የሚከተለውን ሐዲስ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አስተላልፈዋል፡-

“አንድ እለት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-‘ሰዎች በትክክል ተግባራዊ ካደረጉት መድህን የሚያገኙበትን አንቀጽ አውቃለሁ፡፡’ “ይህ አንቀጽ የትኛው ነው? የአላህ መልእክተኛ ሆይ!” ተብለው ሲጠየቁ የሚከተለውን የቁርዓን አንቀጽ አነበቡ፡-

*“…አላህንም የሚፈራ ሰው ለእርሱ መውጫን ያደርግለታል፡፡” (አጥ-ጦላቅ፡ 2)*

አንድ ጊዜ የሆነ ሰው ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መጣና እንዲህ አላቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ጉዞ ላደርግ ነውና ዱዓ ያድርጉልኝ፡፡”

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉት፡-

“አላህ ተቅዋን ይስጥህ!” ሰውየው ሌላ ዱዓ እንዲጨምሩለት በመፈለጉ እንዲህ በማለት አከሉለት፡-

“…አላህ ኃጢአትህን ይማርህ፡፡”

በዚህ ጊዜ ይህ ባልደረባቸው እንዲህ አለ፡- “እናትና አባቴ መስዋእት ይሁኑልዎ! የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እባክዎ አሁንም ይጨምሩልኝ፡፡” “የትም ሆነም መልካም ነገር ለመስራት ትችል ዘንድ አላህ ያግራልህ፡፡” (ቲርሚዚ)

የአላህ መልእክተኛ ለዚህ ባልደረባቸው በመጀመሪያ ያደረጉለት መሠረታዊ ዱዓ ተቅዋን የሚመለከት እንደነበር ልብ ይሏል፡፡ ከዚያም ለኃጢአቱ ምህረት ያገኝ ዘንድ ፀለዩለት፡፡ በመጨረሻም በየትም ሥፍራና ጊዜ መልካም ሥራ መስራትን ገር እንዲያደርግለት አላህን ለመኑለት፡፡

ይህ ማለት አንድ ሰው ተቅዋ (የአላህ ፍራቻ) ካለው ለኃጢአቶቹ ምህረት ማግኘትም ሆነ መልካም ሥራ ለመሥራት መገጠሙ ቀላል ይሆንለታል ማለት ነው።

ተቅዋን ለመላበስ ከፈለግን በሁሉም እንቅስቃሴያችን ጥንቃቄና ንቃት ሊኖረን ይገባል። ኃያሉ አላህ በተቀደሰው መጽሐፉ የነቢዩንና ያለፉትን ሌሎች ነቢያት መልእክት እንዲህ በማለት እየጠቀሰ ያስታውሰናል ፡-

﴿ وَيَٰقَوۡمِ مَن يَنصُرُنِي مِنَ ٱللَّهِ إِن طَرَدتُّهُمۡۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ٣٠ ﴾ هود: ٣٠

*"...ከአላህ ቅጣት የሚያድነኝ ማን ነው? አትገሰጹምን?" (ሁድ፡30)*

﴿ يَٰقَوۡمِ لَآ أَسۡـَٔلُكُمۡ عَلَيۡهِ أَجۡرًاۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا عَلَى ٱلَّذِي فَطَرَنِيٓۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ٥١ ﴾

*"...ምንዳዬ በዚያ በፈጠረኝ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም። አታውቁምን?" (ሁድ፡51)*

አንድ ሰው በማስተንተንና የዚህችን ዓለም አካሄድ በመመርመር ጊዜውን መዋጀት ሲጀምር የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአእምሮው ውስጥ በሰልፍ ሳይመጡበት ምንም ቢሆን አይቀሩም፡-

"ወደዚህ ዓለም ለምን መጣሁ? በሕይወት የመኖሬ ግብ ምንድን ነው? ይህ የምንንከላወስበት አጽናፈ ዓለም የማን ነው? የእለት ጉርሴንና የሚያስፈልጉኝን ነገሮች የሚለግሰኝ አካል ማን ነው? መጨረሻዬስ ምንድን ነው? ለመሆኑ የሞት ምስጢር ምንድን ነው" ወዘተ…

አንድ ሰው እነዚህን ጥያቄዎች ሕሊናውን አንቅቶ መጠየቅ ከጀመረና የአላህን ምሪት ከከጀለ አላህን ለማገልገል (ለመገዛት) የሰከንድ ሽርፍራፊም ብትሆን አያባክንም። ምንም እንኳን ሕይወት አጭር ናት ቢባልም የሰው ልጅ ግን ብዙ ትርፍና ባልባሌ ሁኔታ የሚያልፉ ጊዜዎች

ሞልተውታል፡፡ ክቡሩ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን ጉዳይ አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፡-

“ሁለት ዓይነት ፀጋዎችን ብዙ ሰዎች ትልቅ ግምት አይሰጧቸውም፡፡ እነርሱም ጤንነትና (መልካም ነገር ለመሥራት የሚበቃ) ነጻ ጊዜ ናቸው፡፡” (ቡኻሪ)

ብርክ የሚያስይዝ ስለሆነው የፍርዱ ቀን ካሰብን አንዲትም ሰከንድ መልካም ሥራ ሳንሰራ እንድታልፍብን አንሻም፡፡ ይህ ግን ታላቅ የሆነን የእምነት ደረጃ ይጠይቃል፡፡ ምክንያቱም የቁርአንን ተግሳፆችና የመልእክተኛውንም (ሰ.ዐ.ወ.) ማስጠንቀቂያዎች በንቃት ተቀብሎ ወደ ተግባር መቀየርን ይጠይቃልና፡፡ ይህን በማድረግ ብቻ ነው በዚህች ዓለም የተዘራውን የመኸር አዝመራ በመጪው ዓለም ማጨድና መሰብሰብ የሚቻለው፡፡ ቀጣዩ የቁርአን አንቀጽም የሚያስጠነቅቀን ይህንኑ እንድንፈጽም ነው፡፡

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَلۡتَنظُرۡ نَفۡسٞ مَّا قَدَّمَتۡ لِغَدٖۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرُۢ بِمَا تَعۡمَلُونَ ١٨ ﴾ الحشر: ١٨

*“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ ማንኛይቱም ነፍስ ለነገ ያስቀደመችውን ትመልከት፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው፡፡” (አል-ሐሽር፡18)*

ሌላው ተቅዋን ገንዘባችን የምናደርግበት መንገድ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ሁለንተናዊ ስብእና በማጥናትና ፈለጋቸውን (ሱናቸውን) በመከተል ወይም አጥብቀን በመያዝ ነው፡፡ ባልደረቦቻቸው ይህንን በሚገባ ተገንዝበው ስለነበርና እርሳቸው የተላኩት ለሰው ዘር በሙሉ እዝነት ተደርገው መሆኑን ያውቁ ስለነበር ከሁሉም ነገር -ሌላው ቀርቶ ከራሳቸው ነፍስ- በላይ ያፈቅሯቸው ነበር፡፡ በሁሉም የሕይወት ዘርፍ

የእርሳቸውን ምሳሌነት ተከትለዋል፡፡ ከዚህም በላይ የእርሳቸውና ከእርሳቸው የሆነን ነገር ከምንም ነገር አስበልጠው ያከብሩት ነበር፡፡

ቀጣዩ ሐዲስ ለዚህ አባባላችን ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል ነው፡-

አነስ ኢብኑ ማሊክ (ረ.ዐ.) እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ በተደጋጋሚ የኡሙ ሱለይምን (ረ.ዐ.) ቤት ይጐበኙ የነበረ ሲሆን እዚያም ለጥቂት ጊዜ ያሸልቡ ነበር፡፡ አንድ እለት እንደተለመደው እቤቷ ገብተው እንቅልፍ እንደወሰዳቸው እርሷ መጣች፡፡ "የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዓ.ወ.) በቤትሽ ውስጥ ተኝተዋል" ተባለችም፡፡ እቤት ስትገባም በቆዳ ምንጣፍ ላይ ተኝተው ሳሉ ላባቸው እየተንጠባጠበ በመኝታ ቦታዋ ላይ ሲያርፍ በማስተዋሏ ወዲያውኑ የሽቶ ማስቀመጫ እቃዋን ከፍታ ብልቃጦች አወጣች "ኡሙ ሱለይም ሆይ ምን እያደረግሽ ነው?" አሏት፡፡ እርሷም እንዲህ አለች፡- "የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኛ በዚህ ላይ ለልጆቻችን የሚሆን ተበርሩክ እንፈልግበታለን፡፡" በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

" ትክክለኛ የሆነ ነገር ፈጽመሻል፡፡"

ይህ የሚያሳየን ተከታዮቻቸው ለእርሳቸው የነበራቸው ጥልቅ ፍቅር የት ድረስ ርቆ እንደሚሄድ ነው፡፡ እኛ በዚህ ጨለማ ዘመን ያለነው ከዚህ ሁሉ ክስተት የምንቋደሰው መንፈሳዊ ትሩፋት አለ፡፡ ይኸውም ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ከልብ ማፍቀር፣ ፈለጋቸውን እግር በእግር እየተከታተሉ መፈፀም በዚህም ሆነ በመጪው ዓለም የስኬትን የምስጢር ቋጠሮ ውሉን የሚያስጨብጠን መሆኑን ነው፡፡ ቀናውን ጐዳና መገጠም የኛ ሐብት የሚሆነው እርሳቸውን ከሁሉም ነገር አብልጠን በመውደዳችንና ፈለጋቸውን ለመከተል በምናሳየው ትጋት መሆኑን ልብ ማለት ብልህ ያሰኛል፡፡ የዓለማቱ ጌታ አላህ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ፈለገ ሕይወት (ሱና) የመከተልን ወሳኝነት በቁርአኑ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ ﴾ الحشر: ٧

*"...መልእክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውምንም) ነገር ያዙት::" (አል-ሐሽር:7)*

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٣١ ﴾ آل عمران: ٣١

*"በላቸው:: አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ:: አላህ ይወዳችኋልና:: ኃጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምራልና::" (አሊ-ዒምራን: 31)*

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ٢١ ﴾ الأحزاب: ٢١

*"ለእናንት አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልእክተኛ መልካም መከተል አላችሁ::" (አል-አሕዛብ:21)*

﴿ مَّن يُطِعِ ٱلرَّسُولَ فَقَدۡ أَطَاعَ ٱللَّهَۖ ﴾ النساء: ٨٠

*"መልእክተኛውን የሚታዘዝ ሰው በእርግጥ አላህን ታዘዘ..." (አን-ኒሳእ: 80)*

ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ብዛት ያላቸው የቁርአን አንቀፆችን መዘርዘር የሚቻል ሲሆን ከሐዲስ ደግሞ የሚከተለውን ለናሙና እንጥቀስ::

አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) ባስተላለፉት መሠረት የአላህ መልእክተኛ (.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል:-

“ኡመቶቼ (ሕዝቦቼ) በሙሉ ጀነት ይገባሉ እምቢ ያለ ብቻ ሲቀር” ይህን ሲሉ ከተከታዮቻቸው “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ማን ነው እምቢ የሚለው?” የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው፡፡ እርሳቸውም “የታዘዘኝ ሰው ጀነት ይገባል፤ ትእዛዜን የጣሰ ደግሞ (ጀነት መግባትን) እምቢ ብሏል፡፡” አሉ፡፡ (ቡኻሪ)

ስለዚህ ሁላችንም ለራሳችን የሚከተለውን ጥያቄ ሁልጊዜም ማቅረብ አለብን፦ “የእኔ ሁኔታ፣ አኗኗሬና አጠቃላይ ሕይወቴ የእርሳቸውን ይመስላልን?”

# ምዕራፍ አንድ

# በፈተናዎች የተሞላች ሕይወት

በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ የሕያው ፍጡራን ብቸኛ መገኛ በሆነችው ምድራችን በየብስም ሆነ በባህር ከሚርመሰመሰው ህልቆመሳፍርት የሌለው ፍጡር ሁሉ ሰው ባማረና በተስተካከለ አቋም ላይ ነው የተፈጠረው፡፡ (አህሰነል ኻሊቂን እንዲል ቁርአን አት-ቲን ፡ 4)፡፡ ይህ ያማረና የተስተካከለ አቋም በውስጡ ብዙ ነገሮችን ያካተተ ሲሆን ማሰብ፣ መመራመር፣ መጠየቅ፣ምክንያታዊ መሆን፣ መገንዘብና ሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ፀጋዎችም ይጨምራል፡፡

አላህ ሰውን በዚህ ዓለም ከፈጠረው በኋላ ግን እንዲሁ ልቅ ሆኖ እንዲኖር፣ እየበላና እየጠጣ፣ እየተዋለደም ቆይቶ ሲያረጅ እንዲሞት፣ የእርሱም ነገር እስከወዲያኛው የተረሳ ሆኖ እንዲቀር አልነበረም፡፡ ይህም ብርሃን በተሞላው መለኮታዊ አዋጅ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡-

﴿ أَيَحۡسَبُ ٱلۡإِنسَٰنُ أَن يُتۡرَكَ سُدًى ﴿٣٦﴾ أَلَمۡ يَكُ نُطۡفَةٗ مِّن مَّنِيّٖ يُمۡنَىٰ ﴿٣٧﴾ ﴾ القيامة: ٣٦ - ٣٧

*“ሰው ስድ ሆኖ መተውን ይጠረጥራልን? የሚፈስ ከሆነ የፍትወት ጠብታ አልነበረምን?” (አል-ቂያማህ 36-37)*

﴿ قُتِلَ ٱلۡإِنسَٰنُ مَآ أَكۡفَرَهُۥ ﴿١٧﴾ مِنۡ أَيِّ شَيۡءٍ خَلَقَهُۥ ﴿١٨﴾ مِن نُّطۡفَةٍ خَلَقَهُۥ فَقَدَّرَهُۥ ﴿١٩﴾ ثُمَّ ٱلسَّبِيلَ يَسَّرَهُۥ
﴿٢٠﴾ ثُمَّ أَمَاتَهُۥ فَأَقۡبَرَهُۥ ﴿٢١﴾ ثُمَّ إِذَا شَآءَ أَنشَرَهُۥ ﴿٢٢﴾ ﴾ عبس: ١٧ - ٢٢

*“ሰው ተረገመ ምን ከሐዲ አደረገው? (ጌታው) ከምን ነገር ፈጠረው? (አያስብምን?) ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው መጠነውም፡፡ ከዚያም (ከእናቱ ሆድ መውጫ) መንገዱን አገራው፡፡ ከዚያም ገደለው እንዲቀበርም አደረገው፡፡ ከዚያም (ማንሳቱን) በሻ ጊዜ ያስነሳዋል፡፡” (ዐበሰ፡17፡22)*

ስለዚህ ሰው ወደዚህች ዓለም የተላከው ለታላቅ ፈተና ነው ማለት ነው፡፡ እናም ከአባታችን አደም (ዐ.ሰ.) ጀምሮ ይህችን ምድር የረገጠ ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ወደደም ጠላ ፈተና አለበት፡፡ ይህንን ፈተና በጽናት ተቋቁሞ በደህና ውጤት ካላለፈ ደግሞ ወዮለት፡፡ ብዙ አበሳ ከፊት ለፊቱ ይጠብቀዋልና!

የሰው ልጅ መንፈሳዊ ታሪኩን በዘጋቢ ብእር ማስፈር ከጀመረ አንስቶ ገጾቹን ወደ ኋላ መለስ ብሎ እየገለጠ ቢያስተውል ይህ ፈተና አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ይዘት ያለው ሆኖ ያገኘዋል፡፡ በምድር ላይ ከኖሩት ሰዎች ሁሉ እጅግ የተከበሩትና ከልኡሉ ጌታ ክብርና ሞገስ የተቸራቸው መልእክተኛና ነቢይ ሙሐመድ ኢብኑ አብዱላህ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን የፈተና ሁኔታ በአንድ ሐዲሳቸው ሳያወሱ አላለፉም፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት፡-

“አንድ አማኝ ወንድና አንድ አማኝ ሴት (በዚህች ዓለም ሕይወት ውስጥ) በገዛ ራሱ፣ በልጁና በሃብቱ ላይ ምንም ኃጢአት ሳይኖርበት ኃያሉ አላህን (በትንሳኤው) ቀን እስኪገናኝ ድረስ ለፈተና (ለተፈታታኝ ሁኔታዎች) እንደተጋለጠ ነው፡፡” ሐዲሱን አቡ ሁረይራ ያስተላለፉት ሲሆን ቲርሚዚ ዘግበውታል፡፡

እዚህ ላይ የሁሉንም አትኩሮት የሚሻው ጥያቄ የሰው ልጅ በየዘመናቱ የገጠሙትን ፈተናዎች አእምሮውን፣ የማሰብና የመገንዘብ ብቃቱን ተጠቅሞ እንዴት ሊቋቋማቸውና ወደ መልካም ነገርም ሊቀይራቸው ቻለ? የሚለው ነው፡፡

እንግዲህ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የሰው ልጅ እነዚህን ፈተናዎች ያለ እምነትና የአላህን እገዛ ሳያገኝ ሊወጣቸው እንደማይችል ማወቁ በራሱ የፈተናውን የመጀመሪያ ክፍል እንደማለፍ ይቆጠራል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ታላቅ ፈተና አንጻር አዛኙ ጌታችን አላህ (ሱ.ወ.) ያለምሪት፣ ያለመጽሐፍትና ያለነቢያት አልተወንም፡፡

እውነቱን ለመናገር አላህ (ሱ.ወ.) ነቢያትንም፣ መጽሐፍትንም ሆነ ራእይን ባይልክልን እንኳን ሰማያትንና ምድርን፣ በመካከላቸው ያለውንም ነገር በማስተዋል የእርሱን መኖርና አምልኮትም የሚገባው መሆኑን መገንዘብ አይገደንም:: አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَسْجُدُ لَهُۥ مَن فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَن فِى ٱلْأَرْضِ وَٱلشَّمْسُ وَٱلْقَمَرُ وَٱلنُّجُومُ وَٱلْجِبَالُ وَٱلشَّجَرُ وَٱلدَّوَآبُّ وَكَثِيرٌ مِّنَ ٱلنَّاسِ ﴾ الحج: ١٨

*"አላህ በሰማያት ያለው ሁሉ በምድርም ያለው ሁሉ ፀሐይና ጨረቃም ከዋክብትም፣ ተራራዎችም፣ ዛፎችም ተንቀሳቃሾችም ከሰዎች ብዙዎችም ለእርሱ የሚሰግዱለት መሆኑን አታውቁምን?..." (አል-ሐጅ፡ 18)*

﴿ وَمَا خَلَقْنَا ٱلسَّمَآءَ وَٱلْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا لَٰعِبِينَ ﴿١٦﴾ ﴾ الأنبياء: ١٦

*"ሰማይንም ምድርም በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ ቀላጆች ሆነን አልፈጠርንም::" (አል-አንቢያ፡16)*

## ተቅዋ ምንድን ነው?

የአላህ ወዳጅ የሆኑ ሰዎች ተቅዋን (ፈሪሃ አላህ ያለው መሆንን) በብዙ መንገድ ይተረጉሙታል:: ተቅዋ የሚለውን ቃል በግርድፉ እንተርጉመው ከተባለ - ራስን ከማንኛውም ዓይነት አላህን የማያስደስት ከሆነ ድርጊትና ንግግር ማቀብ፣ መጠበቅና ማራቅ ማለት ይሆናል። ስለሆነም ተቅዋ ካለን የአላህ ጥበቃ አለን ማለት ነው::

እንግዲህ ተቅዋ ብለን የምንጠራው ሁኔታ አንድ ሰው አላህ የከለከላቸውን ነገሮች በመራቅ፣ ያዘዘውንም አቅሙ በፈቀደለት መሠረት በመስራትና የእርሱን እገዛ በመሻት የሚያገኘው ጥበቃና ከለላ ነው፤ ማለትም ይቻላል:: ይህም በመሆኑ ተቅዋን በራስ ላይ ለማምጣት ስጋዊ

ፍላጐትንና የነፍስን ዝንባሌ በመግታት ለመንፈሳዊ ሕይወት ከፍ ያለ ዋጋና ትርጉም መስጠትን ይጠይቃል፡፡

ተቅዋን በሌላ አባባል እንግለፀው ካልን ደግሞ የኢስላምን የሥነምግባር ደንቦች በሙሉ ልብና ፍላጐት መተግበርን፣ አላህን መፍራትና በተገኘው ነገር (ሲሳይ) መብቃቃትን ያመለክታል፡፡

ዓሊ ኢብን አቡ ጧሊብ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት ተቅዋን ገልፀውታል፡-

"አላህን መፍራት በተገኘው መብቃቃትና ለፍርዱ ቀን መዘጋጀት" ነው፡፡

አላህን በመፍራት ለሰው ዘር አብነት የሆኑት ሙሐመድ ኢብኑ አብደሏህ (ሰ.ዐ.ወ.) ስለተቅዋና መቀመጫው የት ላይ እንደሆነ በተከታዩና ከአቡ ሁረይራ ተወርቶ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ተናግረዋል፡፡

"አትመቅኙ፣ ዋጋ አታሳቅሉ፣ በመካከላችሁ ጠብ አይገኝ፡፡ አንዱ በሌላው ወንድሙ ላይ ጀርባውን አያዙር (አትኮራረፉ)፡፡ ከፊሉ በከፊሉ ገበያ ጣልቃ አይግባ፡፡ እናንተ የአላህ ባሪያዎች ስትሆኑ ወንድማማቾች ሁኑ፡፡ ሙስሊም ለሙስሊም ወንድሙ ነው፤ ስለሆነም በደል አያደድርስበት፡፡ አይዋሸው፣ አይናቀውም፡፡ ከዚያም ወደ ልባቸው እያመለከቱ አላህን መፍራት ከዚህ ነው አሉ፡፡ ለአንድ ሙስሊም፣ ወንድሙን አሳንሶ ማየቱ (መናቁ) ብቻ ለወንጀል ይበቃዋል፡፡ ሙስሊም የሌላውን ሙስሊም ደም፣ ገንዘብና ክብር (መንካቱ) ክልክል ነው፡፡"

ኃያሉ አላህ በቁርአኑ የሚነግረንም ተቅዋ ያላቸው ወይም እርሱን እንደሚገባው የሚፈሩት ደሞዛቸው ምን እንደሆነ ነው፡-

﴿ وَسَارِعُوٓاْ إِلَىٰ مَغۡفِرَةٖ مِّن رَّبِّكُمۡ وَجَنَّةٍ عَرۡضُهَا ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلۡأَرۡضُ أُعِدَّتۡ لِلۡمُتَّقِينَ ١٣٣ ﴾ آل عمران: ١٣٣

*“ከጌታችሁም ወደሆነች ምህረትና ስፋቷ እንደሰማያትና ምድር ወደ ሆነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ሲሆን ተቻኮሉ።” (አሊ-ዒምራን፡ 133)*

ለመሆኑ ወደ ተቅዋ የሚያቃርቡን ነገሮች ምንድን ናቸው? አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ جَٰهَدُواْ فِينَا لَنَهۡدِيَنَّهُمۡ سُبُلَنَاۚ وَإِنَّ ٱللَّهَ لَمَعَ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ٦٩ ﴾ العنكبوت: ٦٩

*“እነዚያም በእኛ መንገድ የታገሉ መንገዳችንን በእርግጥ እንመራቸዋለን። አላህም በእርግጥ ከበጐ ሰሪዎች ጋር ነው።” (አል-ዐንከቡት፡69)*

﴿ وَٱعۡبُدۡ رَبَّكَ حَتَّىٰ يَأۡتِيَكَ ٱلۡيَقِينُ ٩٩ ﴾ الحجر: ٩٩

*“እውነቱም (ሞት) እስኪመጣህ ድረስ ጌታህን ተገዛ።” (አል-ሒጅር፡99)*

﴿ وَٱذۡكُرِ ٱسۡمَ رَبِّكَ وَتَبَتَّلۡ إِلَيۡهِ تَبۡتِيلٗا ٨ ﴾ المزمل: ٨

*“የጌታህንም ስም አውሳ። ወደርሱም (መገዛት) መቋረጥን ተቋረጥ። (ለጌታህ ፍጹም አገልጋይ ሁን) (አል-ሙዘሚል፡8)*

እነዚህ ሁሉ የቁርአን አንቀፆች የገዛ ራስን መታገል (ሙጃሃዳ) ወደ ተቅዋ የሚያዳርሰን ድልድይ መሆኑን ነው አበክረው የሚያሳስቡን። ነፍስን ወደ ጥመት ጉዳና ከመዘናበል አባዜዋ አላቆ ወደ አላህ ለመቃረብ ብቸኛው መንገድ ከራስ ጋር ጦርነት መግጠም (ሙጃሃዳ) እንጂ ሌላ አይደለም።

የዓለማት ሁሉ ጌታ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَيَخۡشَ ٱللَّهَ وَيَتَّقۡهِ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡفَآئِزُونَ ٥٢ ﴾ النور: ٥٢

*“አላህንና መልእክተኛውን የሚታዘዝ ሰው አላህንም የሚፈራና የሚጠነቀቀው ሰው እነዚያ እነርሱ ፍላጐታቸውን የሚያገኙ ናቸው፡፡” (አን-ኑር፡ 52)*

﴿ وَمَن جَٰهَدَ فَإِنَّمَا يُجَٰهِدُ لِنَفۡسِهِۦٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَغَنِيٌّ عَنِ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٦ ﴾ العنكبوت: ٦

*“የታገለ ሰውም የሚታገለው ለነፍሱ ነው፡፡ አላህ ከዓለማት በእርግጥ ተብቃቂ ነውና፡፡” (አል-አንከቡት፡6)*

የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) ከነፍስ ጋር እየታገሉ ወደ አላህ የመቃረቢያ መንገዶችን በተለያዩ ሐዲሶቻቸው ገልጸውልናል፡፡ ለአብነት ያክልም የሚከተሉትን እንመልከት፡-

ከአቡ ሁረይራ በተላለፈው መሠረት የአላህ መእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደሚከተለው በማለት አላህ በሐዲስ አልቁድስ የገለፀላቸውን ተናግረዋል፡-

“አላህ እንዲህ ብሏል፡- ለወዳጄ ጠላት በሆነ ሰው ላይ ጦርነት አውጄያለሁ፡፡ አንድ አገልጋዬ ወደ እኔ ለመቅረብ ግዴታ ያደረግኩበትን (የአምልኮት ተግባራት) ከመፈፀሙ ይበልጥ እኔ ዘንድ የተወደደ ነገር የለም፡፡ (ከግዴታው በኋላም) ተጨማሪ (ነዋፊል) ኢባዳዎችን እያዘወተረ ሲመጣ ወደ እኔ (ውዴታ) ይቀርባል፡፡ ለውዴታዬ ሲበቃም የሚሰማበት ጆሮ፣ የሚያይበት ዓይን፣ የሚዳስስበት እጅ፣ የሚራመድበት እግር እሆነዋለሁ፡፡ ቢጠይቀኝ እሰጠዋለሁ፤ ጠብቀኝ ካለኝም እጠብቀዋለሁ፡፡” (ቡኻሪ)

ከአነስ (ረ.ዐ.) በተዘገበው ሌላ ሐዲስ አል ቁድቅም አላህ እንዲህ ብሏል፡-

"አንድ አገልጋዬ (ባሪያዬ) አንድ ስንዝር ወደእኔ ሲቀርብ እኔ አንድ ክንድ ወደርሱ እቀርባለሁ፡፡ አንድ ክንድ ሲቀርበኝም አንድ እርምጃ እቀርበዋለሁ፡፡ እየተራመደ ሲመጣም እየሮጥኩ ወደርሱ እመጣለሁ፡፡"

አላህ በቁርአን እንዲህ ሲል ይናገራል፡-

﴿ وَلَقَدْ خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ وَنَعْلَمُ مَا تُوَسْوِسُ بِهِۦ نَفْسُهُۥ ۖ وَنَحْنُ أَقْرَبُ إِلَيْهِ مِنْ حَبْلِ ٱلْوَرِيدِ ﴿١٦﴾ ﴾

*"ሰውንም ነፍሱ (በሐሳቡ) የምትጫወተውን የምናውቅ ስንሆን በእርግጥ ፈጠርነው፡፡ እኛም ከደም ጋኑ ጅማት ይበልጥ ወደርሱ ቅርብ ነን፡፡" (ቃፍ፡16)*

﴿ وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ ۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴿٤﴾ ﴾ الحديد: ٤

*"እርሱም የትም ብትሆኑ ከእናንተ ጋር ነው፤ አላህም የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነው፡፡" (አል-ሐዲድ፡4)*

የተቅዋን ካባ የደረበችና በእርሱም የተጌጠች ነፍስ በአላህ መንገድ ላይ መጽናቷና ከሰይጣናዊ ድርጊትና ጉትጎታ የመራቅ ዋስትናዋ የተጠበቀ ነው፡፡

﴿ وَتَزَوَّدُوا۟ فَإِنَّ خَيْرَ ٱلزَّادِ ٱلتَّقْوَىٰ ۚ وَٱتَّقُونِ يَٰٓأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٧﴾ ﴾ البقرة: ١٩٧

*"...ተሰነቁም ከስንቅም ሁሉ በላጩ ጥንቃቄ (ተቅዋ) ነው፡፡ የአእምሮ ባለቤቶች ሆይ! ፍሩኝ፡፡" (አል-በቀራህ፡197)*

ቁርአን የያዛቸው አስተምህሮቶች፣ ተግሳፆች፣ የቀደምት ነቢያት ታሪኮች (ቀሰሱል አንቢያ) እየተደጋገሙ የቀረቡልን፣ እንዲሁ አይደለም፡፡

የቀደምት ሕዝቦችን ታሪኮች እያነበብን ከንፈራችንን እንድንመጥና እንድናዝንላቸው አይደለም። እኛም ከእነርሱ የተቅዋ ትሩፋት ተቋዳሾች ሆነን ፈለጋቸውን እንድንከተል እንጂ። አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ ءَايَٰتُهُۥ زَادَتْهُمْ إِيمَٰنًا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ ﴿٢﴾ ﴾ الأنفال: ٢

*"ፍጹም ምእመናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩና፤ በእነርሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው።" (አል-አንፋል፡ 2)*

ተቅዋ የሁሉም ነገር ምንጭና መነሻ ነው።

ኢብን አጣኡሏህ አል እስክንድሪ የተባሉ የአላህ ወዳጅ እንዲህ ብለዋል፦

"አላህ ሆይ! አንተን ያገኘ ሰው ምንድን ነው ያጣው? አንተን ያጣስ ሰው ምንድን ነው ያገኘው?""

አብዛኛው የሰው ልጅ ተቅዋ እንዳይኖረውና አላህን እንዳይገዛ ያደረገው መንፈሳዊ ጠኔ፣ ዓለማዊነት፣ ቁርአንን ብሎም ኢስላምን በቅጡ አለመረዳትና ሕይወት ዓላማ ያለው መሆኑን አለመገንዘቡ ነው። ቀጣዩ ምዕራፍ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ መጠነኛ ዳሰሳ ያደርጋል።

# ምዕራፍ ሁለት

# ሕይወት ዓላማ አለውን? ከሆነስ ምን?

ከ3500 ዓመታት በፊት እንደኖረ የተነገረለት የአላህ ወዳጅ (ነቢይ) እንደሚከተለው እንዳለ ተወስቷል፡፡

"እድሜ 70 ወይም ቢበዛ 80 ዓመታት ሲሆኑ እነርሱም በሃዘንና በመከራ የተሞሉ ናቸው።"

እያንዳንዱ ሰው ማለት ይቻላል በሆነ ወቅት ላይ የሕይወት ዓላማ ምንድን ነው? ብሎ ራሱን መጠየቁ አይቀርም፡፡ ኑሮን ለማሻሻል ተግቶ መስራት፣ ቤተሰባችን የሚያስፈልገውን ነገር ማሟላት፣ ምናልባት እንደተባለው 70 ወይም 80 ዓመታትን ከኖሩ በኋላ መሞትና በዚያው ለዘለዓለም ከህልውና ውጪ ሆኖ መቅረት ነውን? ሁሉም ነገር በሞት ይደመደማል ብለህ ታምናለህ?

﴿ وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ﴿٥٦﴾ ﴾ الذاريات: ٥٦

"ሰውንና ጋኔንንም ሊግገዙኝ (ሊያመልኩኝ) እንጂ አልፈጠርኳቸውም፡፡" (አዝ-ዛሪያት፡56)

﴿ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلْمَوْتَ وَٱلْحَيَوٰةَ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُمْ أَحْسَنُ عَمَلًا ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْغَفُورُ ﴿٢﴾ ﴾ الملك: ٢

*"ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መሆኑን ሊሞክራችሁ ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው..." (አል-ሙልክ፡2)*

የሕይወትን ዓላማ አስመልክቶ ኢስላም በእነዚህ ሁለት የቁርአን አንቀፆች አማካኝነት ከበቂ በላይ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ግን የመኖራቸውን

ግብ በውል ያልተገነዘቡ ሕዝቦች ምንድን ነው የሚሰማቸው? አላህንስ እንደምን ሊፈሩት (ተቅዋ ሊኖራቸው) ይችላል?

እውነቱን ለመናገር በምስራቁም ሆነ በምእራቡ ዓለም የሚኖሩ ብዙ ሰዎች የሕይወት ዋነኛው ዓላማ ቁሳዊ ሃብትን ማካበት እንደሆነ ይሰማቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ አስደሳችና ትርጉም ያለው ሕይወት ሊያስገኝ ይችላል የሚል እምነት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ቁሳዊ ሃብትን ያጋበሱ ሰዎች ያሉበት ሁኔታ ምንድን ነው የሚመስለው? አንድ በካናዳ የሚኖሩ ታዛቢ ይህን ጉዳይ አስምልክተው ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡- “ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የናጠጡ ሃብታሞች ደስተኞች እንዳልሆኑ በተደጋጋሚ ይናገራሉ፡፡ በሰሜን አሜሪካ መጥፎና አፍራሽ የሆነ አመለካከት ተስፋፍቷል፡፡…ለመሆኑ በዚህ ዓለም ላይ ደስተኛ የሆነ ሰው ይገኛልን? ካልለ ደስታ የሚገኝበትን ቁልፍ ሊነግረን ይችላልን?”

የቀድሞው የዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ ፕሬዝዳንትና የኖቤል ተሸላሚ ጂሚ ካርተር እንዲህ በማለት ተናግረዋል፡- “ቁሳዊ ነገሮችን ማግኘት ወይም በእነርሱ መጠቀም ትርጉም ያለው ሕይወት ለማግኘት ያለንን ከፍተኛ ፍላጐት እንደማያረካ ተገንዝበናል፡፡ ቁሳዊ ነገሮችን ማካበት ብቻውን ምንም ዓይነት ዓላማ የሌለውን ባዶ ሕይወት ትርጉም ያለው እንዲሆን ሊያደርገው አይችልም፡፡”

አንድ ሌላ የፓለቲካ መሪ ደግሞ እንዲህ ብለዋል፡- “ራሴንም ሆነ ሕይወቴን በተመለከተ እውነታው ምን እንደሆነ ለማወቅ ለበርካታ ዓመታት ጥልቅ ምርምር ሳደርግ ቆይቻለሁ፡፡ የማውቃቸው ብዙ ሰዎችም እንደዚሁ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ከምንጊዜውም የበለጠ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች እኛ ማን ነን? የሕይወታችን ዓላማስ ምንድን ነው? እያሉ በመጠየቅ ላይ ናቸው፡፡”

﴿ وَمَن يَعْشُ عَن ذِكْرِ ٱلرَّحْمَٰنِ نُقَيِّضْ لَهُۥ شَيْطَٰنًا فَهُوَ لَهُۥ قَرِينٌ ﴿٣٦﴾ ﴾ الزخرف: ٣٦

*"ከአር-ራህማን ግሳጼ (ከቁርአን) የሚደናበርም ሰው ለእርሱ ሰይጣንን እናስጠጋለን። ስለዚህ እርሱ ለእርሱ ቁራኛ ነው።" (አዝ-ዙኽሩፍ፡36)*

ብዙዎቹ የኑሮ ሁኔታዎች እየከፉ መሄዳቸውን ሲመለከቱ ሕይወት ዓላማ ያለው ስለመሆኑ ይጠራጠራሉ። በዓለም ዙሪያ ከአንድ ቢሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች ሥር የሰደደ ሕመም አለባቸው። አለያም የተመጣጠነ ምግብ አያገኙም፤ በተጨማሪም በዚህ ባለፈው በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጦርነት የሞቱት ሰዎች ቁጥር አራት እጥፍ ይሆናል። በየትኛውም ቦታ ወንጀል በተለይም ደግሞ በኃይል እርምጃ የሚፈፀም ወንጀል እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል። የቤተሰብ መፈራረስ፣ አደንዛዥ እፆችን መጠቀም፣ ኤድስ፣ በፆታ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች፣ ስርቆት፣ ግብረሰዶማዊነትና ሌሎችም ጉጂ ነገሮች ሕይወትን ይበልጥ አስቸጋሪ እያደረጉት ነው።

"የዓለም መሪዎችም ሰብዓዊውን ቤተሰብ በማጥቃት ላይ ላሉት ብዙ ችግሮች መፍትሄ ማምጣት አልቻሉም። ስለዚህ ሰዎች የሕይወት ዓላማ ምንድን ነው? ብለው መጠየቃቸው አያስገርምም።" በማለት አንድ ምሁር ይገልጻሉ።

ለመሆኑ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ምሁራንና የኃይማኖት መሪዎች የሚሰጡት መልስ ምንድን ነው? እነዚህ ሁሉ መቶ ዘመናት ካለፉ በኋላ አጥጋቢ መልስ ማግኘት ችለዋን?

የኮንፊሺየስ ኃይማኖት ምሁር የሆኑት ዱ-ዋ-ሚንግ "የመጨረሻው ከፍተኛ የሕይወት ትርጉም በተለመደው ሰብአዊ ሕልውናችን ውስጥ ይገኛል።" ብለዋል። በዚህ አመለካከት መሠረት ሰዎች መወለዳቸውን፣ በሕይወት ለመኖር ትግል ማድረጋቸውንና መሞታቸውን ይቀጥላሉ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት የተስፋ ጭላንጭል እንኳን አይታይበትም። ደግሞስ ይህ አመለካከት እውነት ነውን?

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ብዙ ሰዎች ካለቁባቸው የናዚ ማጎሪያ ካምፖች ውስጥ በሕይወት የተረፉ ኤሊ ቪዝል የተባሉ አይሁዳዊ እንዲህ ብለዋል፡- “በሕይወት የምንኖረው ለምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ የሰው ልጅ መልስ ሊሰጠው የሚገባ እጅግ አንገብጋቢ የሆነ ጥያቄ ነው፡፡…ትርጉም እንዳለው አምናለሁ።”

የአንድ መጽሔት አዘጋጅ የሆኑ ቨርማንት ሮይስተር የተባሉ ሰው ደግሞ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡- “ስለራሱ ስለ ሰው …በአጽናፈ ዓለም ውስጥ ስላለው ቦታ ስናስብ ያለን እውቀት ቀድሞ ከነበረው እምብዛም እድገት አላሳየም፡፡ አሁንም ቢሆን እኛ ማን ነን? በሕይወት የምንገኘውስ ለምንድን ነው? ምን ይጠብቀናል? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ አላገኘንም፡፡

﴿ وَمَن كَانَ فِي هَٰذِهِۦٓ أَعۡمَىٰ فَهُوَ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ أَعۡمَىٰ وَأَضَلُّ سَبِيلٗا ٧٢ ﴾ الإسراء: ٧٢

*“በዚህች ዓለም (ልበ) እውር የሆነ ሰው እርሱ በመጨረሻይቱም (ዓለም) ይበልጥ እውር ነው፡፡ መንገድንም በጣም የተሳሳተ ነው፡፡” (አል-ኢስራእ፡ 72)*

﴿ وَلَقَدۡ صَرَّفۡنَا فِي هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانِ لِيَذَّكَّرُواْ وَمَا يَزِيدُهُمۡ إِلَّا نُفُورٗا ٤١ ﴾ الإسراء: ٤١

*“ይገሰጹም ዘንድ በዚህ ቁርአን ውስጥ ደጋግመን በእርግጥ ገለጽን፡፡ መበርገግንም እንጂ ሌላን አይጨምርላቸውም፡፡” (አል-ኢስራእ፡ 41)*

የዝግመተ ለውጥ ሳይንስ ሊቅ የሆኑት ስቴፈን ጄይ ጉልድ ደግሞ “የላቀ መልስ ለማግኘት እንጓጓ ይሆናል፤ ሆኖም ግን አናገኝም፡፡ ብዙ የኃይማኖት መሪዎች የሕይወት ዓላማ አንድ ሰው ሲሞት ነፍሱ ወደ ሰማይ ሄዳ በዚያ ለዘላለም መኖር እንድትችል ጥሩ የአኗኗር መንገድ መከተል ነው ይላሉ፡፡ መጥፎ ለሆኑ ሰዎች የቀረበው አማራጭ እሳታማ ሲኦል ውስጥ ገብቶ ለዘላለም መሰቃየት ነው፡፡ ሆኖም በዚህ እምነት

መሠረት በምድር ላይ በታሪክ ዘመናት ሁሉ የታየው አጥጋቢ ያልሆነ ኑሮ እንዳለ ይቀጥላል ማለት ነው። ታዲያ የአምላክ ዓላማ ሰዎች ልክ እንደ መላእክት በሰማይ እንዲኖሩ ከነበረ ለመላእክት እንዳደረገው ሰዎችንም መጀመሪያውኑ ለምን በሰማይ ላይ እንዲኖሩ አድርጎ አልፈጠራቸውም?" ብለዋል።

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يُجَٰدِلُ فِى ٱللَّهِ بِغَيۡرِ عِلۡمٍ وَيَتَّبِعُ كُلَّ شَيۡطَٰنٍ مَّرِيدٍ ۝٣ كُتِبَ عَلَيۡهِ أَنَّهُۥ مَن تَوَلَّاهُ فَأَنَّهُۥ يُضِلُّهُۥ وَيَهۡدِيهِ إِلَىٰ عَذَابِ ٱلسَّعِيرِ ۝٤ ﴾ الحج: ٣ - ٤

*"ከሰዎች ያለ እውቀት በአላህ ነገር የሚከራከር ሞገደኛ ሰይጣንንም ሁሉ የሚከተል ሰው አለ። እነሆ! የተከተለውን ሰው እርሱ ያጠመዋል፤ ወደ ነዳጅ እሳት ስቃይም ይመራዋል ማለት በእርሱ ላይ ተጽፏል።" (አል-ሐጅ: 3-4)*

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يُجَٰدِلُ فِى ٱللَّهِ بِغَيۡرِ عِلۡمٍ وَلَا هُدًى وَلَا كِتَٰبٍ مُّنِيرٍ ۝٨ ثَانِىَ عِطۡفِهِۦ لِيُضِلَّ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ لَهُۥ فِى ٱلدُّنۡيَا خِزۡىٌ وَنُذِيقُهُۥ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ عَذَابَ ٱلۡحَرِيقِ ۝٩ ذَٰلِكَ بِمَا قَدَّمَتۡ يَدَاكَ وَأَنَّ ٱللَّهَ لَيۡسَ بِظَلَّٰمٍ لِّلۡعَبِيدِ ۝١٠ ﴾ الحج: ٨ - ١٠

*"ከሰዎችም ውስጥ ያለ እውቀት፣ ያለ ማስረጃም፣ ያለ አብራሪ መጽሐፍም በአላህ ነገር የሚከራከር ሰው አለ። ጐኑን ያጠፈ ሆኖ ከአላህ መንገድ ሊያሳስት (ይከራከራል)። በቅርቢቱ ዓለም ለእርሱ ውርደት አለው። በትንሳኤ ቀንም አቃጣይን ቅጣት እናቀምሰዋለን። ይህ እጆችህ ባስቀደሙት ኃጢአት አላህም ለባሮቹ ፈጽሞ በዳይ ባለመሆኑ ነው። (ይባላል)።" (-ሐጅ :8-10)*

ቀሳውስትም እንኳን ሳይቀሩ እንዲህ ዓይነቶቹ አመለካከቶች ግራ ያጋቧቸዋል። በለንደን የሚገኘው የቅዱስ ጳውሎስ ካቴድራል የቀድሞ ዲን የነበሩት ዶክተር ደብልዩ አር ኢንጅ በአንድ ወቅት እንዲህ ብለው

ነበር፡- “በሕይወት ዘመኔ ሁሉ የሕይወትን ዓላማ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት አድርጌያለሁ። ምንጊዜም መሰረታዊ ነገሮች ናቸው ብዬ አምንባቸው የነበሩ ሦስት ጥያቄዎችን ለመፍታት ሞክሬያለሁ። እነርሱም ዘላለማዊነት፣ የሰውን ሁለንተናዊ ባሕሪና ክፋሳን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ናቸው። ሆኖም ጥረቴ አልተሳካም። ለአንዳቸውም መልስ አላገኘሁም።”

﴿لِّكُلِّ أُمَّةٍ جَعَلْنَا مَنسَكًا هُمْ نَاسِكُوهُ ۖ فَلَا يُنَٰزِعُنَّكَ فِى ٱلْأَمْرِ ۚ وَٱدْعُ إِلَىٰ رَبِّكَ ۖ إِنَّكَ
لَعَلَىٰ هُدًى مُّسْتَقِيمٍ ﴿٦٧﴾ وَإِن جَٰدَلُوكَ فَقُلِ ٱللَّهُ أَعْلَمُ بِمَا تَعْمَلُونَ ﴿٦٨﴾ ٱللَّهُ يَحْكُمُ
بَيْنَكُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ فِيمَا كُنتُمْ فِيهِ تَخْتَلِفُونَ ﴿٦٩﴾﴾ الحج: ٦٧ - ٦٩

*“ለየሕዝቡ ሁሉ እነርሱ የሚሰሩበት የሆነን ሥርአተ ኃይማኖት አድርገናል። ስለዚህ በነገሩ አይከራከሩህ። ወደ ጌታህ መንገድም ጥራ። አንተ በእርግጥ በቅኑ መንገድ ላይ ነህና። ቢከራከሩህም አላህ የምትሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነው በላቸው። አላህ በትንሳኤ ቀን በዚያ በርሱ ትለያዩበት በነበራችሁት ሁሉ በመካከላችሁ ይፈርዳል።” (አል-ሐጅ :67-69)*

የሕይወት አላማን በተመለከተ በተነሳው ጥያቄ ላይ ምሁራንና የኃይማኖት መሪዎች የሚሰጧቸው ብዙ የተለያዩ ሐሳቦች ምን ውጤት አስከትለዋል? ብዙዎች የሚሰጡት ምላሽ አንድ በእድሜ የገፉ ሰው እንዲህ በማለት ከሰጡት አስተያየት ጋር የሚመሳሰል ነው። “በአብዛኛው የሕይወት ዘመኔ የሕይወቴ ዓላማ ምንድን ነው? እያልኩ ስጠይቅ ኖሬያለሁ። አሁን ግን ሕይወት ዓላማ ኖረውም አልኖረው ግድ የለኝም።

በዓለም ኃይማኖቶች ውስጥ ብዙ ዓይነት አመለካከቶች እንዳሉ የተረዱ በርካታ ሰዎች አንድ ሰው ምንም ዓይነት እምነት ቢኖረው የሚያመጣው ለውጥ የለም የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል። ኃይማኖት አንድ ሰው

የሕይወትን ውጣ ውረድ መቋቋም እንዲችል የሚረዳውን መጠነኛ የአእምሮ ሰላምና መጽናኛ የሚሰጥና ሕሊናን የሚያሳፍር ነገር ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ ኃይማኖት ከአጉል እምነት ተነጥሎ የማይታይ ነገር ነው ብለው ያስባሉ፡፡ ለብዙ መቶ ዘመናት ሲሰጡ የኖሩ ግምታዊ የሆኑ ኃይማኖታዊ ሃሳቦች የሕይወትን ዓላማ በተመለከተ ለተነሣው ጥያቄ መልስ ካለመስጠታቸውም በላይ የተራውን ሕዝብ ሕይወት እንዳላሻሻሉ ይሰማቸዋል፡፡ እንዲያውም የዚህ ዓለም ኃይማኖቶች በአብዛኛው የሰውን ልጅ እድገት ወደ ኋላ እንደጐተቱና ለከረረ ጥላቻና ጦርነት መንስኤ እንደሆኑ ታሪክ ያሳያል ባይ ናቸው፡፡

﴿ وَإِن تُطِعْ أَكْثَرَ مَن فِي ٱلْأَرْضِ يُضِلُّوكَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ ۚ إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا ٱلظَّنَّ وَإِنْ هُمْ إِلَّا يَخْرُصُونَ ١١٦ ﴾ الأنعام: ١١٦

*“በምድርም ካሉት ሰዎች አብዛኞቹን ብትከተል ከአላህ መንገድ ያሳስቱሃል፡፡ ጥርጣሬን እንጂ ሌላን አይከተሉም፡፡ እነርሱም የሚዋሹ እንጂ ሌላ አይደሉም፡፡” (ሱራ አል-አንዓም፡116)*

ይህም ሆኖ ግን ስለ ሕይወት ዓላማ እውነታውን ማወቁ አስፈላጊ ነው የሚሉ ብዙ ናቸው፡፡ የስነ አእምሮ ጠበብት የሆኑት ቪክቶር ፍራንክል የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል፡- “አንድን ሰው የሕይወትን ትርጉም ለማግኘት የሚያደርገውን ጥረት ያህል ለሥራ የሚያንቀሳቅሰው ኃይል የለም፡፡...አንድ ሰው ሕይወት ትርጉም እንዳለው ማወቁ ሌላው ቀርቶ እጅግ አስከፊ የሆኑ ሁኔታዎችን እንኳ ሳይቀር በሚገባ መቋቋም እንዲችል በዓለም ላይ ካለው ማንኛውም ነገር በላይ ሊረዳው እንደሚችል ለመናገር እደፍራለሁ፡፡”

እንግዲያውስ የሕይወት ዓላማ ምን እንደሆነ ማን ሊነግረን ይችላል? የማሽን ንድፍ አውጪ ወደሆነ ሰው ብትሄድና ምን እንደሆነ ሊገባህ ያልቻለ የአንድ በጣም ውስብስብ የሆነ ማሽን ንድፍ ሲያወጣ

ብትመለከት መሣሪያው ለምን ዓላማ የሚያገለግል መሆኑን ልታውቅ የምትችለው እንዴት ነው? ከሁሉ የተሻለው መንገድ ንድፍ አውጭውን መጠየቅ ነው።

ጉዳዩ በዚህ መንገድ ከተያዘ ከትንሽዋ ሕዋስ አንስቶ ባሉት ሕያዋን ነገሮች ላይ በጠቅላላው የሚታየውን ንድፍ ጨምሮ በምድር ላይ በዙሪያችን ስለምናየው እጅግ አስደናቂ የሆነ ንድፍ ምን ማለት ይቻላል? በሕዋስ ውስጥ ያሉት በጣም አነስተኛ የሆኑ ሞለኪዩሎችና አተሞች እንኳ አስደናቂ ንድፍ ያላቸውና በሚገባ የተደራጁ ናቸው። እጹብ ድንቅ ንድፍ ስላለው የሰው አእምሮስ ምን የምንለው ነገር አለ? ፕላኔታችን ያለችበት ሥርአት ፀሐይና አጽናፈ ዓለምስ? እነዚህ አስደናቂ ንድፍ ያላቸው ነገሮች ንድፍ አውጪ አያስፈልጋቸውምን?

ኢንሳይክሎፒዲያ አሜሪካና በሕያዋን ፍጥረታት ላይ የሚታየውን እጅግ ውስብስብ የሆነ አሰራርና አደረጃጀት በመጥቀስ እንዲህ ሲል ገልጿል፡- “አበቦችን ትናንሽ ነፍሳትን ወይም አጥቢ አስስሳትን በጥልቀት ስንመረምር የአካል ክፍሎቻቸው አቀማመጥ ለማመን በሚያዳግት ሁኔታ እንከን የማይወጣለት ሆኖ እናገኘዋለን።” እንግሊዛዊው የከዋክብት ተመራማሪ ሰር በርናርድ ሎቭል የሕያዋን ዘር አካላትን (Organisms) ኬሚካላዊ ውህደት በመጥቀስ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- “በጣም አነስተኛ ከሆኑት የፕሮቲን ሞለኪዩሎች መካከል አንዱን ሊያስገኝ የሚችለው አጋጣሚ…ሊከሰት የሚችልበትን ሁኔታ መገመት አዳጋች ነው። …እንዲያውም ፈጽሞ የማይታሰብ ነገር ነው።”

﴿ سَنُرِيهِمْ ءَايَٰتِنَا فِى ٱلْءَافَاقِ وَفِىٓ أَنفُسِهِمْ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَهُمْ أَنَّهُ ٱلْحَقُّ ۗ أَوَلَمْ يَكْفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ شَهِيدٌ ﴿٥٣﴾ ﴾ فصلت: ٥٣

*“እነርሱም (ቁርአን) እውነት መሆኑ ለእነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተአምራቶቻችንን*

*በእርግጥ እናሳያቸዋለን፡፡ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን?" (ሐ.ሚም አስ-ሰጅዳህ፡ 53)*

በተመሳሳይም የከዋክብት ተመራማሪ የሆኑት ፍሬድ ወይል እንዲህ ብለዋል፡-" የባዮሎጂና (*ሥነ-ሕይወት*) *መሠረታዊ ትምህርት አሁንም ሕይወት የተገኘው እንዲሁ ባጋጣሚ ነው የሚለውን አቋሙን ሙጭጭ ብሎ እንደያዘ ነው፡፡ ሆኖም ግን ባዮኬሚስቶች እጅግ አስደናቂ ስለሆነው የሕይወት ውስብስብነት ተጨማሪ ግኝቶች ላይ እየደረሱ በሄዱ መጠን ሕይወት በአጋጣሚ ተገኘ የሚባልባቸው ሁኔታዎች በጣም እያነሱ በመሄድ ከናካቴው እንደሚጠፉ ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ሕይወት በአጋጣሚ ሊገኝ አይችልምና፡፡*

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እያበቡ ካሉት የሳይንስ ዘርፎች አንዱ የሆነው ሞለኪዩላር ባዮሎጂ በጂን፣ በሞለኪዩልና በአተሞች ደረጃ ባሉ ሕያዋን ነገሮች ላይ የሚደረግ ጥናት ነው፡፡ የሞለኪዩላር ባዮሎጂ ሊቅ የሆኑት ሚካኤል ዴንተን በተደረሰበት ግኝት ላይ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተዋል፡- "*ከሚታወቁት ሕዋሶች ሁሉ በውስብስብነቱ ዝቅተኛ ደረጃ የሚሰጠው ሕዋስ እንኳን እጅግ ውስብስብ ከመሆኑ የተነሳ እንዲህ ዓይነቱ ነገር በአንድ እንግዳ በሆነና ፈጽሞ በማይመስል አጋጣሚ ድንገት ተገኘ ብሎ ማመን የማይቻል ነገር ነው፡ ሆኖም ነገሩን ለማመን እጅግ አስቸጋሪ የሚያደርገው እነዚህ ሕያዋን ነገሮች ውስብስብ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ብዙውን ጊዜ በንድፋቸው ላይ የሚንፀባረቀው እጅግ የረቀቀ የፈጠራ ችሎታም ጭምር ነው፡፡*"

ዴንተን በመቀጠል እንዲህ ሲሉ ገልፀዋል፡- "*በየትኛውም አቅጣጫ ብንመለከት የቱንም ያህል ጠልቀን ብንመረምር ሕይወት በአጋጣሚ የተገኘ ነው" የሚለውን ሐሳብ ተቀባይነት የሚያሳጣ ከፍተኛ የብቃት ደረጃ የሚታይበትና እጅግ የሚማርክ የፈጣሪ ችሎታ እናገኛለን፡፡ በአጋጣሚ የተከሰቱ ሂደቶች ከእኛ የፈጠራ ችሎታ በላይ የሆነን በጣም*

የተውሰበሰበ ነገር በአጋጣሚ ከሚገኙ ነገሮች ፍጹም የሚልቀውን ፕሮቲን ወይም ጂን (በራሂ) ሊያስገኙ ይችላሉ ብሎ ማመን ይቻላልን? በአንድ ሕያው ሕዋስ፣ የከበሩ ድንጋዮችን በመሰሉ በጣም የረቀቀ አሰራር ባላቸውና ሕይወት የሌላቸው በሆኑ ነገሮች መካከል ግልጽ የሆነ ሰፊ ልዩነት አለ።።"

ዴንተን ሃሳባቸውን ሲያጠቃልሉ እንዲህ ብለዋል፡- "አሁንም ግትር አቋም ይዘው ይህ ሁሉ አዲስ ነገር እንዲሁ በአጋጣሚ የተገኘ ነው ብለው የሚከራከሩ ሰዎች በተረት የሚያምኑ ናቸው።። እንዲያው "ሕያዋን ነገሮች የተገኙት በአጋጣሚ ነው" የሚለው የዳርዊን እምነት ስለ አጽናፈ ዓለም አመጣጥ የተነገረ የ19ኛው መቶ ዘመን ታላቅ ተረት ነው።።"

﴿ لِلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِالْآخِرَةِ مَثَلُ السَّوْءِ ۖ وَلِلَّهِ الْمَثَلُ الْأَعْلَىٰ ۚ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ ﴿٦٠﴾ ﴾

*"ለእነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም ለማያምኑት መጥፎ ጠባይ አላቸው ለአላህም ታላቅ ባሕሪይ አለው።። እርሱም አሸናፊውና ጥበበኛው ነው።።" (አን-ነሕል፡60)*

﴿ فَإِنَّكَ لَا تُسْمِعُ الْمَوْتَىٰ وَلَا تُسْمِعُ الصُّمَّ الدُّعَاءَ إِذَا وَلَّوْا مُدْبِرِينَ ﴿٥٢﴾ وَمَا أَنتَ بِهَادِ الْعُمْيِ عَن ضَلَالَتِهِمْ ۖ ﴾ الروم: ٥٢ - ٥٣

*"አንተም ሙታንን አታሰማም።። ደንቆሮዎችንም ዟሪዎች ሆነው በሸሹ ጊዜ ጥሪን አታሰማም።። አንተ እውሮችንም ከጥመታቸው የምታቀና አይደለህም…" (አር-ሩም፡52-53)*

ሕይወት የሌለው ነገር እንዲሁ በአጋጣሚ ፈጽሞ ሕያው ሊሆን አይችልም።። አያንዳንዱ ንድፍ የግድ አንድ ንድፍ አውጪ የሚያስፈልገው በመሆኑ በምድር ላይ ያሉት በጣም አስደናቂ የሆነ

ንድፍ ያላቸው ሕያዋን ነገሮች በሙሉ በድንገተኛ አጋጣሚ ሊመጡ አይችሉም። ያለ ንድፍ አውጪ የተገኘ ንድፍ ልትጠቅስ ትችላለህ? አንድም የለም። ንድፉ ይበልጥ ውስብስብ በሆነ መጠን የንድፍ አውጪው ችሎታም የዚያኑ ያክል የላቀ ይሆናል።

ሁኔታውን በሚከተለውም መንገድ በምሳሌ ማስረዳት ይቻላል። አንድን ቅብ ስንመለከት ቅቡ አንድ ቀለም ቀቢ እንዳለ የሚመሰክር መሆኑን አምነን እንቀበላለን። አንድ መጽሐፍ ስናነብ ያዘጋጀው ሰው እንዳለ እናምናለን። አንድን ቤት ስንመለከትም ቤቱን የሰራው ሰው እንዳለ እንረዳለን። የትራፊክን መብራት ስንመለከት አንድ ሕግ አውጪ አካል እንዳለ እናምናለን። ሰሪዎቻቸው እነዚህን ሁሉ ነገሮች የሰሩት በዓላማ ነው። እነዚህን ነገሮች ስለሰሩት ሰዎች ጠንቅቀን የማናውቅ ቢሆንም እንኳ ሰዎች መኖራቸውን እንደማንጠራጠር የታወቀ ነው።

በተመሳሳይም በምድር ላይ ያሉትን ሕያዋን ፍጥረታት ንድፍ አሰራር ውስብስብነት በመመልከት አንድ የላቀ ችሎታ ያለው ንድፍ አውጪ መኖሩን መረዳት ይቻላል። ሁሉም አንድ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ ያለው አካል እንዳለ ያመለክታሉ። እያንዳንዳቸው በቢሊዮን የሚቆጠሩ ከዋክብት የያዙ በቢሊዮን የሚቆጠሩ የከዋክብት ርጭቶች (clusters) ያቀፈው አጽናፈ ዓለም ያለው ንድፍ አሰራርና ውስብስብነት ይህንኑ የሚመሰክር ነው። ሁሉም ሰማያዊ አካላት የሚመሩት የእንቅስቃሴ፣ የብርሃን፣ የድምጽ፣ የኤሌክትሮ ማግኔቲዝምና የስበትን ኃይል ሕግ በመሰሉ ዝንፍ በማይሉ ሕጎች አማካኝነት ነው። ታዲያ ሕግ አውጪ ሳይኖር ሕጎች ሊኖሩ ይችላሉን?

የሮኬት ሳይንቲስት የሆኑት ጀርመናዊው ፎን ብራውን እንዲህ ብለዋል፡- “ የአጽናፈ ዓለም ሕጎች ፈጽሞ ዝንፍ የማይሉ በመሆናቸው ወደ ጨረቃ የሚመጥቅ መንኮራኩር ለመሥራት ምንም ዓይነት ችግር የማይገጥመን ከመሆኑም በላይ የበራሪውን ሰዓት በሰከንድ ክፋይ እንኳን

ሳይቀር ለይተን በትክክል ማስቀመጥ እንችላለን፡፡ እነዚህን ሕጎች ያወጣ አንድ አካል መኖር አለበት፡፡

﴿ٱلَّذِى خَلَقَ سَبۡعَ سَمَٰوَٰتٖ طِبَاقٗاۖ مَّا تَرَىٰ فِى خَلۡقِ ٱلرَّحۡمَٰنِ مِن تَفَٰوُتٖۖ فَٱرۡجِعِ ٱلۡبَصَرَ هَلۡ تَرَىٰ مِن فُطُورٖ ٣ ثُمَّ ٱرۡجِعِ ٱلۡبَصَرَ كَرَّتَيۡنِ يَنقَلِبۡ إِلَيۡكَ ٱلۡبَصَرُ خَاسِئٗا وَهُوَ حَسِيرٞ ٤﴾ الملك:

*“ያ ሰባትን ሰማያት የተነባበሩ ሆነው የፈጠረ ነው፡፡ በአር-ራሕማን አፈጣጠር ውስጥ ምንም መዛነፍን አታይም፡፡ ዓይንህንም (ወደ ሰማይ) መልስ ከስንጥቆች አንዳችን ታያለህን? ከዚያም ብዙ ጊዜ ዓይንህን መላልስ፡፡ ዓይንህ ተዋርዶ እርሱም የደከመ ሆኖ ወዳንተ ይመለሳል፡፡” (አል-ሙልክ:3-4)*

እርግጥ ነው ታላቁን ንድፍ አውጪና ሕግ ሰጪ በሥጋዊ ዓይናችን ማየት አንችልም፡፡ “ሳያዩ የሚያምኑ ብጹዓን ናቸው” እንዲል መጽሐፉ፡፡ ለመሆኑ ሁሉንም ምስጢራት በአይኑ በብረቱ ካየ ካስተዋለና ካረጋገጠ በኋላ የሚክድ ፍጡር ይገኛልን? ተቅዋ ማለት እንግዲህ ከስሜት ሕዋሳቶቻችን በራቁ ምስጢራት (ገይብ) ማመን እንጂ ሌላ አይደለም፡፡

﴿ٱلَّذِينَ يُؤۡمِنُونَ بِٱلۡغَيۡبِ وَيُقِيمُونَ ٱلصَّلَوٰةَ وَمِمَّا رَزَقۡنَٰهُمۡ يُنفِقُونَ ٣﴾ البقرة: ٣

*“ለእነዚያ በሩቅ ነገር (ከሕዋሳት በራቀው ነገር) የሚያምኑ...” (አል-በቀራህ: 3)*

ይሁን እንጂ የስበትን፣ የማግኔትን፣ ወይም የኤሌክትሪክን ኃይል እንዲሁም የሬዲዮ ሞገዶችን ልናያቸው ስላልቻልን ብቻ መኖራቸውን እናስተባብላለን? የሚያከናውኑትን ነገር ወይም የሚፈጥሩትን ተጽእኖ ስንመለከት መኖራቸውን ፈጽሞ አንክድም፡፡ እንግዲያው ታላቁ ንድፍ አውጪና ሕግ ሰጪ ያከናወናቸውን አስደናቂ ነገሮች መመልከት እየቻልን እርሱን ልናየው ስላልቻልን ብቻ መኖሩን እንዴት እንክዳለን?

﴿ لَّا تُدۡرِكُهُ ٱلۡأَبۡصَٰرُ وَهُوَ يُدۡرِكُ ٱلۡأَبۡصَٰرَۖ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلۡخَبِيرُ ﴿١٠٣﴾ ﴾ الأنعام: ١٠٣

*"ዓይኖች አያገኙትም (አያዩትም) እርሱም ዓይኖችን ያያል፡፡ እርሱም ርኅራሄው ረቂቁ ውስጠ አዋቂው ነው፡፡" (አል-አንዓም፡103)*

የፊዚክስ ፕሮፌሰር የሆኑት ፕል ዴቪስ የሰው ልጅ ወደ ሕልውና የመጣው እንዲሁ ድንገት በተከሰተ አጋጣሚ እንዳልሆነ ተናግረዋል፡፡

"ወደ ሕልውና የመጣው በዓላማ ነው" ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ስለ አጽናፈ ዓለም ሲናገሩም እንዲህ ብለዋል፡-"ያካሄድኩት ሳይንሳዊ ምርምር ግኡዝ አጽናፈ ዓለም እጅግ አስደናቂ በሆነ የፈጠራ ችሎታ የተንቀሳቀሰ ነው ብዬ መደምደም ያዳግተኛል፡፡ ይበልጥ ጥልቀት ያለው ማብራሪያ መኖር ያለበት ይመስለኛል፡፡"

﴿ سَنُرِيهِمۡ ءَايَٰتِنَا فِي ٱلۡأٓفَاقِ وَفِيٓ أَنفُسِهِمۡ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَهُمۡ أَنَّهُ ٱلۡحَقُّۗ أَوَلَمۡ يَكۡفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ﴿٥٣﴾ أَلَآ إِنَّهُمۡ فِي مِرۡيَةٖ مِّن لِّقَآءِ رَبِّهِمۡۗ أَلَآ إِنَّهُۥ بِكُلِّ شَيۡءٖ مُّحِيطُۢ ﴿٥٤﴾ ﴾ فصلت: ٥٣ - ٥٤

*"እርሱም (ቁርአን) እውነት መሆኑ ለእነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን፡፡ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን? ንቁ! እርሱ በነገሩ ሁሉ (እውቀቱ )ከባቢ ነው፡፡ (ሐ.ሚም. አስ-ሰጅዳህ፡ 53-54)*

እንግዲህ የሰው ልጅ በተለይም ከእስልምና ኃይማኖት ውጭ የሚገኘው አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ቀናውን ጐዳና እንዳይከተል ያደረጉትን ብዙ ምክንያቶች ማስቀመጥ ቢቻልም ዋናውና ትልቁ አላህን ማወቅ የሚገባውን ያህል አለማወቁ ነው፡፡ የአላህ ባህሪያትና ስሞች ይህን ዓለምና በውስጡ ያሉ ነገሮችን፣ ፍጥረታትንና የሰው ልጅን ለምን

እንደፈጠራቸውም ካላወቀ ደግሞ አላህን ሊፈራ (ተቅዋ ሊኖረው) አይችልም፡፡ ስለሆነም ባልተሸራረፈና ባልተከፋፈለ መልኩ የዓለማቱን ጌታ አላህን ማወቁ የሕይወትንም ግብ ከማወቅ ጋር ጥብቅ ትስስር አለው፡፡ እናም…

﴿ وَمَا قَدَرُوا۟ ٱللَّهَ حَقَّ قَدْرِهِۦ وَٱلْأَرْضُ جَمِيعًا قَبْضَتُهُۥ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ وَٱلسَّمَٰوَٰتُ مَطْوِيَّٰتٌۢ بِيَمِينِهِۦ ۚ سُبْحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿٦٧﴾ ﴾ الزمر: ٦٧

*"አላህንም በትንሣኤ ቀን ምድር በመላ ጭብጡ ስትሆን ሰማያትም በኃይሉ የሚጠቀለሉ ሲሆኑ (ከእርሱ ጋር ሌላን በማጋራታቸው) ተገቢ ክብሩን አላከበሩትም፡፡ ከሚያጋሩት ጠራ፤ ላቀም፡፡" (አዝ-ዙመር፡ 67)*

﴿ وَلَقَدْ ذَرَأْنَا لِجَهَنَّمَ كَثِيرًا مِّنَ ٱلْجِنِّ وَٱلْإِنسِ ۖ لَهُمْ قُلُوبٌ لَّا يَفْقَهُونَ بِهَا وَلَهُمْ أَعْيُنٌ لَّا يُبْصِرُونَ بِهَا وَلَهُمْ ءَاذَانٌ لَّا يَسْمَعُونَ بِهَآ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ كَٱلْأَنْعَٰمِ بَلْ هُمْ أَضَلُّ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْغَٰفِلُونَ ﴿١٧٩﴾ ﴾ الأعراف: ١٧٩

*"ከጋኔንም ከሰዎችም ብዙዎችን ለገሃነም በእርግጥ ፈጠርን፡፡ ለእነርሱ በርሳቸው የማያውቁባቸው ልቦች አሏቸው፡፡ ለእነርሱም በእርሳቸው የማያዩባቸው አይኖች አሏቸው፡፡ ለእነርሱም በእርሳቸው የማይሰሙባቸው ጆሮዎች አሏቸው፡፡ እነዚያ እንደ እንስሳዎች ናቸው፡፡ …" (አል-አዕራፍ፡ 179)*

# ምዕራፍ ሦስት

## በሁሉም ጉዳዮችህ ውስጠ ተቅዋ (የአላህ ፍራቻ) ይኑርህ

ሕይወት አቀበትና ቁልቁለት የሞላባት መሆኗ ያለና የነበረ ነው። የሰው ሕልውና ምሶሶና ማገር ሕይወት ውጣ ውረድ ያለባት እንድትሆን በማድረጉ ዙሪያ የተማከለ ይመስላል። እናም አንድ ጊዜ ችግርና መከራን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሃብትና ምቾትን የሰው ልጅ ያስተናግዳል። ሃዘንና ጭንቀት ደህና አድርገው የሚገርፉት የመሆኑን ያክል የደስታና የፍሰሃ ዘመናትም ይገኙበታል። እንግዲህ ከሞላ ጉደል የዚህችን ዓለም አካሄድ ካስተዋልናት ሰው ከደስታው ይልቅ ሃዘኑና መከራው የበዛ ሆኖ እናገኘዋለን።

የዓለማት ጌታ አላህም ይህንኑ ሃቅ እንዲህ በማለት ያንፀባርቃል፡-

﴿ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلْإِنسَـٰنُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ رَبِّكَ كَدْحًا فَمُلَـٰقِيهِ ۝٦ ﴾ الانشقاق: ٦

*“አንተ ሰው ሆይ! አንተ ጌታህን (በሞት) እስከምትገናኝ ድረስ ልፋትን ለፊ ነህ ተገናኚውም ነህ።” (አል-ኢንሺቃቅ:6)*

እንግዲህ በሁሉም የሕይወት እንቅስቃሴያችን አላህን ልንፈራ ወይም ተቅዋ ሊኖረን ይገባል። የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን ጉዳይ አጽንኦት ሰጥተው ሲገልጹ፡-

“በችግርም ሆነ በምቾት ጊዜ አላህን ፍራ።” ብለዋል።

ስለሆነም በመከራና ሁኔታዎች ጥሩ በማይሆኑበት ጊዜ ትእግስት ማድረግና ሚዛንን ሳይስቱ የአላህን እገዛ በመሻት ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር መሞከር ተገቢ ነው። ብልጽግናና ሰላም በሰፈነበት ጊዜ ደግሞ አላህ ለሰጠን ፀጋ አመስጋኞች ሆነን መገኘት ይኖርብናል። ከዚያ

በመለስ ግን ጉራ በመቸርቸርና አለሁ አለሁ በማለት ራስን ለዝቅጠት መዳረግ የአንድ አማኝ ባህሪ አይደለም፡፡ አንድ የሚያስደስት ሁኔታ ሲገጥመንም ከጀርባው አላህ የሻው አንዳች ጥበብና ለእኛ ጥሩ የሆነ ነገር ይኖራል ብለን መልካም ትእግስትን በማድረግ ምሬትን ማስወገድ አለብን፡፡

“ይህ ጉዳይ ለእኔ መልካም ነገር በውስጡ ይዞልኝ ይሆናል፤ ወይም አላህ ደግን ነገር በዚህ በደረሰብኝ መከራ ምክንያት ይሰጠኝ ይሆናል” ማለት ይኖርብናል፡፡

## ወደ አላህ የመቃረቢያ መንገዶች

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَٱبْتَغُوٓاْ إِلَيْهِ ٱلْوَسِيلَةَ وَجَـٰهِدُواْ فِى سَبِيلِهِۦ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ﴿٣٥﴾ ﴾ المائدة: ٣٥

*“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ ወደርሱም መቃረቢያን (መልካም ሥራን) ፈልጉ፡፡ ትድኑ ዘንድም በእርሱ መንገድ ታገሉ፡ ፡” (አል-ማኢዳህ፡35)*

ታዲያ ወደ አላህ ሊያቃርቡን የሚችሉ እውነተኛ መንገዶች የትኞቹ ናቸው? የመጀመሪያው ነፍስን ከዝንባሌዋ መግታትና ማንጻት፣ አላህን በብዙ ማውሳትና ትእዛዛቱን መጠበቅ እንዲሁም ለአላህና ለመልእክተኛው (ሰ.0.ወ.) ያለንን ፍቅር በየጊዜው ከፍ ማድረግ ወዘተ…ናቸው፡፡

ኃያሉ ጌታችን አላህ እንዲህ ይለናል፡-

﴿ فَٱذْكُرُونِىٓ أَذْكُرْكُمْ وَٱشْكُرُواْ لِى وَلَا تَكْفُرُونِ ﴿١٥٢﴾ ﴾ البقرة: ١٥٢

*“አስታውሱኝ አስታውሳችኋለሁና፡፡ እኔንም አመስግኑ አትካዱኝም፡፡” (አል-በቀራህ፡ 152)*

﴿ إِنَّ فِي خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفِ ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ لَءَايَٰتٍ لِّأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٠﴾ ٱلَّذِينَ يَذْكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِى خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَٰطِلًا سُبْحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿١٩١﴾ ﴾ آل عمران: ١٩٠ - ١٩١

*“ሰማያትና ምድርን በመፍጠር ሌሊትና ቀንንም በመተካካት ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አሉ፡፡ (እነርሱም) እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠውም አሳህን የሚያወሱ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ ጌታችን ሆይ! ይህን በከንቱ አልፈጠርከውም፤ ጥራት ይገባህ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን የሚሉ ናቸው፡፡” (አሊ-ዒምራን፡190-191)*

# ምዕራፍ አራት

## ወደ መድህን የሚያቃርቡን ምስጢራት

የተወሰኑ የቁርአን አንቀፆች የሚጀምሩት በመሃላ ሲሆን ይህም የአንባቢውን ትኩረት ወደ አንድ ጠቃሚ አቅጣጫ ለመሳብ የታለመ ነው። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ደግሞ አላህ የሚምልባቸው ነገራት ብዛት በዚያ አንቀጽ ይበልጥ አጽንኦት ሰጥቶ ሊገልጻቸው እንደሚፈልጋቸው መልእክቶች ብዛት ይጨምራል። ለምሳሌ በሱራ አሽ-ሽምስ መጀመሪያ ላይ በሰባት ተፈጥሮአዊ አካላትና ክስተቶች ምሏል። በመጨረሻም መሃላውን የሚያሳርገው ስለነፍስ አፈጣጠርና በውስጥ ስለያዘችው ዝንባሌ በማውሳት ሲሆን ይህንን ዝንባሌ ወደ አፍራሽ መንገድ መምራት ወይም ነፍስ አፍራሽ የሆነውን ዝንባሌዋን እንድትከተል መፍቀድ (መልቀቅ) በፍርዱ ቀን አንገት የሚያስደፋና የሚያሳፍር እንደሆነ እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

﴿ وَٱلشَّمْسِ وَضُحَىٰهَا ١ وَٱلْقَمَرِ إِذَا تَلَىٰهَا ٢ وَٱلنَّهَارِ إِذَا جَلَّىٰهَا ٣ وَٱلَّيْلِ إِذَا يَغْشَىٰهَا ٤
وَٱلسَّمَآءِ وَمَا بَنَىٰهَا ٥ وَٱلْأَرْضِ وَمَا طَحَىٰهَا ٦ وَنَفْسٍ وَمَا سَوَّىٰهَا ٧ فَأَلْهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقْوَىٰهَا
٨ ﴾ الشمس: ١ - ٨

*“በፀሐይና በብርሃኗ እምላለሁ። በጨረቃም፣ በተከተላት ጊዜ፣ በቀኑም (ፀሐይን) በገለጻት ጊዜ፣ በሌሊቱም በሸፈናት ጊዜ፣ በሰማይቱም በገነባትም (ጌታ)፣ በምድሪቱም በዘረጋትም፣ በነፍስም ባስተካከላትም፣ አመጽዋንና ፍርሃቷንም ባሳወቃት (አምላክ እምላለሁ)።” (አሽ-ሽምስ፡ 1-8)*

የዓለማት ጌታ አላህ ይህን ካለ በኋላ የመሃላውን ዋነኛ ጉዳይ እንዲህ በማለት ያነሳል ፡-

﴿ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ۝٩ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ۝١٠ ﴾ الشمس: ٩ - ١٠

*"...(ከሃጢአት) ያጠራት ሰው ፍላጐቱን በእርግጥ አገኘ፡፡ (በሃጢአት) የሸፈናትም ሰው በእውነት አፈረ፡፡" (አሽ-ሽምስ፡ 9-10)*

**ቁርአን በዚህ አገላለጽ ነፍስ ለሁለት ተቃርኖዎች የተገራች መሆኗንና ወደ አመጽም ሆነ ወደ ተቅዋ (አላህን ወደ መፍራት) ትሄድ ዘንድ ተጽእኖ ሊያደርግባት የሚችለው ባለቤቷ ራሱ መሆኑን ነው የሚያስገነዝበን፡፡ ስለሆነም ተቅዋን ለመላበስ ወሳኙ ነገር የነፍስን አፍራሽ ዝንባሌ መግታት ነው ማለት ነው፡፡**

## ወደ ተሳሳተው ጐዳና አትዘናበል

**በሃይማኖት ጉዳይ ላይ መደራደር የለም፡፡ አንድ ሰው አምኛለሁ ካለ ከሃዲያንንና ሃጢአተኛ የሆኑ ሰዎችን ጨርሶ መራቅ ነው ያለበት፡፡ ቁርአን እንዲህ ይለናል፡-**

﴿ فَلَا تُطِعِ ٱلۡمُكَذِّبِينَ ۝٨ وَدُّواْ لَوۡ تُدۡهِنُ فَيُدۡهِنُونَ ۝٩ وَلَا تُطِعۡ كُلَّ حَلَّافٍ مَّهِينٍ ۝١٠ هَمَّازٍ مَّشَّآءِۭ بِنَمِيمٍ ۝١١ مَّنَّاعٍ لِّلۡخَيۡرِ مُعۡتَدٍ أَثِيمٍ ۝١٢ عُتُلِّۭ بَعۡدَ ذَٰلِكَ زَنِيمٍ ۝١٣ ﴾ القلم: ٨ - ١٣

*"ለአስተባባዮችም አትታዘዙ፡፡ ብትመሳሰላቸውና ቢመሳሰሉህ ተመኙ፡፡ መሐለኛ ወራዳንም ሁሉ አትታዘዙ፡፡ ሰውን አነዋሪና በማሳበቅ ሂያጅን፡፡ ለበጐ ነገር ከልካይን ወሰን አላፊንና ኃጢአተኛን፡፡..." (አል-ቀለም፡ 8-13)*

**ጥበበኛው አላህ ይህን የሚመክረን ለምንድን ነው? ይህ ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም የሰው ነፍስ በተፈጥሮዋ አቀማማጯንና አኗኗሪዋን ስለምትመስል ነው፡፡ አላህ እንደገናም በሌላ አንቀጽ የሚከተለውን ተግሳጽ ይሰጠናል፡-**

﴿ وَلَا تَرۡكَنُوٓاْ إِلَى ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ فَتَمَسَّكُمُ ٱلنَّارُ ﴾ هود: ١١٣

*"ወደእነዚያ ወደ በደሉት አትጠጉ እሳት ትነካችኋለችና፡፡...." (ሁድ፡113)*

ለጓደኝነትና ለመኗኗር በምንመርጣቸው ሰዎችና በእምነታችን ጥንካሬ መካከል ቀጥተኛ የሆነ ትስስር እንዳለ እናስተውል፡፡ ምክንያቱም መጥፎና ኃጢአተኛ እንዲሁም ልበ ደረቅ ከሆኑ ሰዎች (ሙስሊምም ቢሆኑ ማለት ነው) ጋር መዋል ካበዛን የኋላ ኋላ ከእነርሱ ጋር ያለን የባሕሪና የአመለካከት ልዩነት እየጠበበ ሄዶ በመጨረሻም ተመሳስለነው ስለምናርፍ ነው፡፡ ይህ መመሳሰል ደግሞ በዚህች በቅርቢቱ ዓለም ላይ ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን እስከ መጪው ዓለምም አብሮ የሚዘልቅ መሆኑን በብርሃንና በሃቅ ብቻ የተሞላው መጽሐፍ ቁርዓን ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَيَوۡمَ يَعَضُّ ٱلظَّالِمُ عَلَىٰ يَدَيۡهِ يَقُولُ يَٰلَيۡتَنِي ٱتَّخَذۡتُ مَعَ ٱلرَّسُولِ سَبِيلٗا ٢٧ يَٰوَيۡلَتَىٰ لَيۡتَنِي لَمۡ أَتَّخِذۡ فُلَانًا خَلِيلٗا ٢٨ لَّقَدۡ أَضَلَّنِي عَنِ ٱلذِّكۡرِ بَعۡدَ إِذۡ جَآءَنِيۗ وَكَانَ ٱلشَّيۡطَٰنُ لِلۡإِنسَٰنِ خَذُولٗا ٢٩ ﴾ الفرقان: ٢٧ - ٢٩

*"በዳይም - ከመልእክተኛው ጋር ቀጥተኛን መንገድ ይዤ በሆነ ዋ ምኞቴ! እያ (በጸጸት) ሁለት እጆቹን (የጣቶቹን አጽቆች) የሚነክስበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ ዋ ጥፋቴ! እገሌን ወዳጅ ባልያዝኩ ኖሮ እመኛለሁ፡፡ (የእምነት ቃል) ከመጣልኝ በኋላ ከማስታወስ በእርግጥ አሳሳተኝ (ይላል) ሰይጣንም ለሰው አጋላጭ ነው፡፡" (አል-ፉርቃን፡ 27-29)*

አላህ እርሱን ከማይወዱና የእርሱም ጠላቶች ከሆኑ ሰዎች ጋር እንዳንቀራረብ ወዳጅና ጓደኛም አድርገን እንዳንይዛቸው እንዲህ በማለት በግልጽ መክሮናል ፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَتَّخِذُواْ عَدُوِّي وَعَدُوَّكُمۡ أَوۡلِيَآءَ تُلۡقُونَ إِلَيۡهِم بِٱلۡمَوَدَّةِ وَقَدۡ كَفَرُواْ بِمَا جَآءَكُم مِّنَ ٱلۡحَقِّ ﴾ الممتحنة: ١

*"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጠላቶቼንና ጠላቶቻችሁን ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዙ፡፡ ከእውነቱ የመጣላችሁን ኃይማኖት በእርግጥ የካዱ ሲሆኑ ውዴታን ወደነርሱ ታደርጋላችሁ፡፡" (አል-ሙምተሂናህ፡1)*

ክቡሩ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"ከመልካም ሰው ጋር የሚቀመጥ ልክ ከሽቶ ሻጭ (ነጋዴ) ጋር እንደተቀመጠ ሰው ነው፡፡ ነጋዴው ሽቶ ሲሸጥ መልካም መዓዛ ይሸተዋል ወይም ራሱ ይገዛል፡፡ ከመጥፎ ሰው ጋር የሚቀማመጥ ደግሞ ከወናፍ ነፊ ጋር እንደተቀመጠ ሰው ነው፡፡ ይህ ሰው ከባለወናፉ ጋር ሲቀመጥ የእሳቱ ፍንጣሪ ወይም አመዱ ይነካዋል፡፡"

የአላህ መልእክተኛ እንዲህም ብለዋል፡-

"መናፍቃንን ጌታዬ (አለቃዬ) ብላችሁ አትጥሯቸው፡፡ ምክንያቱም ይህ ሁኔታ ያንን ከሃዲ የእናንተ የበላይ ከማድረጉም በላይ የጌታችሁን ቁጣም ያስከትልባችኋል፡፡" (አቡ ዳውድ)

በተጨማሪም እንዲህ ብለዋል፡-

"ከሕዝቦች ጋር የተመሳሰለ ከእነርሱ እንደሆነ ይቆጠራል፡" (አቡ ዳውድ)

ተቅዋን በልብ ላይ ለማሳደር ብዙ ጥረቶችን የሚጠይቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም የከሃዲያንን፣ የአይሁዶችን፣ የክርስቲያኖችንና የቁሳካላውያንን ባሕል፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ እንዲሁም የሃይማኖታዊ ወጉቻቸውን መከተል (መደገፍና ማድነቅ) በቀልብ ላይ የሚያሳድረው የራሱ የሆነ ተጽእኖ አለው፡፡ ለዚህም ነው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ተከታዮቻቸው የሙሐረምን 10ኛ ቀን እንዲፆሙ

ሲያዝዙ 9ኛውንና 11ኛውንም ቀን አብረው እንዲፆሙ የመከሩት፡፡ ምክንያቱም የሙሐረምን 10ኛ ቀን ብቻ አይሁዳውን ይፆሙ ስለነበር ነው፡፡ ስለዚህም የአላህ መልእክተና (ሰ.ዐ.ወ.) ከሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ጋር በማያመሳስለን መልኩ እምነታችንን እንድናራምድ ይህንን ለይተው ደነገጉልን፡፡

እናም በማይረቡ ሃሳቦች ልባችንን ማጨናነቅ እንዲሁም የከሃዲያንን የአኗኗር ዘይቤ በመኮረጅ ሁሉንም ነገር ወደ ቀልባችን ማስገባት የደም ሥርን በስህተት ከመቁረጥ ጋር ይመሳሰላል፡፡ የደም ሥር አንድ ጊዜ ከተቆረጠ ደም ፈስሶ ስለሚያልቅ ለሞት ሊዳርግ ይችላልና፡፡

ልብ (ቀልብ) ራሷን የቻለችና ሌላው ቀርቶ (የትእዛዛት ሁሉ ማእከል) የሆነው አእምሮ ከሞተ በኋላ እንኳን መምታት የምትቀጥል መሆኗ ተደርሶበታል፡፡ ስለሆነም የልብን ብክለት ከሚያስከትሉ እሳቤዎችና ድርጊቶች መጠበቅ ተቅዋን ለማግኘት ዋነኛው መንገድ ነው፡፡

## ሁልጊዜም ከእውነተኞች ጋር ሁኑ

ብዙውን ጊዜ በአንዱ ወይም በሌላ ምክንያት አብረናቸው ከምንሆነው ሰዎች በኩል ተጽእኖ የሚያርፍብን መሆኑ ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ እርግጥ ነው በስራ ወይም በአንዳንድ ማኅበራዊ ጉዳዮች አካሄዳቸውን ከቁርአንና ከኢስላማዊ እሴቶች ጋር ማስኬድ ከማይችሉ እንዲሁም ጭራሽ የሌላ ሐይማኖት ተከታይ ወይም ዓለማዊ ከሆኑ ሰዎች ጋር ልንገናኝ እንችላለን፡፡ ሆኖም ግን በዚያ ጊዜ ምን ማድረግና እስከምን ድረስ ርቀን መሄድ እንዳለብን የምንወስነው እኛው ነን፡፡ ይህን ሁሉ ሳናደርግና ሳንታገል ተቅዋ እንደ ዛር እላያችን ላይ እንዲሰፍርብን መጠበቅ የለብንም፡፡ የአለማቱ ጌታ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَن جَٰهَدَ فَإِنَّمَا يُجَٰهِدُ لِنَفۡسِهِۦٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَغَنِيٌّ عَنِ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٦ ﴾ العنكبوت: ٦

*“የታገለ ሰው የሚታገለው ለነፍሱ ነው፡፡ አላህ ከዓለማት በእርግጥ ተብቃቂ ነውና፡፡” (አል-ዐንከቡት፡6)*

እውነትን አጥብቆ መያዝ እና በሃቅ ላይ መቆም የጽድቅ ሥራ ሲሆን የአላህን እዝነት ለማግኘትና ልብንም ለማቅናት ወሳኝ ነው፡፡ እውነትንና እውነተኞችን እንደሚወድ አላህ በብዙ ቦታዎች ላይ በቁርአን የገለጸ ሲሆን ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ቀርበዋል፡-

﴿...وَٱلصَّٰدِقِينَ وَٱلصَّٰدِقَٰتِ ...﴾ الأحزاب: ٣٥

*“...እውነተኞች ወንዶችና እውነተኞች ሴቶች...” (አል-አሕዛብ፡35)*

﴿...فَلَوۡ صَدَقُواْ ٱللَّهَ لَكَانَ خَيۡرٗا لَّهُمۡ ٢١﴾ محمد: ٢١

*“...እውነተኞች ቢሆኑ ኖሮ ለእነርሱ የተሻለ በሆነ ነበር፡፡” (ሙሐመድ፡ 21)*

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَكُونُواْ مَعَ ٱلصَّٰدِقِينَ ١١٩﴾ التوبة: ١١٩

*“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ ከእውነተኞቹም ጋር ሁኑ፡፡” (አል ተውባህ 119)*

ተወዳጁ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) እውነት አርነት እንደሚያመጣ ሲገልጹ እንደሚከተለው ብለዋል፡-

“እውነት ወደ በጎ ተግባር ይመራል፡፡ በጎ ተግባር ደግሞ ወደ ገነት ይመራል፡፡ አንድ ሰው አላህ ዘንድ እውነተኛ ተብሎ እስከመመዘገብ (እስከሚሰየም) ድረስ እውነተኛ ይሆናል፡፡ ውሸት ወደ ክፉ ሥራ ይመራል፡፡ ክፉ ሥራ ደግሞ ወደ ገሃነም እሳት ይመራል፡፡ አንድ ሰው

አላህ ዘንድ ዋሾ ሰው ተብሎ እስከመመዝገብ (እስከሚሰየም) ድረስ ይዋሻል፡፡” (ቡኻሪና ሙስሊም)

አቡ ሙሐመድ ሐሰን ቢን አሊይ ቢን አቡ ጧሊብ (ረ.ዐ.) ባወሩትና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“የምትጠረጥረውን ነገር ትተህ የማትጠረጥረውን ነገር ያዝ፡፡ እውነት የሕሊና እርካታ ሲሆን ውሸት ሕሊናን ሰላም የሚነሳ ጥርጣሬ ነውና፡፡”

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“ሻጭና ገዥ የሚያደርጉት የሽያጭ ስምምነት ሁለቱ ተለያይተው እስካልሄዱ ድረስ ሊፈርስ ይችላል፡፡ ሻጭና ገዥ እውነትን ከተናገሩ ግብይይታቸው ብሩክ ይሆናል፡፡ (የሸቀጡን ነውር) እንከኑን ከደበቁና ከዋሹ ገን ግብይታቸው በረከት አልባ ይሆናል፡፡” (ቡካሪና ሙስሊም)

ሰዕዲ ሲራዚ ከእውነተኞች ጋር የመሆንን ትሩፋት ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡-

“የዋሻው ባለቤቶች (አስሃቡል ከህፍ) ውሻ ከእነርሱ ጋር ስለነበረ ብቻ በዓለም ላይ ካሉ ውሾች ሁሉ ተለይቶ በቁርአንና በታሪክ መጽሐፍት ሊጠቀስና ሊወሳ ችሏል፡፡

በሌላ በኩል ከእውነት ጋር የተፋቱና ሃሰትን መከተል የመረጡ ወገኖች፣ ሌላው ቀርቶ እንደ ነቢዩ ኑህ (ዐ.ሰ.) ያሉ የአላህ ወዳጆች ሚስቶች ቢሆኑ እንኳን ከአሰቃቂው የምድር ላይ ቅጣትና ዘላለማዊ ከሆነው የመጪው ዓለም እሳት አይተርፉም፡፡ ይህ የሚያሳየን መልካም ሥራና እውነተኛነት እንጂ ከመልካም ሰዎች ጋር በዘርና በጋብቻ መተሳሰር አርነት (ፈላህ) እንደማያወጡ ነው፡፡ ተከታዩ ሐዲስ ከዚህ አባባል ጋር ተለክቶ እንደተሰፋ ልብስ ስምሙ ነው፡-

አቡ ሁረይራ ባወሩትና ሙስሊም በዘገቡት መሰረት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አንድን አማኝ ካለበት አለማዊ ጭንቅ የገላገለ ሰው አላህ ከፍርዱ ቀን ጭንቀቶች አንዱን ይገላግለዋል፡፡…ሰዎች ከአላህ ቤቶች በአንዱ ተሰብስበው የአላህን መጽሐፍ በሚያነብቡበት ወቅት በእነርሱ ላይ እርጋታ ይሰፍናል፡፡ የአላህ እዝነትም ይከብባቸዋል፣ መላእክትም ያጅቧቸዋል፡፡ አላህም ለእርሱ ቅርብ ከሆኑ ክፍሎች (መላእክት ዘንድ) ያወሳቸዋል፡፡ ሥራው (ወደ ኋላ) የሚጐትተው ዘሩ ወደፊት አያስቀድመውም፡፡”

## ፍም እሳትን እንደመጨበጥ

በሐዲስ እንደተጠቀሰው የሰዎች ሁሉ ዓይነታ የሆኑት ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“ለአረቦች ወዮላቸው !ታላቅ የሆነ ፈተና ተደቅኖባቸዋልና፡፡ ይህ መከራ ልክ እንደ ሌሊት ቁራጮች ነው፡፡ አንድ ሰው ምእመን ሆኖ አንግቶ ከሃዲ (ካፊር) ሆኖ የሚያመሽባት፣ ሙእሚን ሆኖ አምሽቶ ካፊር ሆኖ የሚያነጋበትና ለዓለማዊ ጥቅም (ለዱንያ) ብሎ ኃይማኖቱን የሚሸጥበት ጊዜ ይመጣል፡፡ በዚያ ጊዜ ኃይማኖቱን አጥብቆ የያዘ በእጁ ፍም እንደጨበጠ ያክል ነው፡፡” (አህመድ፣ሙስሊም ቲርሚዚ)

## በአምልኮት በተለይም በሶላት ውስጥ የተቅዋ አስፈላጊነት

ለአላህ በምናደርጋቸው አምልኮቶች ላይ ይበልጥ ጠንቃቃዎች በሆንንና ይበልጥ ወደ አላህ በቀረብን ቁጥር ተቅዋ እያገኘ መሄዳችን አይቀርም፡፡ ለአላህ በምናቀርበው ማንኛውም የአምልኮት ተግባር ላይ በግዴለሽነትና በግብር ይውጣ ሳይሆን ጥንቃቄ ካለን ብቻ ነው ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት የምናገኘው፡፡ ለምሳሌ ሰላትን እንመልከት፡፡ ሶላት እንድንሰግድ በዋነኛነት

የተፈለገበት ምክንያት በየእለቱና በየቀኑ የተለያዩ ክፍሎች ከአላህ ጋር ያለን ትስስር እንዲጠናከርና ፀንቶ እንዲቆይ እንዲሁም እኛም ከእኩይ ምግባራት እንድንርቅ ታስቦ ነው፡፡ ይህ ከእያንዳንዱ የሶላት ወቅት ጀርባ በግልጽ የሚንፀባረቅ መለኮታዊ ጥበብ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿....وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ تَنْهَىٰ عَنِ ٱلْفَحْشَآءِ وَٱلْمُنكَرِ وَلَذِكْرُ ٱللَّهِ أَكْبَرُ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ مَا تَصْنَعُونَ ﴿٤٥﴾﴾ العنكبوت: ٤٥

*"....ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፡፡ ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡ አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው.." (አል-ዐንከቡት፡45)*

እንግዲህ ዋነኛው ጥያቄ የሚነሳው እዚህ ላይ ነው፡፡ እውነት እኛ የምንሰግደው ሶላት ከመጥፎ (ፋህሻእ) እና ከሚጠላ (ሙንከር) ይከለክለናልን? መልሳችን አወንታዊ ከሆነ እሰየው ነው፡፡ ምንኛ የስኬት ማማ ላይ የወጣን ሰዎች ነን! መልሳችን አሉታዊ ከሆነ ግን በታላቅ አደጋ ላይ መሆናችንን ማወቅ አለብን፡፡

ተከታዩ የቁርአን አንቀጽም ቢሆን በሶላት ላይ ሲሆኑ ምእመናን ልባቸውና ድምጻቸው ወደ አላህ ብቻ መሆን እንዳለበት ነው የሚናገረው፡-

﴿كَلَّا لَا تُطِعْهُ وَٱسْجُدْ وَٱقْتَرِب ﴿١٩﴾﴾ العلق: ١٩

*"...ስገድም (ወደ አላህ) ተቃረብም፡፡" (አል-ዐለቅ፡19)*

ሆኖም ግን ሃቁ ያለው ወዲህ ነው፡፡ ብዙዎቻችን በሶላታችን ውስጥ ሆነን አላህን ከምናስታውሰው የበለጠ ስለቤተሰባችን፣ ንግዳችን፣ ሥራችን ወይም አንዳች ማኅበራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ጉዳይ ነው የምናብሰለስለው፡፡ ይህ ደግሞ ግልጽ የሆነ የሰይጣን ጉትጎታ ውጤት

ነው። አላህ ባዘዘን መልኩና መልእክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ.) የሰገዱትን ዓይነት ሶላት ብንሰግድ ኖሮ ቤተሰባዊ ሕይወታችን ባማረ፣ ንግዳችን በሰመረና በማንኛውም ተግባራችን ለስኬት በበቃን ነበር። በዚህም አለ በዚያ ቀጣዩ የቁርአን አንቀጽ ለብዙዎቻችን አሳሳቢና እጅግ አስፈሪ እንደሆነብን እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ ይዘልቃል፡-

﴿ فَوَيْلٌ لِّلْمُصَلِّينَ ۝٤ ٱلَّذِينَ هُمْ عَن صَلَاتِهِمْ سَاهُونَ ۝٥ ﴾ الماعون: ٤ - ٥

*"ወዮላቸው ለሰጋጆች! ለእነዚያ እነርሱ ከስግደታቸው ዘንጊዎች ለሆኑት (ሰጋጆች)።" (አል-ማዑን፡4-5)*

በሌላ መለኮታዊ አንቀጽ አላህ ሶላታቸውን እርሱን እየፈሩና ተገቢውን ክብሩን እየሰጡት የሚሰግዱ ለሆኑ ምእመናን ብስራቱን ሲገልጽላቸው እንዲህ ይላል፡-

﴿ قَدْ أَفْلَحَ ٱلْمُؤْمِنُونَ ۝١ ٱلَّذِينَ هُمْ فِى صَلَاتِهِمْ خَٰشِعُونَ ۝٢ ﴾ المؤمنون: ١ - ٢

*"ምእመናን ፍላጎታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ (ዳኑ)። እነዚያ እነርሱ በስግደታቸው ውስጥ (አላህን) ፈሪዎች።" (አል-ሙእሚኑን፡1-2)*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ጊዜ ሶላት እየሰገደ ከጺሙ ጋር የሚጫወትን ሰው ተመልክተው እንዲህ አሉ፡- "ተመልከቱ! የዚህ ሰው ልብ አላህን ብትፈራ (ኹሹዕ ቢኖራት) ኖሮ አካላቱ ሁሉ አላህን ይፈሩ (ይረጋጉ) ነበር።"

## በፆም ወቅት የተቅዋ አስፈላጊነት

ፆም የአላህን ውዴታ በመሻትና ምንዳውንም በመከጀል ከምግብና መጠጥ እንዲሁም ፀያፍ ከሆኑ ምግባራት ራስን ማቀብ ማለት ነው። ፆም ትክክለኛ በሆነና ተቀባይነት ባለው ሥነ -ምግባር እስከተመራ ድረስ

የጂሚውን ሁለንተናዊ ባሕሪ የመግራት፣ ነፍሱን የማርረቅና ወደ አላህ ይበልጥ የማስጠጋት ሚና አለው። በፆም ውስጥ ሌላው የምናገኘው ጥቅም በቀን ውስጥ ሲርበን ወይም ሲጠማን ኩርማን ዳቦና አንድ ብርጭቆ ውሃ ምን ያህል ትልቅ ግምት የምንሰጠውና የምንናፍቀው እንዲሆን ያደግርገናል። ይህም የሰው ልጅን ደካማነት፣ ባከማቸው ሃብትም ሆነ በአካሉ ሊመካ የማይገባው መሆኑን ያሳያል። ያቺን ቁራሽ ዳቦ በሌላ ጊዜ ለማግኘትና ከረሃብ ለመዳን ሌላ ምርጫ ሁሉ ዝግ ቢሆንበት ያለውን ሃብት ሁሉ ሰጥቶ ከመግዛት ውጭ ነፍሱን ለማትረፍ ምን ሊያደርግ ይችላል? ስለዚህ ፆም የሰው ልጅን ልኩን እንዲያውቅና በዚህች ዓለም ላይ ሲኖር ያለፈጣሪው መልካም ፈቃድ አንዳች ነገር ሊከውን የማይችል ገልቱ መሆኑን እንዲገነዘብ ያደርገዋል።

እንግዲህ ፆም ተቅዋ ከታከለበት ሙሉ ተቀባይነት የሚያገኝ ሲሆን በአልባጩ ከሆነ ደግሞ ዝም ብሎ መራብና መጠማት ብቻ ይሆናል ማለት ነው። የዓለማቱ ጌታ አላህ በጥበብ በታጨቀው መጽሐፉ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ١٨٣ ﴾ البقرة: ١٨٣

*"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ፆም በእነዚያ ከእናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በእናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነገገ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።" (አል-በቀራህ፡183)*

የሰው ልጅ እድሜ ልኩን የሰበሰበውን ሃብት ሌላው ቀርቶ ይህችን ዓለም እንኳ ቢሰጥና ከረሃቡ ወይም ከጥሙ ቢገላገል እንደሚመርጥ ቀጣዩ ምሳሌ ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡-

ታዋቂው የአባሲዮች ኸሊፋ ሃሩን አል-ረሺድ በዘመኑ እጅግ ጥበበኛና ታማኝ የነበረ ኢብን አል-ሰማክ የተባለ አማካሪ ነበረው፡፡ በአንድ ወቅት አብረው ተቀምጠው ሲጨዋወቱ ሃሩን አል-ረሺድ በብርጭቆ የተሞላ ውሃ መያዙን ያስተዋለው ኢብን አል-ሰማክ እንዲህ አለው፡-

“አንተ የምእመናን አዛዥ ሆይ! በጣም የተጠማህ ሆነህ እያለህ ይህን በእጅህ የያዝከውን ውሃ እንዳትጠጣ ብትከለከል ኖሮ አሁን የያዝከውን ግዛት በአንድ ብርጭቆ ውሃ ብትለውጥ አትፈቅድምን?”

በጠቢቡ ንግግርና ጥያቄ የተደነቀው ኸሊፋ “በእርግጥ በጣም ከተጠማሁና ምርጫ ከሌለኝ ግዛቴን በሙሉ በአንድ ብርጭቆ ውኃ መለወጤ የሚቀር አይመስለኝም” አለው፡፡

ጥበበኛው ኢብን አል-ሰማክም የኸሊፋውን መልስ ካዳመጠ በኋላ እንዲህ አለው፡- “መልካም! ግዛት ማለት እንግዲህ እንደምታየው የማይረባና ከአንዲት ብርጭቆ ውሃ የማይሻል ነገር መሆኑን አስተውል፡፡”

## ምጽዋት (ሰደቃ) ስንሰጥ የሚኖረን ተቅዋ

ለተቸገሩ ሰዎች ምጽዋት (ሰደቃ) ስንሰጥ ማወቅ ያለብን ትልቁ ነገር በእጃችን ያለው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት አላህ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ነው ለተቅዋ (አላህን ለመፍራት) የሚያነሳሳን ቀስቃሽ ኃይል፡፡

እርግጥ ነው የሰው ልጅ ሲባል በነፍሱ ውስጥ ንፍገት ተጽፎበታል፡፡ ያንን የንፍገት ባሕሪ ተቆጣጥሮ ከቻለም አስወግዶ ነው እንግዲህ የጀነትን መንገድ መያዝ የሚችለው፡፡ “ጥበበኛውና አስተዋዩ ጌታችን አላህ የብዙዎቻችንን የባሕሪ መወለካከፍና በሰጠን ሲሳይ ላይ የሌሎችን መብት የማንጠብቅ መሆናችንን በዝንታለም አብሪ መጽሐፉ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፡-

﴿ إِنَّ ٱلْإِنسَـٰنَ خُلِقَ هَلُوعًا ﴿١٩﴾ إِذَا مَسَّهُ ٱلشَّرُّ جَزُوعًا ﴿٢٠﴾ وَإِذَا مَسَّهُ ٱلْخَيْرُ مَنُوعًا ﴿٢١﴾ إِلَّا
ٱلْمُصَلِّينَ ﴿٢٢﴾ ٱلَّذِينَ هُمْ عَلَىٰ صَلَاتِهِمْ دَآئِمُونَ ﴿٢٣﴾ وَٱلَّذِينَ فِىٓ أَمْوَٰلِهِمْ حَقٌّ مَّعْلُومٌ ﴿٢٤﴾ ﴾
المعارج: ١٩ - ٢٤

*"ሰው ቅጠ ቢስ ሆኖ ተፈጠረ፡፡ ክፉ ነገር ባገኘው ጊዜ ብስጭተኛ፡፡ መልካምም ነገር (ድሎት) ባገኘው ጊዜ ከልካይ (ሆኖ ተፈጠረ)፡፡ ሰጋጆቹ ብቻ ሲቀሩ እነዚያ እነርሱ በስግደታቸው ላይ ዘውታሪዎች የሆኑት እነዚያም በገንዘቦቻቸው ላይ የታወቀ መብት ያለባቸው የሆኑት፡፡" (አል-መዓሪጅ፡ 19-24)*

ስለሆነም ኃያሉ አላህ ከእኛ የሚፈልገው የምንሰጣትን እያንዳንዷን ድንቡሎና እያንዳንዷንም የምናበላትን ቁራሽ የእርሱን አዛብ (እሳት) ከራሳችን ላይ ለመገፍተር በማሰብ (በመነየት) እንድንመጸውት ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَيُطْعِمُونَ ٱلطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِۦ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا ﴿٨﴾ إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ ٱللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنكُمْ جَزَآءً
وَلَا شُكُورًا ﴿٩﴾ إِنَّا نَخَافُ مِن رَّبِّنَا يَوْمًا عَبُوسًا قَمْطَرِيرًا ﴿١٠﴾ ﴾

*"ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለድሃ፣ ለየቲምም ለምርኮኛም ያበላሉ፡፡ የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው፡፡ ከእናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፍልግም፡፡ እኛ (ፊቱን) የሚያጨፈግግን ብርቱን ቀን ከጌታችን እንፈራለንና (ይላሉ)፡፡" (አድ-ደህር፡ 8-10)*

ይህም ማለት የሚሰጡትን ምጽዋት ሁሉ ወደጌታቸው መቃረቢያ በማድረግ እንጂ ከተቀባዩ ሌላን አይነት አጸፋ፣ ዋጋ ወይም ምስጋናን አይሹም፡፡ ከዚህ አልፈው የሰጡትን ምጽዋት በመጥቀስ ተቀባዮቹን የሚያስከፉትንና የሚመጻደቁትን አላህ እንደሚከተለው በማለት ይገስጻቸዋል፡-

﴿ قَوْلٌ مَّعْرُوفٌ وَمَغْفِرَةٌ خَيْرٌ مِّن صَدَقَةٍ يَتْبَعُهَآ أَذًى ۗ وَٱللَّهُ غَنِىٌّ حَلِيمٌ ﴿٢٦٣﴾ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تُبْطِلُوا۟ صَدَقَـٰتِكُم بِٱلْمَنِّ وَٱلْأَذَىٰ ﴾ البقرة: ٢٦٣ - ٢٦٤

*“መልካም ንግግርና ምኅረት ማድረግ ማስከፋት ከሚከተላት ምጽዋት በላጭ ነው:: አላህም ተብቃቂ ታጋሽ ነው:: እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እንደዚያ ገንዘቡን ለሰዎች ማሳየት ሲል እንደሚሰጠውና በአላህና በመጨረሻውም ቀን እንደማያምነው ሰው ምጽዋቶቻችሁን በመመጻደቅና በማስከፋት አታበላሹ::” (አል-በቀራህ፡ 263-264)*

የሰው ልጅ ያለውንና የሚጠበቅበትን ለድሆችና ለደካሞች በማካፈል ጽድቅን እንዳይፈልግ ሰይጣን ሁልጊዜም በመንገዱ ላይ አንፈራጥጦ በመቆም እያንሾሻሾከ በድህነት ያስፈራራዋል፡፡ ይህም በቁርአን እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

“ሰይጣን (እንዳትለግሱ) ድህነትን ያስፈራራችኋል፡፡..”

ይህንን የሰይጣንና የነፍስን ንፍገት በመርገጥ የአላህን ውዴታ በመሻት አላህ ከሰጣቸው ሲሳይ የሚለግሱ ለሆኑ ሰዎች ታላቅ ምንዳን እንደሚሰጣቸው ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَمَن يُوقَ شُحَّ نَفْسِهِۦ فَأُو۟لَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴿٩﴾ ﴾ الحشر: ٩

*“...የነፍሱንም ንፍገት የሚጥጠበቅ ሰው እነዚያ እነርሱ ምኞታቸውን አግኚዎች ናቸው::” (አል-ሐሽር፡9)*

ምጽዋት (ሰደቃ) የምንሰጠው ከመልካሙ ነገር መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህም ለእኛ ሲስሰጠን አይናችንን ጨፍነን እንጂ የማንወስደውን ነገር ለሰዎች ለመስጠት እጃችንን መዘርጋት የለብንም፡፡ ሁልጊዜም

ከመልካሙና ጥሩ ከሆነው ነገር መስጠት እንዳለብን ቁርአን እንዲህ በማለት ይናገራል፡-

﴿لَن تَنَالُواْ ٱلۡبِرَّ حَتَّىٰ تُنفِقُواْ مِمَّا تُحِبُّونَۚ وَمَا تُنفِقُواْ مِن شَيۡءٖ فَإِنَّ ٱللَّهَ بِهِۦ عَلِيمٞ ٩٢﴾

*“የምትወዱትን እስከምትለግሱ ድረስ በጐን ሥራ (ዋጋውን) አታገኙም፡፡ ከምንም ነገር ብትለግሱ አላህ ያውቀዋል፡፡” (አሊ-ዒምራን፡92)*

## ተቅዋ በሐጅ ፀሎት አፈጻጸም ላይ

የሐጅ ሥርዓተ ፀሎት ምንም እንኳን የገንዘብና አካላዊ ብቃትን የሚጠይቅ ቢሆንም አጠቃላዩን ሂደት በትክክለኛ ግንዛቤና ኢኽላስ (ፍጹማዊነት) መከወኑ ተቅዋን ይጠይቃል፡፡ የአላህን ቤት በአካል እዚያ ተገኝቶ መጐብኘት መቻል በራሱ ታላቅ የሆነ መንፈሳዊ ደረጃን የሚያጐናጽፍ መሆኑ እንዳለ ሆኖ እዚያ በመገኘት አላህ እንዳይፈጸሙ የከለከላቸውን ነገሮች መጠንቀቅና የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በፈጸሙት መልኩ ሁሉንም ሥርአት ማከናወን ለሐጅ ሥራ ተቀባይነት ማግኘት ወሳኝ ነው፡፡ ከአልባሌ ድርጊቶች፣ በተከለከሉ ክልሎች አውሬን ከማደን፣ ከባለቤት ጋር ግንኙነት ከማድረግ፣ ከሚጠሉና ከአስከፊ ባህሪያት ራስን በማቀብ ንጹህ የሆነን የሐጅ ሥርአት መፈፀም ልክ ከእናቱ ሆድ እንደወጣ አራስ ልጅ ከኃጢአት ያፀዳል ተብሎ በነቢያዊ ሐዲስ ተገልጿል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# በተቅዋ መንገድ ላይ የተደቀኑ ደንቃራዎች

## 1) ኩራት

የሰው ልጅ ወደ አላህ እንዳይቃረብ ከሚያሰናክሉት ነገሮች ምናልባትም ዋነኛው ኩራትና ለራስ ከፍ ያለ ግምት መስጠት ነው። ይህም የሚገለፀው አላህ የሰጠንን ማናቸውም ፀጋዎች፣ ለምሳሌ ሃብት፣ ንብረት፣ እውቀት፣ ችሎታ ስልጣን፣ መልክ፣ አቋምና ደምግባት ወዘተ ልክ በራሳችን ችሎታና ጥረት እንዳገኘናቸው ሁሉ የሰጠንን ፈጣሪ ረስተን ላልተገባ ጉዳይ ስናውላቸው ነው። ኩራትና የበላይነት ስሜት በመጀመሪያ የተጸነሱት በኢብሊስ (ሰይጣን) ሕሊና ውስጥ ሲሆን በኋላም ፈርኦንን በመሰሉ ቀንደኛ ተከታዮቹ አማካኝነት በሰው ልጅ ስብእና ላይ ሥጋ ለብሰው ታይተዋል።

የዓለማት አስገኝ፣ ጠባቂና አስተናባሪ የሆነው አላህ ከሁሉም በላይ የሚፀየፈውና የሚቆጣው ስልጣኑን በሚገዳደረውና የኩራት ባሕሪን በሚያንፀባርቅ ሰው ላይ ነው። እንዲህ ይላል፡-

﴿وَلَا تَمۡشِ فِي ٱلۡأَرۡضِ مَرَحًاۖ إِنَّكَ لَن تَخۡرِقَ ٱلۡأَرۡضَ وَلَن تَبۡلُغَ ٱلۡجِبَالَ طُولًا ٣٧﴾

"በምድር ላይ የተንበጣረርክ ሆነህ አትሂድ። አንተ ፈጽሞ ምድርን አትሰረጉድምና። በእርዝመትም ጋራዎችን አትደርስምና።"*(አል-ኢስራእ ፡ 37)*

﴿ وَلَا تُصَعِّرْ خَدَّكَ لِلنَّاسِ وَلَا تَمْشِ فِي ٱلْأَرْضِ مَرَحًاۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ كُلَّ مُخْتَالٖ فَخُورٖ ١٨ وَٱقْصِدْ فِي مَشْيِكَ وَٱغْضُضْ مِن صَوْتِكَۚ إِنَّ أَنكَرَ ٱلْأَصْوَٰتِ لَصَوْتُ ٱلْحَمِيرِ ١٩ ﴾ لقمان: ١٨ - ١٩

*"ጉንጭህንም (በኩራት) ከሰዎች አታዙር። በምድርም ላይ ተንጠባርረህ አትሂድ። አላህ ተንበጣራሪን ጉረኛን ሁሉ አይወድምና። በአካሄድህም መካከለኛ ሁን። ከድምጽህም ዝቅ አድርግ። ከድምጾች ሁሉ አስከፊው የአህዮች ድምጽ ነውና።" (ሉቀማን:18-19)*

ተወዳጁ ነቢይ (.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"ሸርጡን (ቀሚሱን ወይም ሱሪውን) በኩራት እያረዘመ መሬት ላይ የሚሄድን ሰው በፍርዱ ቀን አላህ ወደ እርሱ አያይም (ይቆጣበታል)።"

## 2) ስስታምነት

የሰው ልጆች ተቅዋ እንዳይኖራቸው ደንቃራ የሚሆንባቸው ሁለተኛው ነገር የስስታምነት (የስግብግብነት) ባህሪ ነው።

የሰው ልጅ የንፉግነት ባሕሪ በውስጡ እንደተቀመጠበት አላህ በአብሪ የቁርአን አንቀጾች ገልጿል። ይህን ጉዳይ በይበልጥ ቀደም ባለውና የምጽዋት (ሰደቃን) ጉዳይ በተመለከትንበት ምእራፍ ያብራራነው በመሆኑ አሁን ለምንነጋገርበት ርዕስ በቂ የሆኑ ጥቂት የቁርአን አንቀጾችን ብቻ ጠቅሰን እናልፈዋለን። ሰው ቆጣቢና ስስታም መሆኑን አላህ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُل لَّوْ أَنتُمْ تَمْلِكُونَ خَزَآئِنَ رَحْمَةِ رَبِّيٓ إِذٗا لَّأَمْسَكْتُمْ خَشْيَةَ ٱلْإِنفَاقِۚ وَكَانَ ٱلْإِنسَٰنُ قَتُورٗا ١٠٠ ﴾ الإسراء: ١٠٠

*“እናንተ የጌታዬን የችሮታ መካዘኖች ብትይዙ ኖሮ ያን ጊዜ በማውጣታችሁ ማለቋን በመፍራት በጨበጣችሁ ነበር፡፡ ሰውም በጣም ቆጣቢ ነው፡፡” (አል-ኢስራእ፡100)*

ገንዘባችንን ከእርሱ ጋር ለሚኖረን መቀራረብ እንዴት እንደምናወጣው ሲነግረንም የሚከተለውን ይላል፡-

﴿ وَلَا تَجْعَلْ يَدَكَ مَغْلُولَةً إِلَىٰ عُنُقِكَ وَلَا تَبْسُطْهَا كُلَّ الْبَسْطِ فَتَقْعُدَ مَلُومًا مَّحْسُورًا ﴿٢٩﴾ ﴾

*“እጅህንም ወደ አንገትህ የታሰረች አታድርግ (ገብጋባ አትሁን)፣ መዘርጋትንም ሁሉ አትዘርጋት (አታባክን) የተወቀስክ የተቆጨህ ትሆናለህና፡፡” (አል-ኢስራእ፡29)*

﴿ وَالَّذِينَ إِذَا أَنفَقُوا لَمْ يُسْرِفُوا وَلَمْ يَقْتُرُوا وَكَانَ بَيْنَ ذَٰلِكَ قَوَامًا ﴿٦٧﴾ ﴾

*“እነዚያም በለገሱ ጊዜ የማያባክኑት የማይቆጥቡትም ናቸው፡፡ በዚህም መካከል (ልግስናቸው) ትክክለኛ የሆነ ነው፡፡” (አል-ፉርቃን፡ 67)*

﴿ وَأَنفِقُوا مِن مَّا رَزَقْنَاكُم مِّن قَبْلِ أَن يَأْتِيَ أَحَدَكُمُ الْمَوْتُ فَيَقُولَ رَبِّ لَوْلَا أَخَّرْتَنِي إِلَىٰ أَجَلٍ قَرِيبٍ فَأَصَّدَّقَ وَأَكُن مِّنَ الصَّالِحِينَ ﴿١٠﴾ ﴾ المنافقون: ١٠

*“አንዳችሁ ሞት ሳይመጣውና ጌታዬ ሆይ እንድመፀውትና ከደጋጎቹም ሰዎች እንድሆን ጥቂት ጊዜ ብታቆየኝ ኖሮ እመኛለሁ ከማለቱ በፊት ከሰጠናችሁ ሲሳይ ለግሱ፡፡” (አል-ሙናፊቁን፡10)*

## 3. ችላ ባይነትና ሞኝነት

ይህችን ዓለምና የዚህችን ዓለም ጣፋጭ ነገሮች ብቻ በማየት ብልጭልጭ በሆነው ተፈጥሮዋ ተማርኮ ለመጪው ዓለም ከማይዘጋጅ ሰው የበለጠ ቸልተኛና ሞኝ የለም፡፡ ከዚህም የባሰ ተቅዋን የሚገድልና

የኢብሊስ ተከታይ የሚያደርግ ተግባር የለም። በቁርአን እንዲህ ዓይነት ሰዎችን አስመልክቶ የሚከተለው ተጽፏል፡-

﴿إِنَّ ٱلَّذِينَ لَا يَرۡجُونَ لِقَآءَنَا وَرَضُواْ بِٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَٱطۡمَأَنُّواْ بِهَا وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَنۡ ءَايَٰتِنَا غَٰفِلُونَ ٧﴾ يونس: ٧

*"እነዚያ መገናኘታችንን የማይፈሩ ቅርቢቱንም ሕይወት የወደዱ በእርሷም የረኩ እነዚያም እነርሱ ከአንቀጾቻችን ዘንጊዎች የሆኑ እነዚያ ይሰሩት በነበሩት ምክንያት መኖሪያቸው በእሳት ውስጥ ነው።" (ዩኑስ:7)*

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّ وَعۡدَ ٱللَّهِ حَقّٞۖ فَلَا تَغُرَّنَّكُمُ ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَاۖ وَلَا يَغُرَّنَّكُم بِٱللَّهِ ٱلۡغَرُورُ ٥﴾

*"እናንተ ሰዎች ሆይ! የአላህ ቀጠሮ እውነት ነው። የቅርቢቱም ሕይወት አታታላችሁ። አታላዩም (ሰይጣን) (በአላህ መታገሥ) አያታላችሁ።" (ፋጢር: 5)*

﴿ٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ دِينَهُمۡ لَهۡوٗا وَلَعِبٗا وَغَرَّتۡهُمُ ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَاۚ فَٱلۡيَوۡمَ نَنسَىٰهُمۡ كَمَا نَسُواْ لِقَآءَ يَوۡمِهِمۡ هَٰذَا وَمَا كَانُواْ بِـَٔايَٰتِنَا يَجۡحَدُونَ ٥١﴾ الأعراف: ٥١

*"እነዚያ ኃይማኖታቸውን መሳለቂያና መጫወቻ አድርገው የያዙ፣ የቅርቢቱም ሕይወት ያታለለቻቸው ይህንን ቀናቸውን መገናኘትን እንደረሱ በተአምራታችንም ይክዱ እንደነበሩ ዛሬ እንረሳቸዋለን (ባሉበት የእሳት ቅጣት ውስጥ እንተዋቸዋለን)።" (አል-አዕራፍ:51)*

የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) ተላላና ዝንጉ ስለሆኑ ሰዎች የሚከተለውን ብለዋል፡-

"አዋቂና ብልህ ሰው ማለት *ሥጋዊ* ፍላጎቱንና ስሜታዊ ዝንባሌውን ተቆጣጥሮ ከሞት በኋላ ላለው ሕይወቱ የሰራ ሰው ነው። ሞኝ ተላላና ደካማ ሰው ማለት ደግሞ ራሱን በስሜታዊ ዝንባሌው ቁጥጥር ስር

አውሎ የዝንባሌው ተከታይ በመሆን (ምህረትና ፀጋውን ያለአንዳች ጥረት) ከአላህ የሚጠብቅ ሰው ነው፡፡” (ቲርሚዚ)

አቡ ሰኢድ አል-ኹድሪ (ረ.ዐ.) ባስተላለፉትና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“ይህች ዓለም (ዱንያ) አረንጓዴና ጣፋጭ ናት፡፡ አላህ በዓለም ላይ ተጠሪው (ኸሊፋው) አድርጓችሁ የምትሰሩተን ያያል፡፡ በዓለማዊ መጠቀሚያ (በዱንያ) ውስጥ ተዘፍቃችሁ ከመማረክና ከሴቶች ጋር በሚኖራችሁ ግንኙነት ከሚፈጠረው እኩይ ተግባር ተጠንቀቁ፡፡ አላህን ፍሩ፡፡ የነገደ እስራኤል የመጀመሪያ መፈታተኛ ሴቶችን የሚመለከት ነበርና፡፡”

## ‘ፍቅረ ንዋይ’ በተቅዋ መንገድ ላይ የተቀመጠ ደንቃራ

ገንዘብ ጌታህ ነው ወይስ አገልጋይህ? በሚል ርዕስ በአንድ ኃይማኖታዊ ሃራጥቃ በሚዘጋጅ ብሮሸር[1] ላይ የሰፈረን ጽሑፍ ከቁርአንና ከነቢያዊ ሐዲሶች ጋር አስማምተን ዳሰሳ ብጤ ብናደርግ ወደድኩ፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) “ለብልህ ሰው እውቀት የጠፋች ኃብቱ በመሆኗ ከወደቀችበቱ ቦታ ሁሉ ያነሳታል፡፡” ብለዋልና፡፡ ከዚህም በላይ የምንገኝበት ዘመን ፍቅረ ንዋይና ስግብግብነት እጅግ የነገሰበት እንደመሆኑ ከዚህ የተቅዋ ጠንቅ እንጠነቀቅ ዘንድ ጽሑፉ መጠነኛ ግንዛቤ ያስጨብጠናል ብዬ በማመኔ ነው፡፡ እናም እንዲህ አድርጌ አጠናቅሬዋለሁ፡፡

---

[1] አዌክ ብሮሸር መጋቢት 2009

በነገው እለት ድንገት ባለፀጋ ብትሆን ምን ታደርጋለህ? ሩጫ ያልበዛበት ሕይወት በመምራት ዘና ብለህ መኖር ትጀምራለህ? አላህን እርሱ እንደሚፈልገው አድርገህ ትግገዛዋለህ? መንፈስህን ሰከን ጽሞናህንም ሰብሰብ በማድረግ ይህን አጽናፈ ዓለምና በውስጡ የያዛቸውን ነገሮች ሁሉ ያስገኘውን ፈጣሪ አላህን ታወድሰዋለህ? ምሉእ በኩልሄ በሆነው ጥበቡ የፈጠራቸውን ነገሮች በማድነቅ ታስተነትናለህ? (ተፈኩር ታደርጋለህ?) ከቤተሰብህና ከወዳጆችህ ጋር ከቀድሞው የበለጠ ጊዜ ታሳልፋለህ? የአላህን መጽሐፍ (ቁርአንን) ለማንበብና በውስጡ ያዘላቸውን ጥበባት ለመመርመር (ተደቡር ለማድረግ) ዘለግ ያለ ጊዜህን ትዋጃለህ?

አሳዛኙ ነገር ባለፀጋ ወደ መሆን የተሸጋገሩ ብዙ ሰዎች ይህን አያደርጉም። ከዚያ ይልቅ አዲሱ አኗኗራቸው ያስከተለባቸውን የክብር እዳ ጠብቀው ለማቆየትና በሰዎች ዘንድ ተራ ሞገስ ለማግኘት በመሻት ከበፊቱ የበለጠ እየተጨነቁና መከራ እየበሉ ቀሪውን ዘመናቸውን ተጨማሪ ሃብት ለማጋበስ በመሮጥ ያሳልፉታል።

﴿ زُيِّنَ لِلنَّاسِ حُبُّ ٱلشَّهَوَٰتِ مِنَ ٱلنِّسَآءِ وَٱلۡبَنِينَ وَٱلۡقَنَٰطِيرِ ٱلۡمُقَنطَرَةِ مِنَ ٱلذَّهَبِ وَٱلۡفِضَّةِ وَٱلۡخَيۡلِ ٱلۡمُسَوَّمَةِ وَٱلۡأَنۡعَٰمِ وَٱلۡحَرۡثِۗ ذَٰلِكَ مَتَٰعُ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَاۖ وَٱللَّهُ عِندَهُۥ حُسۡنُ ٱلۡمَـَٔابِ ١٤ ﴾ آل عمران: ١٤

*“ከሴቶች፣ ከወንዶች ልጆችም፣ ከወርቅና ከብር፣ ከተከማቹ ገንዘቦችም፣ ከተሰማሩ ፈረሶች፣ ከግመል ከከበትና ከፍየልም፣ ከአዝመራም የሆኑ ፍላጎቶችን መውደድ ለሰዎች ተሸለመ:: ይህ ሁሉ የቅርቢቱ ሕይወት መጠቀሚያ ነው አላህም ከእርሱ ዘንድ መልካም መመለሻ (ገነት) አለለ።” (አሊ-ዒምራን:14)*

ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነት አካሄድ የተከተሉ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ ሰዎች ፍቅረ ንዋይ በጤናቸው፣ በቤተሰባቸው፣ በሕይወታቸውና በልጆቻቸው ሥነ-ምግባር ላይ ያደረሰውን ጉዳት እየተመለከቱና የዘሩትን እያጨዱ ነው፡፡

“የአደም ልጅ አንድ ሸለቆ ሙሉ ወርቅ ቢኖረው ሌሎች ሸለቆዎች እንዲኖሩት ይሻል፡፡ አፉን የሚሞላው አፈር ብቻ ነው፡፡..” (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ)

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በመጽሐፍት፣ በመጽሔቶችና በጋዜጦች ላይ የሚወጡ ርእሶች፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችና ቪዲዮዎች ከመጠን ያለፈ ቅንጦት የሚያስከትለውን አደጋ በማስጠንቀቅ ሰዎች በምትኩ ቀለል ያለ አኗኗርን እንዲመርጡ እያበረታቱ ነው፡፡ በርካታ ምንጮች እንዳመለከቱት ቁሳዊ ነገሮችን በማሳደድ መጠመድ አእምሯዊም ሆነ አካላዊ ጤንነትህን ሊያቃውሰው እንዲሁም በስሜትህ ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡

አንድ ታዋቂ ምሁር እንዲህ ይላሉ፡- “አንድ ሰው ክድህነት ከተላቀቀ በኋላ ገቢው መጨመሩ ሊያገኘው ከሚችለው ደስታ ጋር ያለው ዝምድና በጣም ውስን ነው፡፡” ቀደም ባለ ጊዜ አንድ ጋዜጠኛ በዓለም ላይ እጅግ ሃብታም ከነበሩትና በብረታ ብረት ኢንዱስትሪ መስክ ቀደምት አምራች ከሆኑት ከአንድሩ ካርኒጌ ጋር ቃለ ምልልስ ባደረገበት ወቅት ፈጽሞ የማይረሳ ትምህርት አግኝቷል፡፡ ካርኒጌ እንዲህ ብለውት ነበር፡-

“ሰዎች በእኔ ሊቀኑብኝ አይገባም፡፡ ያካበትኩት ሃብት ምን ሊረዳኝ ይችላል? አሁንስ ስልሳ አመቴ ነው፡፡ የምበላው ምግብ እንኳ በአግባቡ አይፈጭልኝም፡፡ ወጣትነትና ጤንነትን ማግኘት ብችል በልዋጩ በሚሊዩን የሚቆጠር ገንዘብ እሰጥ ነበር፡፡”

ጋዜጠኛው ቀጥሎ እንዲህ ብሏል፡- "ሚስተር ካርጌ በድንገት ዞር ብለው ዝግ ባለ ድምጽና በቁጭት እንዲሁም ስሜታቸውን ለመግለጽ በሚያስቸግር ሁኔታ 'እንደገና መኖር ብችል ማንኛውንም ነገር በደስታ እሰጥ ነበር' አሉ፡፡"

በነዳጅ ሽያጭ በብዙ ሚሊዬን የሚቆጠር ገንዘብ ያካበተው ዲን ፖል ይህንኑ ሐሳብ በመደገፍ ከጊዜ በኋላ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡- "ገንዘብ ምናልባት ከደስታ ማጣት ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆናል እንጂ ከደስታ ጋር የግድ ግንኙነት አለው ብለን ማሰብ የለብንም፡፡"

እንግዲህ ይህን ሁኔታ ስናጤነው ሕይወት ማለት ሥራ ብቻ አይደለም ብለን ለማሰብና ለመናገር ምክንያት እናገኛለን፡፡ በአውስትራሊያ የሚኖር አንድ ሰው እንዲህ ብሏል፡- "እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ማንም ሰው ሊሞት በሚያጣጥርበት ጊዜ ምነው በሥራዬ ላይ የበለጠ ጊዜ ባሳለፍኩ ኖሮ ብሎ አይቆጭም፡፡" እርግጥ ነው ሕይወታችን የሚያረካና ትርጉም ያለው እንዲሆን ለሥራ የሚሆን ጊዜ መመደብ ያስፈልገናል፡፡ ይሁንና ለሌሎች ነገሮችም ማለትም ለመንፈሳዊ ጉዳዮች፣ ለቤተሰብ፣ ለማኅበራዊ ኑሮ ወዘተ… ጊዜ መመደብ አስፈላጊ ነው፡፡ ታዲያ በሕይወት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን እነዚህን ነገሮች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ማከናወን አይቻል ይሆን?

## የገንዘብ ሌላ ገጽታ

"ወርቅ ወደ ወርቅ ይመራል፡፡ ከዚያም ወደ እረፍት ማጣት በመጨረሻም ሙልጭ ወዳለ ድህነት፡፡" (ካህሊል ጂብራን ሊባኖሳዊ ፈላስፋና ደራሲ )

በገንዘብ ሕመም እየተሰቃየህ ነው? ከዓለም ሕዝብ መካከል አብዛኞቹ በዚህ ሕመም መሰቃየታቸውን ሪፖርቶች ያሳያሉ፡፡ ለመሆኑ ይህ ሕመም ምንድን ነው? በታላቋ ብሪታንያ የአእምሮ ጤና ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሮጀር ሄንደርሰን ስለ ገንዘብ በማሰብ የሚጨነቁ ሰዎች

የሚያጋጥማቸውን አካላዊና ሥነልቦናዊ ቀውስ ለመግለጽ በቅርቡ “የገንዘብ ሕመም” የሚለውን ስያሜ ተጠቅመዋል። ከዚህ ሕመም ምልክቶች መካከል የመተንፈስ ችግር፣ ራስ ምታት፣ ማቅለሽለሽ፣ ሽፍታ፣ የምግብ ፍላጎት ማጣት፣ በሆነው ባልሆነው መቆጣት፣ የመርረበሽ ስሜትና አፍራሽ አስተሳሰብ ይገኙበታል። ሄንደርሰን “ስለ ገንዘብ መጨነቅ ለውጥረት ዓይነተኛው መንስኤ ነው” በማለት ተናግረዋል።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሰዎች ከገንዘብ ጋር ተያይዞ ለሚመጣ ጭንቀት መዳረጋቸው ምንም አያስገርምም።

ገንዘብ ለማግኘት ብሎ ከመጠን በላይ የመስራት ልማድ ጤናማ ላልሆነ ውፍረት፣ የአልኮል ሱሰኝነት፣ ለልብ ሕመም፣ በሥራ ቦታ ለሚደረስ አደጋ፣ ለመድኃኒት ሱሰኝነት፣ ለኃይለኛ ድካም፣ ለመንፈስ ጭንቀትና በውጥረት ምክንያት ለሚመጡ ብዙ ችግሮች ሊያጋልጥ ይችላል። አንድ ዘገባ እንዳመለከተው በጃፓን በየዓመቱ 10000 የሚያህሉ ሰዎች በሥራ ብዛት ምክንያት እንደሚሞቱ የሚገመት ሲሆን ይህ አሃዝ በዚያች አገር በመኪና አደጋ ምክንያት በየዓመቱ ከሚሞቱት ሰዎች ቁጥር ጋር እኩል ነው። “ካሮሺ” ወይም “ከመጠን በላይ በመሥራት የሚከሰት ሞት” ተብሎ የሚጠራው ይህ ችግር በጃፓን ብቻ የተወሰነ አይደለም። ይህን አሳዛኝ ጉዳት የተመለከተ አንድ አስተዋይ ሰው እንዲህ ብሏል። ”የምንሰራው ለመኖር ነው እንጂ የምንኖረው ለመስራት አይደለም።”

ታዲያ ሁኔታው የመሻሻል አዝማሚያ እያሳየ ነው ማለት ይቻል የይሆን? ፈጽሞ ሁኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ ከመባባስ ውጭ የመሻሻል ምልክቶችን አያሳይም። በእንግሊዝ የምትኖር አንዲት ሴት “ሥራዬ ሃይሌን በሙሉ ስለሚያሟጥጠው ለልጆቼ የሚተርፈኝ ጉልበት በጣም ትንሽ ነው።” ስትል ተጨባጩን ሁኔታ በምሬት ተናግራለች።

በዩናይትድ ስቴትስ ጥናት ከተደረገባቸው 5 የሚሆኑና በአሥራዎቹ እድሜ ውስጥ የሚገኙ ልጆች መካከል አንዱ በዋነኛነት የሚያሳስበው ነገር ከወላጆቹ ጋር በቂ ጊዜ ማሳለፍ አለመቻሉ እንደሆነ ገልጿል፡፡ በዚያች ጉደኛ አገር የተደረገ አንድ ሌላ ጥናት እንደሚጠቁመው ደግሞ ሁለቱም ሠራተኛ የሆኑ ባልና ሚስት በቀን ውስጥ እርስ በርስ የሚነጋገሩት በአማካይ ለ12 ደቂቃ ብቻ ነው፡፡ በርካታ ግለሰቦች በሥራ ቦታ የሚያጋጥማቸው ውጥረት እየጨመረ መሄዱ ስለታከታቸው ቅድሚያ ሊሰጧቸው የሚገቡ ነገሮችን መለስ ብለው ከመረመሩ በኋላ ለውጥ ማድረግ ጀምረዋል፡፡ ሁለት ትናንሽ ልጆች ያሉት አንድ አባወራ እንዲህ ይላል፡- “እኔ ትርፍ ሰዓት የምሰራ ሲሆን ባለቤቴ ደግሞ ቅዳሜና እሁድን ጭምር ትሰራ ነበር፡፡ አንገናኝም ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በመጨረሻ ግን ሕይወታችንን ከገመገምን በኋላ የሥራ ሁኔታችንን ለውጠን አሁን በጣም ደስተኞች ነን፡፡”

ከ850 ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ ባለበት በዚህ ዓለም ውስጥ በጣም ሃብታም መሆን ችግር ሊያስከትል ይችላል ብሎ ማሰብ ይከብድ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ ዋነኛ ግባቸው ሃብታም መሆንና ገንዘብ የሚገዛቸውን ነገሮች ሁሉ ማግኘት በሚሆንበት ጊዜ ምን ሊያጋጥማቸው ይችላል? ይህ ዓይነቱ አካሄድ በልጆች ላይስ ምን ተጽእኖ ያሳድራል?

በዩናይትድ ስቴትስ ለምሳሌ አንድ ልጅ በአንድ አመት ውስጥ ብቻ በቴሌቪዥን የሚተላለፉ 40000 የንግድ ማስታወቂያዎችን እንደሚመለከት ይገመታል፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ልጆች በሱቆችና በጓደኞቻቸው ቤቶች ውስጥ የሚያዩዋቸውን የቪዲዮ ጨዋታዎች፣ ዘመናዊ የሙዚቃ ማጫወቻዎች፣ የኮምፒዩተር ፕሮግራሞችና በታዋቂ ዲዛይነሮች የተዘጋጁ ውድ የፋሽን ልብሶች እንዲገዛላቸው ለወላጆቻቸው የሚያቀርቧቸውን ጥያቄዎች ለማሰብ ሞክር፡፡ አንዳንድ ወላጆች

ልጆቻቸው የፈለጉትን ሁሉ ያሟሉላቸዋል፡፡ ለምን? ወላጆች እነርሱ ራሳቸው ልጆች ሳሉ በቅንጦት ስላላደጉ ልጆቻቸው ምንም ነገር እንደቀረባቸው ሳይሰማቸው እንዲያድጉ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ሌሎች ወላጆች ደግሞ ልጆቹ የፈለጉትን ነገር ሁሉ ለማሟላት ፈቃደኛ ካልሆኑ ልጆቻቸው እንዳይጠሏቸው ይፈራሉ፡፡ ሌሎች ወላጆችም እንዲሁ ከመጠን በላይ በሥራ ተጠምደው ከልጆቻቸው ጋር ለመሆን ባለመቻላቸው ለልጆቻቸው ብዙ ስጦታን በማዥጎድጎድ ይህን ሁኔታ ለማካካስ ይሞክራሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የሳምንቱን ቀናት ሁሉ በሥራ ተወጥረው የቆዩ ወላጆች ልጆቻቸው ለሚያቀርቡት ጥያቄ “አይሆንም” የሚል መልስ ቢሰጡ ይህን ተከትሎ የሚመጣው ንዝንዝ ስለሚታያቸው ለልጆቹ የፈለጉትን ነገር ገዝተው መገላገል እንደሚሻል ይሰማቸዋል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## ፀባያችንን በማሳመር በኩል ተቅዋ የሚጫወተው ሚና

የዓለማት ጌታ አላህ የእውነት ነቢይ የሆኑትን ሙሐመድ ኢብኑ አብዱላህን (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ ሰው ዘር በሙሉ መልእክተኛ አድርጐ ሲልክ ለቁርአንና ለሱና ተግባራዊ ማሳያነት እርሳቸውን ብቁ አድርጎ ነው:: እናም ምጡቅ የሆነን ስብእና ከሽጋ ባሕሪ ጋር አቀናጅቶ የፍጥረቱ ዓይነታ አደረጋቸው:: ከዚያም ሙሉ በሙሉ እንድንከተላቸው እንዲህ በማለት አመላከተን:-

﴿ لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُواْ ٱللَّهَ وَٱلْيَوْمَ ٱلْآخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرًا ﴿٢١﴾ ﴾ الأحزاب: ٢١

*"ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልእክተኛ መልካም መከተል አልላችሁ::" (አል-አሕዛብ :21)*

﴿ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ ﴿٤﴾ ﴾ القلم: ٤

*"አንተም በታላቅ ፀባይ ላይ ነህ::" (አል-ቀለም:4)*

﴿ وَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ إِلَّا رَحْمَةً لِّلْعَٰلَمِينَ ﴿١٠٧﴾ ﴾ الأنبياء: ١٠٧

*"(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጂ አልላክንህም::" (አል-አንቢያ:107)*

የአላህ መልዕክተኛም የእርሳቸውን ወደዚህች ዓለም የመላክ አንኳር ምስጢር እንዲህ በማለት ገልፀዋል:-

“እኔ የተላኩት መልካም ስነ ምግባራትን ለመሙላት ነው፡፡” (ኢብን ረጀብ)

በተጨማሪም እንዲህ ብለዋል፡-

“የትም ቦታ ብትሆን አላህን ፍራ፡፡ መጥፎ ሥራህን በመልካም አስከትል (ወንጀልህን) ታብስልሃለችና፡፡ ከሰዎች ጋር ያለህም ግንኙነት ግብረ-ገባዊ ይሁን፡፡” (ቲርሚዚ)

አንድ የዳእዋ ሰው እንዲህ ይለናል፡-

“ጠባይን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ ሁለቱ ዓይነት ስብእና ያላቸው ሰዎች ጉልተው ይታያሉ፡-

-የመጀመሪያዎቹ የተበላሸ ጠባይ ያላቸው ሆኖም ግን አላህን በቋሚነት የሚያመልኩና ኃይማኖታዊ ግዴታዎቻቸውን እንደምንም ብለው የሚፈጽሙ ናቸው፡፡

-ሁለተኛዎቹ ደግም መልካም ጠባይ ያላቸውና ገራገሮች ሆነው አላህን በቋሚነት ከማምለኩ ላይ ዳተኞች የሆኑ እንዲያውም ግዴታዎቻቸውን በመወጣት ላይም የሚዘናጉ ናቸው፡፡

…ታዲያ ስለነዚህ ሰዎች የምንሰጠው አስተያየት ምንድን ነው? ሁለቱም ወገኖች በኢስላም ውስጥ ፈጽሞ ቦታ የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ከአላህ ዘንድ መልካም አቀባበል እንዲኖረው የሚሻ ሰው ጥሩ ጠባይ ያለውና አላህንም በቋሚነት የሚያመልክ (ግዴታዎቹን ሁሉ የሚወጣ) መሆን ይኖርበታል፡፡”

ዳዒው የስነ ምግባር ጉዳይ እንዲህ በቀላሉ ችላ ተብሎ የሚተው ጉዳይ አለመሆኑን እንደሚከተለው ይገልጻል፡-

“አንድ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ ተደመጡ፡- “በአላህ ይሁንብኝ አላመነም! በአላህ ይሁንብኝ አላመነም! በአላህ ይሁንብኝ አላመነም!”

‘የአላህ መልእክተኛ ሆይ ማን ነው እርሱ?’ የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) “ጐረቤቱ ከእርሱ ተንኮል ነጻ ያልሆነ ሰው” በማለት መልስ ሰጡ፡፡ ለምሳሌ አንዲት ሴት ያጠበቻቸውን ገና ከውሃ የወጡ ልብሶች ጐረቤቷ ካጠበቻቸውና ከደረቁ ልብሰቿ ላይ ብታሰጣቸው ጐረቤቷን ሁኔታው ምን ያህል እንደሚያቆስላት ገመታችሁ? ይህች ሴት የሰራችውን እኩይ ድርጊት አቅልለን ለምን እንመለከተዋለን? በእርግጥ ይህን ሥራዋን መጥፎ ተግባሮችን የሚመዘግበው በግራ ትከሻዋ ላይ የተቀመጠው መልአክ ሳይመዘግበው ይቀራል ብላችሁ አታስቡ፡፡ ተውበት እስካላደረገች ድረስ፡፡ ምክንያቱም በራሷ ላይ እንዲደረግባት የማትፈልገውን ድርጊት በጐረቤቷ ላይ ፈጽማለችና?”

አንድ ጊዜ ሰዎች ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መጡና ስለ አንዲት ሴት እንዲህ በማለት ተናገሩ፡- “ይህች ሴት ሌሊት የምትሰግድ፣ አዘውትራ የምትፆምና ሰደቃም በብዛት የምትሰጥ ናት፡፡ ሆኖም ግን ጐረቤቷን አዛ ታደርጋለች፡፡” እርሳቸውም እንዲህ አሉ “እርሷ የጀሃነም ናት፡፡” እንግዲህ የሴትየዋን የመልካም ምግባር ባለቤት መሆን አስቡት! ሆኖም ግን ለጐረቤቷ መልካም ሆና ባለመገኘቷ እነሆ የጀሃነም ሲሳይ መሆኗን በክቡሩ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) አፍ እየሰማን ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ስለ ሌላ ሴት ተጠየቁ፡፡ ይህች ሴት በሶላቷ በፆሟ እስከዚህም የሆነችና አነስተኛ ሰደቃ ስለምትሰጥ ሆኖም ግን ለጐረቤቶቿ ጥሩ የሆነች ናት፡፡ ነቢዩ፡- “እርሷ የጀነት ናት፡፡” በማለት ብስራት ተናገሩ፡፡

ጥበበኛ የሆነው አላህ እንዲህ በማለት ሰይጣን ፀባያችንን እንዳያበላሽብን ይመክረናል፡-

﴿ وَإِمَّا يَنزَغَنَّكَ مِنَ ٱلشَّيۡطَٰنِ نَزۡغٞ فَٱسۡتَعِذۡ بِٱللَّهِۖ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ٣٦ ﴾

*"ከሰይጣንም ጉትጎታ ቢያገኝህና (ከመልካም ጠባይም ቢመልስህ) በአላህ ተጠበቅ፡፡ እነሆ እርሱ ሰሚው አዋቂው ነውና፡፡" (አስ-ሰጅዳህ፡36)*

ከላይ የተወሱት ዳዒ እንዲህ ይላሉ፡-

"ልጁ በሌሊት ተነስቶና ጐረቤቶቻቸው ሳያዩዋቸው ቆሻሻ በጉዳናዎች ላይ እንዲጥል ስለምትጠይቀው እናትስ ምን እንበል? ይህች ሴትኮ ምናልባትም የፈጅርን (ሱብሂ) ሶላት ሰግዳ ይሆናል፤ እንዲሁም ሂጃቧንም አሳምራና አስተካክላ ትለብስ ይሆናል? ሰዎች ሆይ! እምነትንና መልካም ምግባርን እያለያየን የምንጓዘው እስከመቼ ነው?

የአላህ መልእክተኛ "በጀነት ውስጥ ከእኔ ጋር የሚጐራበቱት ጥሩ ጠባይ ያላቸው ናቸው፡፡" በማለት ተናግረዋል፡፡ (አህመድ)

# ተቅዋ በኢእሣር ላይ ሲንፀባረቅ

አል-ኢእሳር ብለን የምንጠራው የአረብኛ ቃል ከራስ ይልቅ የሌሎች ሰዎችን ጥቅምና ደስታ ማስቀደም የሚል ትርጓሜን ይዟል፡፡ እርግጥ ነው ይህ ዓይነት ምርጥ ባሕሪ ዛሬ ዛሬ ከሙስሊሙ ኡማ (ማኅበረሰብ) ስብእና ውስጥ እንደማይገኝ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ሰናይ ባሕሪ በሶሃባ ትውልድና ከዚያም በኋላ በተከታታይ በመጡት የኢስላም ትውልዶች ዘንድ እጅግ ሰፊ ግምትና ትልቅም ቦታ የሚሰጠው ነበር፡፡ ኃያሉ አላህ የመካ ሙሃጅሮች (ስደተኞች) ወደ ሃገራቸው መዲና ሲሄዱ መዲናውያን (አንሷሮች) በእንዴት ዓይነት ሞቅ ያለ ወንድማዊ አቀባበል ተቀብለው፣ ያላቸውንም ከራሳቸው በማስበለጥ ሲሰጧቸው በልባቸው ላይ ቅሬታ እንኳን እንዳልታየባቸው እያወደሰ መዲናውያንን በቁርአን ሲገልጻቸው እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ تَبَوَّءُو ٱلدَّارَ وَٱلۡإِيمَٰنَ مِن قَبۡلِهِمۡ يُحِبُّونَ مَنۡ هَاجَرَ إِلَيۡهِمۡ وَلَا يَجِدُونَ فِي صُدُورِهِمۡ
حَاجَةٗ مِّمَّآ أُوتُواْ وَيُؤۡثِرُونَ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمۡ وَلَوۡ كَانَ بِهِمۡ خَصَاصَةٞۚ وَمَن يُوقَ شُحَّ نَفۡسِهِۦ
فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ٩ ﴾ الحشر: ٩

*“እነዚያም ከበፊታቸው አገሪቱን መኖሪያ ያደረጉት እምነትንም የለመዱት ወደነርሱ የተሰደዱትን ሰዎች ይወዳሉ። (ስደተኞቹ) ከተሰጡትም ነገር በልቦቻቸው ውስጥ ቅሬታን አያገኙም። በእነርሱ ላይ ችግር ቢኖርባቸውም በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ይመርጣሉ። የነፍሱንም ንፍገት የሚጥጠበቅ ሰው እነዚያ እነርሱ ምኞታቸውን አግኚዎች ናቸው።” (አል-ሐሽር፡9)*

የሚከተለው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ታዋቂ ሐዲስ የአል-ኢእሳርን እውነተኛ ትርጉም ያሳየናል፡፡

“አንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ነገር ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አላመነም፡፡”

በስደት ወደ መዲና የሄዱትን ሰዎች (ሙሃጅሮች) ከአገሬው ነዋሪዎች (አንሷሮች) ጋር በወንድማማችነት ያስተሳሰሩት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሁለቱን ክፍሎች በመለኮታዊ የፍቅር ገመድ አስተሳስረዋቸው ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ አባባል በአብነት ሊጠቀስ የሚችለው ከአብዱረህማን ኢብኑ አውፍ (ረ.ዐ.) ጋር በወንድማማችነት የተሳሰረው ሰዒድ ኢብን ረቢዕ (ረ.ዐ.) ሲሆን ወንድሙን አብዱራሕማንን (ረ.ዐ.) እንዲህ አለው፡-

“በመዲና ውስጥ እኔን በሃብት የሚፎካከረኝ ሰው የለም፡፡ ሁለት ምርጥ የሆኑ የአትክልት ማሳዎች አሉኝ፡፡ አንዱን መርጠህ ውሰድ፡፡ እንዲሁም ሁለት ሚስቶችም አሉኝ፤ ደስ ያለችህን ምረጥና ፈትቼ አጋባሃለሁ፡፡” ይሁን እንጂ አብዱራሕማን (ረ.ዐ.) በሰዒድ አባባል ልቡ እጅጉን ቢነካም

ግብዣውን ባለመቀበል እንዲህ አለው፡- “አላህ በገንዘብህ ላይ በረካ ያውርድበት፡፡ እኔ አሁን የምፈልገው የገበያውን ቦታ ብቻ እንድታሳየኝ ነው፡፡”

የሚከተለውን አስገራሚ ታሪክ ስንቃኝ አል-ኢእሳር (ከራስ ይልቅ የሌሎችን ጥቅምና ደስታ ማስቀደም) ምን ትርጉም እንዳለው በሚገባ እንገነዘባለን፡፡ ከላይ ያወሳናቸው እንዲህ ይላሉ፡-

“አብደላህ ኢብኑ ዑመር (ረ.ዐ.) በአጋጣሚ ዓሣ በስጦታ መጥቶለት ነበር፡፡ ዓሣ መመገብ እንደሚወድ የምታውቀው ባለቤቱ ያንን ዓሣ በጥሩ ሁኔታ ጠብሳ አቀረበችለት፡፡ እርሱም ሊመገብ በተዘጋጀበት ቅጽበት በሩ ተንኳኩቶ አንድ ድሃ ሰው ምግብ እንዲሰጡት ጠየቀ፡፡ በዚህ ጊዜ አብደላህ (ረ.ዐ.) ባለቤቱ ዓሣውን ለለማኙ እንድትሰጠው አዘዛት፡፡ ባለቤቱ ደግሞ “የገበስ ዳቦና ሥጋ አለ፤ እርሱን እሰጠዋለሁ” አለች፡፡ አብደላህ (ረ.ዐ.) ግን እንዲህ አለ፡-

﴿لَن تَنَالُوا۟ ٱلْبِرَّ حَتَّىٰ تُنفِقُوا۟ مِمَّا تُحِبُّونَ ۚ وَمَا تُنفِقُوا۟ مِن شَىْءٍ فَإِنَّ ٱللَّهَ بِهِۦ عَلِيمٌ ﴿٩٢﴾﴾

*“የምትወዱትን እስከምትለግሱ ድረስ በጐን ሥራ (ዋጋውን አታገኙም) ከምንም ነገር ብትለግሱ አላህ ያውቀዋል፡፡” (አሊ-ዒምራን፡ 92)*

“ስለሆነም ዓሣውን ስጪው“ አላት፡፡ ባለቤቱ ምርጫ ስላልነበራት ዓሣውን ለለማኙ ሰው ለመስጠት በእጅዋ ይዛ እንዲህ አለችው “ይህን ዓሣ በአንድ ድርሃም አትሸጥልኝምን?” ሰውየው በዚህ ሃሳብ ስለተስማማ ድርሃሙን ተቀብሎ ሄደ፡፡ ባለቤቱም ዓሣውን ወደ አብደላህ ይዛ በመመለስ አቀረበችለት፡፡ ኢብን ኡመርም (ረ.ዐ.) በባለቤቱ ድርጊት እየተደነቀ ለመመገብ በተዘጋጀበት ሰዓት አሁንም ያው ለማኝ ሰው ተመልሶ በመምጣት በሩን ካንኳኳ በኋላ ምግብ እንዲሰጡት ጠየቀ፡፡ ኢብን ኡመርም “ዓሣውን ስጭው” በማለት ባለቤቱን አዘዛት፡፡ ባለቤቱም

“አንድ ጊዜ ሰጥቼው የለም እንዴ” በማለት ተናገረች፡፡ “አላህ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ብዙ ጊዜ ሰደቃ እንድንሰጥ አላህ አዞናል” አላት፡፡ ባለቤቱ አሁንም ዓሣውን ይዛ በመሄድ ለሰውየው ሳትሰጠው በፊት በሌላ አንድ ዲርሃም እንዲሸጥላት ተደራደረች፡፡ ሰውየውም ተስማማ፡፡ ከዚያም እንዲህ አለች “እባክህ ከዚህ በኋላ ተመልሰህ አትምጣ!”

## ተቅዋ በአል - ኢህሳን (በማሳመር) ሲገለጽ

አል-ኢህሳን (ማሳመር) የምንለው ነገር ቀጥተኛ ትርጓሜው ስህተት አልባ መሆን፣ አስተካክሎ መከወን፣ በተቻለ አቅም ወደ ፍጹምነት መጠጋት ማለት ነው፡፡ ይህ አል-ኢህሳን (ማሳመር) የኢስላማዊ ስነምግባር ዋና መገለጫ ነው፡፡ የምንሰራው ሥራ፣ አምልኮታችን፣ ንግግራችንና ባህሪያችን ሁሉ በአል-ኢህሳን ስር የሚታቀፉ እንደመሆናቸው አላህን ልንፈራ (ተቅዋ) ሊኖረን ይገባል፡፡ ቁርአን ስለ አል-ኢህሳን (ማሳመር) ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ يَأۡمُرُ بِٱلۡعَدۡلِ وَٱلۡإِحۡسَٰنِ وَإِيتَآيِٕ ذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَيَنۡهَىٰ عَنِ ٱلۡفَحۡشَآءِ وَٱلۡمُنكَرِ وَٱلۡبَغۡيِۚ يَعِظُكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ٩٠ ﴾ النحل: ٩٠

*“አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዝዛል፡፡ ከአስከፊም (ከማመንዘር) ከሚጠላም ነገር ሁሉ ከመበደልም ይከለክላል፡፡ ትገነዘቡ ዘንድ ይገስጻችኋል፡፡” (አን-ነሕል፡ 90)*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡- “ስራቸውን አጠንክረውና አስተካክለው የሚሰሩ ሰዎችን አላህ ይወዳል፡፡” (ጠበራኒ፣ሃይሰሚ)

በሌላ ሐዲስ ደግሞ እንዲህ ማለታቸው ተጠቅሷል፡-

“የአላህን ውዴታ ለማግኘት አትጓጉምን? እንደዚያ ከሆነ ሥራችሁን አሳምሩ፡፡ ሥራን ለማሳመር (ለማስተካከል) ብዙ በደከማችሁ ቁጥር አላህም እየወደዳችሁ ይመጣል፡፡”

አቡ ያእላ ሸዳድ ኢብን አውስ (ረ.ዐ.) እንዳወሩት የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አላህ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ጥራትን ደንግጓል፡፡ ስትገድሉ አገዳደላችሁን አሳምሩ፡፡ ስታርዱም አስተራረዳችሁን አሳምሩ፡፡ ከናንተ አንዳችሁ ቢላውን በደንብ ይሳል፡፡ የሚታረደውን እንስሳም ከስቃይ (ያሳርፈው)” (ሙስሊም)

# ምዕራፍ ሰባት

# ባለን ነገር ከመርካት (ሪዷ) አንፃር ተቅዋ የሚኖረው ሚና

የሰዎችን ሁኔታና በዙሪያቸው ያሉ ክስተቶችን በአራት ክፍል ልናያቸው እንችላለን፡-

## 1. ውስጣቸውም ውጪአቸውም መልካም የሆኑ ሰዎች

አንድ ሰው በኢስላም ሸሪዓ የተፈቀደ (ሃላል) በሆነ መንገድ ገንዘብ እያገኘ ያንኑም አላህ በፈቀደው ነገር ላይ ብቻ በማዋል በየጊዜው ሰደቃ (ምጽዋት) የሚሰጥ፣ የሰው ልጆች ሕይወት የተሻለና መልካም ይሆኑ ዘንድ የሚያግዝ፣ የአካባቢውን፣ የእንስሳቱን ሁሉ ሃቅ የሚጠብቅ ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው የሚሰራውን ማንኛውም መልካም ሥራ የአላህን ውዴታ ለማግኛ ሰበብ አድርጐ ይንቀሳቀሳል፡፡ የዚህ ሰው ውስጡም ሆነ ውጩ ያማረ ነው፡፡

## 2. ውስጣቸውም ሆነ ውጪያቸው የተበላሹ ሰዎች

እንዲህ ዓይነት ሰው ሁልጊዜም ሃሳቡና ፍላጐቱ ወደ ጥምመትና አዘቅት የምትጐትተውን ነፍሱን መከተል ሲሆን በዚህ ዓለም ወራዳ የሆነ ሕይወትን ይመራል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው ደስተኛ ሕይወት አገኛለሁ እያለ ራሱን በማታለል ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ሰው በዚህች በቅርቢቱም ሆነ በመጪው ዓለም ውርደትና ሃዘን እንጂ ሌላ ምንም አይገጥመውም፡፡

## 3. ላይ ላዩን ሲታዩ መልካም የሚመስሉ ሆኖም ግን ውስጣቸው መጥፎ የሆኑ ክስተቶች

አንዳንድ ጊዜ ከውጭ ወይም የላይ ገጽታቸውን ስንመለከተው ጥሩና መልካም የሚመስሉ የኋላ ኋላ ግን የሚያመጡት መዘዝ መጥፎ የሆኑ ክስተቶች ያጋጥማሉ። ለምሳሌ ከግዴለሽነት ጋር የተቆራኘ ሃብት ነፍስን ለጥመት በመዳረግ የሚስተካከለው የለም። ስለዚህ ፈጣሪያችን ሃብትንም ሆነ ማንኛውንም ፀጋ እንዲሰጠን ስንጠይቅ ለእኛ የሚበጀን እንዲያደርግልንም መለመን አለብን። ለነገሩ አላህ የሁላችንንም ሁኔታ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ማንኛውንም ፀጋ ሲለግሰን ለክቶ ነው። እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَوْ بَسَطَ ٱللَّهُ ٱلرِّزْقَ لِعِبَادِهِۦ لَبَغَوْا۟ فِى ٱلْأَرْضِ وَلَـٰكِن يُنَزِّلُ بِقَدَرٍ مَّا يَشَآءُ ۚ إِنَّهُۥ بِعِبَادِهِۦ خَبِيرٌۢ بَصِيرٌ ﴿٢٧﴾ ﴾ الشورى: ٢٧

*"አላህም ለባሮቹ (ሁሉ) ሲሳይን በዘረጋ ኖሮ በምድር ውስጥ (ሁሉም) ወሰን ባለፉ ነበር። ግን የሚሻውን በልክ ያወርዳል። እርሱ በባሮቹ (ሁኔታ) ውስጥ አዋቂ ተመልካች ነውና።" (አሽ-ሹራ፡ 27)*

በተጨማሪም አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَعَسَىٰٓ أَن تَكْرَهُوا۟ شَيْـًٔا وَهُوَ خَيْرٌ لَّكُمْ ۖ وَعَسَىٰٓ أَن تُحِبُّوا۟ شَيْـًٔا وَهُوَ شَرٌّ لَّكُمْ ۗ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ وَأَنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ ﴿٢١٦﴾ ﴾ البقرة: ٢١٦

***አንድ ነገር ጠልታችሁት ያ ነገር ለናንተ መልካም የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። አንድን ነገር ደግሞ ወዳችሁት ያ ነገር ለናንተ መጥፎ የሚሆንበት አጋጣሚ ይከሰታል። አላህ (የነገሮችን ፍጻሜ፣ በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም የሚበጃችሁንና የሚጠቅማችሁን) ጠንቅቆ ያውቃል። እናንተ ግን አታውቁም። (አል-በቀራህ፡ 216)***

### 4. ላይ ላዩን ሲታዩ መጥፎ የሚመስሉ ነገር ግን ውስጣቸው መልካም የሆኑ ነገሮች፡-

እንበልና አንድ ሰው በሕመም ምክንያት ጤናው ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ ይሄደል፡፡ ይህ ለእርሱም ሆነ ውጫዊውን ሁኔታ ለሚመለከት ማንም ሰው ጥሩ ያልሆነ ስሜት ማሳደሩ አይቀርም፡፡ ሆኖም ግን ባለቤቱ ጉዳዩን መለኮታዊ በሆነ መነጽር ቢያስተውለው ይህ በሽታ ደካማ መሆኑን፣ በቀላሉ እንደሚሰበር፣ እንዲሁም የዓለማት ጌታ አላህ ጤና አሳጥቶ አንድ የማስተዋል መስኮት እየከፈፈለት መሆኑን ይገነዘባል፡፡ በእውነቱ ይህ ለሰውየው መልካም ነገር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

አብደላህ ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡- “ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘንድ ስሄድ በሃይለኛ ትኩሳት ተይዘው አየሁ፡፡ ከዚያም እንዲህ አልኳቸው “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የያዝዎት ትኩሳት ኃይለኛ ይመስላል፡፡” ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት መለሱልኝ፡፡ “አዎን! የሁለት ሰዎችን ህመም ያክል ታምሜያለሁ፡፡” እኔም “እንደዛ ከሆነ ምናልባትም የሁለት ሰዎችን ያክል ምንዳ (አጅር) ያገኛሉ ማለት ነው?” ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡- “አንድን ሙስሊም አንዳች መከራ አይገጥመውም፣ ከሃጢአቱ የተወሰነው የሚሰረይለት ቢሆን እንጂ፡፡ ሌላው ቀርቶ እሾህ ቢወጋው እንኳ” (ቡኻሪ)

እንግዲህ ተቅዋን በልባችን በመሰነቅ አላህ የሰጠንን ፀጋዎች እያመሰገነን ተበቃቅተን ለመኖር እንችላለን፡፡ ይህም የአላህን ውዴታ ያስገኝልናል፡፡

## ተውበት አድርጐ ወደ አላህ ለመመለስ የተቅዋ አስፈላጊነት

ተውበት ተቀባይነት እንዲያገኝ ልባዊ (እውነተኛ) የሆነ ፀፀትና ኃጢአትን ማቆም ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ስለዚህ የተቅዋ ፍሬ ነገር ይህን ፀፀትና ንስሃ (ተውባ) ሲያደርጉ በኃጢአት ታውሮና ደንቁሮ የነበረው የልባቸው ብርሃንና የህሊናቸው ድምፀት ይስተካከላል፡፡ ነፍሳቸው ከእዝነ ልቦናቸው በሚወጣው የምህረት ፍለጋ ዋይታ ወደጌታዋ ትቃረብ ዘንድ

እነሆ መንገድ ታገኛለች፡፡ ዓይኖች በእንባ ጭጋግ ይጋረዳሉ፡፡ እጆችም ወደሰማይ ይዘረጋሉ፡፡ ይህ ነው እንግደህ ለተቅዋ መንገድን የሚያበጅ የሆነ እውነተኛ ተውበት (ንስሃ) የሚባለው፡፡

ጥበበኛውና የእውቀት ሁሉ ባለቤቱ አላህ የባሮቹን ሁኔታ በጥልቀት ስለሚገነዘብ ማንኛውንም ኃጢአት (ሽርክንም ቢሆን) የፈፀሙ ሰዎች ከእዝነቱ ተስፋ ቆርጠው በዚያው ከእዝነቱ እንዳይኮበልሉ እንዲህ እያለ ይጋብዛል፡-

﴿ قُلْ يَـٰعِبَادِىَ ٱلَّذِينَ أَسْرَفُوا۟ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ لَا تَقْنَطُوا۟ مِن رَّحْمَةِ ٱللَّهِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَغْفِرُ ٱلذُّنُوبَ جَمِيعًا ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٥٣﴾ ﴾ الزمر: ٥٣

*“በላቸው -እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ አላህ ኃጢአቶችን በመላ ይምራልና፡፡ እነሆ እርሱ መሃሪው አዛኙ ነውና፡፡” (አዝ-ዙመር፡53)*

ስለሆነም መፀፀት፣ ተውበት ማድረግና ወደ መልካም ሥራ መመለስ በባሪያውና በጌታው መካከል ተፈጥሮ የነበረውን መንፈሳዊ ዳፍንት ይገፍፋል፡፡ የሻከረውን ግንኙነት ያለሰልሳል፣ የአላህን ቁጣ ያበርዳል፡፡ ይህ ማለት ተቅዋ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡

ዓሊ ኢብን አቡ ጧሊብ (ረ.ዐ.) ለአንዱ ሃገረ ገዥ የሚከተለውን ምክር ለግሰውታል፡-

“ሰዎችን፣ ራቅ ብሎ መንጋውን በጉምዥታ እንደሚያማትር ተኩላ ብጤ አትመልከት! ለእነርሱ ፍቅርና አሳቢነት ይኑርህ፡፡ እንዲሁም ከልብህ ደግነትን አሳያቸው፡፡ ይህን ስታደርግም አንድም የእምነት ወንድሞችህ መሆናቸውን አለያም ደግሞ የሰው ልጅ መሆናቸውን ብቻ ታሳቢ አድርገህ ነው፡፡ ሰዎች በየጊዜው ስህተት ላይ ሊወድቁ ይችላሉ፡፡ እርዳታ

ለሚያሻቸው ምንዱባን የእርዳታ እጅህን ዘርጋላቸው፤ እንዲሁም ከአላህ ምህረትን ለምንላቸው፡፡ ሁሌም ቢሆን ይቅርታህ አይለያቸው፣ በማንኛውም ሁኔታቸው ሆደ ሰፊነትን አሳይ፡፡ የአላህን ትእዛዝ በሚመለከት ቸልተኛ አትሁን፡፡ እንዲሁም ፊጽሞ አትገዳደር፡ ይቅርታህን ከሰጠህ በኋላ ቃልህን አታፍርስ፡፡ ባጠፉት ጥፋትም ቢሆን ሰዎችን በመቅጣት አትደሰት፡፡

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች አንዱ የሆነው አቡ ደርዳእ (ረ.ዐ.) በደማስቆ ዳኛ ሆኖ በነበረበት ጊዜ ሰዎች አንድ ሃጢአት የፈፀመን ሰው ከብበው ሲጮሁበትና ሲሰድቡት አስተዋለ፡፡ ከዚያም አቡ ደርዳእ (ረ.ዐ.) ሰዎቹን እንዲህ አላቸው፡- "ሰዎች ሆይ! አንድ ሰው ጉድጓድ ውስጥ ወድቆ ብታዩ ምን ታደርጋላችሁ?" ሰዎቹም እንዲህ አሉ፡- "ገመድ እንልክለትና ከጉድጓዱ ውስጥ ልናወጣው እንሞክራለን፡፡" አቡደርዳእ (ረ.ዐ.) በዚህ ጊዜ እንዲህ አለ፡- "ታዲያ ይህን በኃጢአት ጉድጓድ የወደቀ ወንድማችሁን ከዚያ ሁኔታ ልታወጡት ለምን አትሞክሩም?" ሰዎቹም፡- ‹‹በዚህ ኃጢአትኛ ሰው ላይ አልተናደድክምን?" አሏቸው፡፡ አቡ ደርዳእ በዚህ ጊዜ ታላቅ ጥበብ የተንፀባረቀበትን መልስ እንዲህ በማለት ሰጧቸው፡- "እኔ ሰውየውን ሳይሆን ሃጢአቱን ነው የምጠላው፡፡"

﴿ وَإِنِّي لَغَفَّارٌ لِّمَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ صَٰلِحًا ثُمَّ ٱهْتَدَىٰ ﴿٨٢﴾ ﴾ طه: ٨٢

*"እኔም ለተፀፀተ ላመነም መልካምን ለሰራ ከዚያም ለተመራ ሰው በእርግጥ መሃሪ ነኝ፡፡" (ጦሃ፡82)*

## በበጎ ነገር ለማዘዝና ከእኩይ ድርጊትም ለመከልከል የተቅዋ አስፈላጊነት

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ ...وَٱدۡعُ إِلَىٰ رَبِّكَۖ ... ﴾ القصص: ٨٧

*"...ወደ ጌታህም (ሰዎችን) ጥራ ..." (አልቀሶስ:86)*

﴿ ٱدۡعُ إِلَىٰ سَبِيلِ رَبِّكَ بِٱلۡحِكۡمَةِ وَٱلۡمَوۡعِظَةِ ٱلۡحَسَنَةِۖ ﴾ النحل: ١٢٥

*"ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ (በለዘብታ ቃል) ጥራ:: " (አን-ነሕል:125)*

﴿ وَلۡتَكُن مِّنكُمۡ أُمَّةٞ يَدۡعُونَ إِلَى ٱلۡخَيۡرِ وَيَأۡمُرُونَ بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَيَنۡهَوۡنَ عَنِ ٱلۡمُنكَرِۚ ﴾

*"ከእናንተም ወደ በጎ ነገር የሚጠሩ፣ በመልካም ሥራም የሚያዝዙ ከክፉም ነገርም የሚከለክሉ ሕዝቦች ይኑሩ::" (አሊ-ዒምራን: 104)*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል:-

"ሌላውን ሰው ወደ በጎ ነገር ያመላከተና የመራው ሰው ከፈጻሚው ጋር ተመሳሳይ የሆነ ምንዳ ያገኛል::" (ሙስሊም)

ከአቡ ሁረይራ በተላለፈው መሰረት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) "ወደ ቅንና እውነተኛ መንገድ ጥሪ ያደረገ ሰው (ጥሪውን ሰምተው መንገዱን) የተከተሉ ሰዎችን ምንዳ ብጤ ከእነርሱ ምንዳ ላይ ምንም ሳይቀነስባቸው ያገኛል::" (ሙስሊም)

ሰዎች መልካም ነገሮችን እንዲፈጽሙና በዚያው ላይ እንዲበረቱ ማድረግ እንዲሁም ከክፉና ሰይጣናዊ ድርጊቶች ይርቁ ዘንድ መምከር የአንድ ሙስሊምና አማኝ ሰው ዋነኛ ባሕሪ ነው:: ቅን የሆኑ የአላህ ወዳጆች ይህንን ጉዳይ ይበልጥ ባማረና ጨዋነትን በተላበሰ አቀራረብ ነው የሚያከናውኑት:: ይህንንም የሚያደርጉ ከንግግራቸው በላይ

በተግባራዊ እንቅስቃሴዎቻቸው ነው ሰውን የሚስቡት፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)

"እነዚያ የአላህ ትክክለኛ ወዳጆች ስታያቸው መጪውን ዓለም (አኺራን) የሚያስታውሱ ናቸው።" ብለዋልና፡፡

ስለሆነም በመልካም ማዘዝንና ከእኩይ ድርጊቶች መከልከልን ቀላል ጉዳይ አድርገን መውሰድ የለብንም፡፡ ይልቁንም ይህ ጉዳይ ከሁሉም ቀደምት ሕዝቦች ይበልጥ የተመረጥንበትና አላህም ለየት ያለ ማእረግ እንዲኖረን አድርጐ ያጐናፀፈን ፀጋ ነው፡፡ እንዲህ ይላል፡-

﴿ كُنتُمۡ خَيۡرَ أُمَّةٍ أُخۡرِجَتۡ لِلنَّاسِ تَأۡمُرُونَ بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَتَنۡهَوۡنَ عَنِ ٱلۡمُنكَرِ وَتُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِۗ ﴾ آل عمران: ١١٠

*"ለሰዎች ከተገለፀች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ሆናችሁ፡፡ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ፡፡ ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ፤ በአላህም አንድነት ታምናላችሁ፡፡" (አሊ-ዒምራን፡110)*

የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) እያንዳንዱ ሰው በነፍስ ወከፍ በየጊዜውና በየአንዳንዱ እንቅስቃሴው ያለበትን ኃላፊነት እንዲህ በማለት ጠቁመዋል፡-

"ሕገ ወጥ (ሐራም) ነገር ሲፈፀም የተመለከተ በእጁ ይቀይረው፡፡ ይህን ማድረግ ካልቻለ በምላሱ ይናገር፣ ይህንንም ካልቻለ በልቡ (ጉዳዩን) ይጥላ፡፡ ይህ ግን የመጨረሻው ደካማ የእምነት ደረጃ ነው፡፡"

ዘይነብ ቢንት ጃህሽ (ረ.ዐ.) የተባለችው ባለቤታቸው የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ጊዜ እንዲህ በማለት ጠየቀቻቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በእኛ መካከል አማኞች እያሉ እንጠፋለን?” እርሳቸውም እንዲህ አሏት፡- “ኃጢአትና ፀያፍ ምግባራት ከተንሰራፉ አዎን!” (ቡኻሪ)

ስለዚህ ከመለኮታዊው ቀጣና ጥፋት ማምለጫው ብቸኛ መንገድ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ውስጥ በመልካም ነገር የሚያዝዙ ከሚጥጠላ (ፀያፍ) ነገሮች ደግሞ የሚከለክሉ ሰዎች መኖር ነው፡፡ ይህንን ስናደርግም ከቁርአንና ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሱና ብቻ መመሪያ በመውሰድ አለብን፡፡ እንዲሁም በየዘመናቱና በየአካባቢው የሚወጡ ብቃት ያላቸውን የእውቀት ባለቤቶች (ኡለማእ) ማማከርና ኢጅቲሃድ (ምሁራዊ ጥረትና ምርምር) እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይገባል፡፡

## ታማኝ ለመሆንም ተቅዋ ያስፈልጋል

ታማኝነት የሚለውን ቃል የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሰፋ ያለ ትርጓሜን በመስጠት ላቅ ያሉ መንፈሳዊ፣ ስጋዊና ሞራላዊ እሴቶችን በውስጡ እንዳካተተ እንዲህ በማለት ገልፀውታል፡፡

“ኃይማኖተኝነት ታማኝነት (ነሲሃ) ነው” አሉ፡፡ እኛም “ለማን? የአላህ መልእክተኛ ሆይ!” አልናቸው፡፡ እርሳቸውም “ለአላህና ለመጽሐፉ፣ ለመልእክተኛው፣ ለሙስሊም መሪዎችና ለሕዝበ ሙስሊሙ (ኡማው) ነው” አሉን፡፡ (ሙስሊም)

የታላቁን መምህር የነቢዩ ሙሐመድ ኢብን አብዱላህን (ሰ.ዐ.ወ.) ሕይወት እንዳለ ስንቃኘው በታማኝነት ላይ የተሞላ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመጀመሪያ ለጌታቸውና ለፈጣሪያቸው ለአላህ ፍጹም ታማኝና ጽኑ አገልጋይና ባሪያው ነበሩ፡፡ እንዲሁም ላወረዳቸው ሕግጋትና ለቁርአኑ ፍጹም ታማኝ ነበሩ፡፡ ከዚያም ለምእመናንና ለመላው ሙስሊም ማኅበረሰብ፣ ለቤተሰባቸው፣ ለትዳር አጋሮቻቸው፣ ለዘማዶቻቸው ሁሉ የታማኝነት ተምሳሌት የነበሩ ለመሆናቸው ሣር ቅጠሉ

ይመሰክርላቸዋል፡፡ “ሙሐመዱል አሚን” (ታማኙ ሙሐመድ) እያሉ ይጠሯቸው የነበሩ መሆኑን ብቻ መጥቀሱ በቂ ነው፡፡

የምእመናን እናት አዒሻ (ረ.ዐ.) እንዲህ ትላለች፡- “መካ በተከፈተበት ጊዜ አንዲት አሮጊት ሴት ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እየተራመደች ቀረበች፡፡ እርሳቸውም ማንነቷን ሲጠይቋት እርሷም “የሙዛኑዋ ጀስማህ ነኝ” በማለት ራሷን አስተዋወቀች፡፡ (ይህ ስም በቀጥታ ግዙፏ የሚል ትርጓሜን ስለሚይዝ) ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ስሟን ቀይረው “አይሆንም ከዚህ በኋላ የሙዛኑዋ ሃስናህ (ውቧ የሚል ትርጓሜን የያዘ ስም ነው) ነው መባል ያለብሽ” አሉ፡፡ ከዚያም ለመጨረሻ ጊዜ ከተያዩ በኋላ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሳለፈች እየጠየቋት ለረዥም ጊዜ ቆዩ፡፡ እርሷም …‹‹እኔም ሆንኩ መላው ቤተሰቤ ደህና ነን፡፡ እናቴና አባቴ መስዋእት ይሁኑልዎትና!” በማለት መለሰች፡፡ ሴትዮዋ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ተሰናብታ እንደሄደች አዒሻ (ረ.ዐ.) ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት ጠየቀቻቸው፡-

“ይህን ያክል ክብር የቸሯትና ለረዥም ጊዜም ሲያጫውቷት የቆየችው ይህች አሮጊት ማን ናት?” እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡- “ኸዲጃ በሕይወት በነበረችበት ጊዜ በየጊዜው ወደቤታችን ትመጣ ነበር፡፡ ታማኝነት ከእምነት ክፍል ነው፡፡” (ሐኪም)

በሚያሳዝን ሁኔታ ዛሬ ዛሬ ይህ ታላቅ የሆነ ፀጋ፣ ይህ ታማኝነት ደብዛው እየጠፋ መጥቷል፡፡ ይህ ቃል ዛሬ ዛሬ በመዝገበ ቃላቶች ላይ ብቻ ሰፍሮ የሚታይ ሆኗል፡፡ ለዚህ የምናቀርበው ምክንያት ሌላ ሳይሆን አላህን መፍራት እየቀነሰና ሰውም ከእምነት ብዙ እየራቀ መሄዱን እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ ቀጣዩን ሐዲስ ተመልከት፡፡

“ቃል ኪዳኑን ለሚያፈርስ ለማንኛውም ሰው በፍርዱ ቀን ባንዲራ ይውለበለብለታል፡፡ ይህ ባንዲራ የወጣበት ሰው ቃል ኪዳኑን ያፈረሰ መሆኑም ይታወጃል፡፡” (ቡኻሪና ሙስሊም)

እንግዲህ ስለታማኝነት ስናወራ በመጀመሪያ ታማኝ መሆን ያለብን ለአላህ ሲሆን ቀጥለን ደግሞ ለመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) ነው፡፡ ይህ ነው የስኬት ምንጩና የዘላለማዊ ደስታ ማረጋገጫ ዋስትና፡፡

ለታላላቆቻችን ታማኝነትን ማሳየት፣ በሕይወት ለሚገኙም ይሁን ለሞቱ እንዲሁም ለሃገራችንም ሆነ ለማኅበረሰባችን ታማኞች ሆነን መገኘታችን የተቅዋችን (አላህን የመፍራታችን) መገለጫ ባሕሪያችን ሆኖ ሊታይ ይችላል፡፡

## ተቅዋ በፍቅር ሲገለጽ

በልባችን ውስጥ ፍቅር ሳይኖር ምንም የተሳካ ነገር ልንከውን አንችልም። ጥቃቅን የሚባሉ ጉዳዮችን እንኳን ለመፈፀም ፍቅር ሊያድርብን ግድ ነው፡፡ ይህ ዓለምና የተሰራበት የጥበብ ድርና ማግ ፈጣሪያችን አላህ ለሰው ዘሮችና ለሌሎች ፍጡራኑ ያለውን እዝነት፣ ፍቅርና ርህራሄ ያሳየበትና የገለፀበት ወደፊትም እንደዚያው የሚያደርግበት ሪሱን የቻለ ትእይንት ነው፡፡ ስለሆነም ሁሉን በሁሉ አድርጐ የከወነው ጌታ አንዱን ከአንዱ እያሳሳበ፣ እያስማማ፣ እያዋደደ፣ እያስተዛዘነና እያፋቀረም ያቋቁማል፡፡

“በብርሃን አለሁ እያለ ወንድሙን የሚጠላ ዋሾ ነውና እስከዛሬም በጨለማ ይኖራል፡፡ ወንድሙን የሚወድ ግን በብርሃን ይኖራል፡፡ ከእርሱ ዘንድ እንቅፋት የለም፡፡ ወንድሙን የሚጠላ ደግሞ አይኖቹን ጨለማ አሳውሮታልና በጨለማ ይመሰላል፡፡ ወዴት እንደሚሄድ አያውቅምና” እንዲል መጽሐፍ ፍቅር እንደሜዳ ሣር ተወልዶ መልሶ የሚያብብና የሚለመልም እንጂ ከልብ ተፍቆ የሚወድቅ መሆን የለበትም፡፡ ፍቅርና መዋደድ የጠፋ እለት ሁሉም ነገር ትርጉም ያጣልና፡፡

ከወደ ምስራቅ በኩል ብቅ ያለ አንድ መንፈሳዊ ሰው ሌሎች ሰዎችን መውደድና እነርሱንም አለማሳዘን ተገቢ መሆኑን ሲሰብክ እንዲህ ይላል፡ -

"ተአቀቡ! ተአቀቡ! የማንንም ልብ አታሳዝኑ ዘንድ፡፡"

"ተአቀቡ! ተአቀቡ! ለአንድም ፍጡር ተስፋ መቁረጥ ምክንያት አትሆኑ ዘንድ፡፡"

"ማንም ቢሆን የአንድ ሰው ልብ ሃዘን ወይም የአንዲት ነፍስ ተስፋ መቁረጥ ምክንያት ሆኖ በምድር ላይ ከሚራመድ ራሱን መቀመቅ ቢያስገባ ይሻለዋል፡፡"

እንግዲህ የሰው ልጅ የራሱ ብጤ ለሆነው ሰብአዊ ፍጡር፣ ለተፈጠሮ፣ ለእንስሳት፣ ለሌሎችም ፍጡራን እዝነትና ርኅራሄ ይኖረው ዘንድ በመጀመሪያ የእነዚህ ሁሉ አስገኚና አስተናባሪ የሆነውን የዓለማት ጌታ ከልቡ ማፍቀር ይኖርበታል፡፡ ልቡ በፈጣሪው ፍቅር ከተጥለቀለቀ ዘንዳ የተወዳጁን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) ፍቅርም ማግኘቱ አይቀርም፡፡ አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) ማፍቀርና ይህን ፍቅርም ከምንም በላይ አድርጎ ማየት የተቅዋ (አላህን የመፍራት) ቁንጮ ነው፡፡ ቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُلْ إِن كَانَ ءَابَآؤُكُمْ وَأَبْنَآؤُكُمْ وَإِخْوَٰنُكُمْ وَأَزْوَٰجُكُمْ وَعَشِيرَتُكُمْ وَأَمْوَٰلٌ ٱقْتَرَفْتُمُوهَا وَتِجَٰرَةٌ تَخْشَوْنَ كَسَادَهَا وَمَسَٰكِنُ تَرْضَوْنَهَآ أَحَبَّ إِلَيْكُم مِّنَ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَجِهَادٍ فِى سَبِيلِهِۦ فَتَرَبَّصُوا۟ حَتَّىٰ يَأْتِىَ ٱللَّهُ بِأَمْرِهِۦ ۗ وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْفَٰسِقِينَ ﴿٢٤﴾ ﴾ التوبة: ٢٤

*"አባቶቻችሁ ወንዶች ልጆቻችሁም ሚስቶቻችሁም ዘመዶቻችሁም የሰበሰባችኋቸው ኃብቶችም፣ መክሰሩዋን የምትፈሯት ንግድም፣*

*የምትወዷቸው መኖሪያዎችም ከእናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልእክተኛው፣ በእርሱ መንገድ ከመታገልም ይበልጥ የተወደዱ እንደሆኑ አላህ ትእዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ተጠባበቁ በላቸው፡፡ አላህም አመፀኞች ሕዝቦችን አይመራም፡፡" (አት-ተውባህ፡24)*

አነስ (ረ.ዐ.) እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"ከእናንተ አንዳችሁ ከልጁ ከወላጆቹና ከሰው ዘር በአጠቃላይ ከርሱ ዘንድ እኔ ይበልጥ ተወዳጅ እስካልሆንኩ ድረስ አላመነም፡፡" (ቡኻሪና ሙስሊም)

ቡኻሪና ሙስሊም አነስን (ረ.ዐ.) ጠቅሰው እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"ሦስት ባህሪያት ያሉት ሰው የኢማንን ለዛ አጣጥሟል፤ ከማንም ይበልጥ አላህና መልእክተኛው ከሱ ዘንድ ተወዳጅ መሆናቸው፣ አንድን ሰው ሲወደው ለአላህ ብሎ መሆኑና አላህ ከኩፍር ካዳነው በኋላ እንደገና ወደ ኩፍር መመለስን ከእሳት ውስጥ የመግባትን ያህል ሲጠላ፡፡"

በሌላ ዘገባ ደግሞ

"ከእናንተ አንዳችሁ አንድን ሰው ሲወድ ለአላህ ብቻ ብሎ እስካልሆነ ድረስ የኢማንን ለዛ አያጣጥምም፡፡" የሚል ተወስቷል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ተከታዩን መናገራቸውን ኢብን አባስ (ረ.ዐ.) አስተላልፈዋል፡-

"ለአላህ ሲል የወደደና ለአላህ ሲል የጠላ፣ ለአላህ ሲል የተወዳጀና ለአላህ ሲል ወዳጅነቱን ያቋረጠ የአላህን ወዳጅነት ያተርፋል፡፡ አንድ ባሪያ ባህሪው እንዲህ እስካልሆነ ድረስ ሶላቱና ፆሙ የቱን ያህል ቢበዛም የኢማንን ለዛ አያጣጥምም፡፡ አብዛኛዎቹን ሰዎች ከሌሎቹ ጋር

የሚያወዳጃቸው አለማዊ ጉዳይ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ወዳጅነት ደግሞ ቅንጣት አይፈይድም።" (ኢብን ጀሪር)

ከሁሉም በላይ አላህን የምንወድ ለመሆናችን እንደቃል ኪዳን ማሰሪያ ሊሆኑ የሚችሉት ሁለት የቁርአን አንቀፆች የሚከተሉት ናቸው:-

﴿ قُلْ إِن كُنتُمْ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِى يُحْبِبْكُمُ ٱللَّهُ ﴾ آل عمران: ٣١

*"በላቸው፡ አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ አላህ ይወዳችኋልና፡ ፡..." (አሊ-ዒምራን:31)*

﴿ قُلْ إِنَّ صَلَاتِى وَنُسُكِى وَمَحْيَاىَ وَمَمَاتِى لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٦٢﴾ ﴾ الأنعام: ١٦٢

*"ስግደቴ መገዛቴም ሕይወቴም ሞቴም ለዓለማት ጌታ አላህ ነው በል።" (አል-አንአም:162)*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህችን ዓለም በሞት ተሰናብተው በሄዱ ጊዜ ባልደረቦቻቸው በታላቅ ሃዘን ላይ ወድቀው ነበር። የተወሰኑት ወደ ቀይ ባሕር አቅጣጫ ዝም ብለው ጋለቡ። ኡመርን (ረ.ዐ.) የመሳሰሉት ደግሞ የአእምሯቸውን ሚዛን ተነጥቀው "ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ሞቷል የሚልን ሰው ጭንቅላቱን እንቆርጠዋለን!" ሲሉ ተደመጡ። ሌሎቹ ደግሞ የሚይዙ የሚጨብጡትን አጥተው ዋለሉ። ይህ ሁሉ የሆነው ሁሉም ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የነበራቸው ፍቅር ዳር ድንበር ስላልነበረው ነው። አብደላህ ኢብን ዘይድም (ረ.ዐ.)ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ጥልቅ ፍቅር ከነበራቸው ተከታዮቻቸው መካከል አንዱ ነበርና እንዲህ ሲል ልመናውን ለአላህ አቀረበ:-

"አላህ ሆይ! በዚህች ዓለም ላይ ከእንግዲህ ተወዳጁን ነቢይ የማላይ ከሆነ ዓይኔን አልፈልገውምና ውሰደው።" ዱዓውን ያደረገው ጥርት ባለው

ልቡ ስለነበር የዓይን ብርሃኑን ወዲያውኑ ነበር ያጣው፡፡ ሰውባን (ረ.ዐ.) ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩ እየወየበና ወዘና እየራቀው እየከሳም ሲሄድ ይታይ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉት፡- "ሰውባን ሆይ! ምን ሆነህ ነው እንዲህ የምትገረጣው? ህመም አድሮብሃልን?" ሰውባንም (ረ.ዐ.) እንዲህ ሲል መለሰ "የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በእኔ ላይ አንዳች ሕመም የለብኝም፡፡ ሆኖም ግን ሁልጊዜ አንድ ነገር ያሳስበኛል፡፡ ሥራዬ አምሮ ጀነት ከገባሁ ምናልባት አይዎት ይሆናል፡፡ ያ ሳይሆን ቀርቶ ጀነት የማልገባ ከሆነ ግን እስከምንግዜውም የማንገናኝ መሆኑን ሳስብ በጣም ይጨንቀኛል፡፡ ይህ ነው ትልቁ ችግሬ፡፡" ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በዚህ አባባል ልባቸው ተነካ፡፡ ከዚያም እንዲህ አሉት፡- "ሰውባን ሆይ! ሰው ከሚወደው ጋር ነውና የሚሆነው (አብሽር) እንገናኛለን፡፡"

# ምዕራፍ ስምንት

# <u>የተቅዋ ልዩ ልዩ ገጽታዎች</u>

## ተቅዋ በኢኽላስ (ፍጹምነት) ላይ ያለው ድርሻ

ኢኽላክስ (ፍጹምነት) መልካም ሥራዎች ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ቅድመ ሁኔታ ነው። ኢኽላስ ማለት ከማንኛውም ዓለማዊ ጥቅማጥቅም ነጻ ሆኖ መልካም ሥራን መሥራትና በዚያም የአላህን ውዴታ መሻት ማለት ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُواْ ٱلزَّكَوٰةَۚ ﴾

*"አላህን ኃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ሆነው ሊግገዙት፣ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ፣ ዘካንም ሊሰጡ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ…" (አል-በይናህ፡5)*

አንድ ሰው ተቅዋ ካለውና ይህንን ተቅዋውንም በኢኽላስ (ሥራን ፍጹም ለአላህ በማጥራት) የሚጠብቅ ከሆነ በእውነቱ ከዚህ የተሻለ ስኬት የለም።

## ተቅዋ አደራን በመጠበቅ ላይ ስለሚጫወተው ሚናስ ምን እንበል?

ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّا عَرَضۡنَا ٱلۡأَمَانَةَ عَلَى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱلۡجِبَالِ فَأَبَيۡنَ أَن يَحۡمِلۡنَهَا وَأَشۡفَقۡنَ مِنۡهَا
وَحَمَلَهَا ٱلۡإِنسَٰنُۖ إِنَّهُۥ كَانَ ظَلُومٗا جَهُولٗا ٧٢ ﴾ الأحزاب: ٧٢

*“እኛ አደራን በሰማያትና በምድር፣ በተራራዎችም ላይ አቀረብናት፡፡ መሸከሟንም እንቢ አሉ፡፡ ከእርሷም ፈሩ፡፡ ሰውም ተሸከማት፡፡ እርሱ በጣም በደለኛ ተሳሳች ነውና፡፡” (አል-አሕዛብ:72)*

አደራ ስንል እንግዲህ ከሁሉም በፊት የአላህን ኃይማኖት (ኢስላምን) ማለታችን እንደሆነ መታወቅ አለበት፡፡ የኢስላምን ህግጋት ጠብቆ ከመሞትና አላህ ጋር ከመገናኘት የበለጠ ታላቅ የሆነ አደራ የለም፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ حَقَّ تُقَاتِهِۦ وَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسْلِمُونَ ١٠٢﴾

*“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት እናንተም ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጂ እንዳትሞቱ፡፡” (አሊ-ዒምራን: 102)*

﴿وَٱلَّذِينَ هُمْ لِأَمَٰنَٰتِهِمْ وَعَهْدِهِمْ رَٰعُونَ ٨﴾ المؤمنون: ٨

“እነዚያም እነርሱ ለአደራዎቻቸውና ለቃል ኪዳናቸው ጠባቂዎቹ፡፡” (አል-ሙእሚኑን፡ 8)

## ተቅዋ በኃላፊነት ላይ ያለው ሚና

ኃላፊነት ማለት በማንኛውም ሁኔታ እኛ የበላይ ሆነን እንድንመራው፣ እንድናስተዳድረውና እንድንጠብቀው የተሰጠንን አንዳች ነገር በተገቢው ሁኔታ መጠበቅ ነው፡፡ አንድ ሰው ተቅዋ (የአላህ ፍራቻ) ከሌለው እውነተኛና ለኃላፊነትም ብቁ ሊሆን አይችልም፡፡

ከሁሉም በላይ እያንዳንዱ ሰው በነፍስ ወከፍ ያለበት ኃላፊነት ራሱንና ቤተሰቡን ከክህደት ጠብቆ ቀናውን መንገድ እንዲይዙ ማድረግ ነው። በቁርአን እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ قُوٓاْ أَنفُسَكُمۡ وَأَهۡلِيكُمۡ نَارٗا وَقُودُهَا ٱلنَّاسُ وَٱلۡحِجَارَةُ ﴾ التحريم: ٦

*“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ድንጋዮች ከሆነች እሳት ጠብቁ።” (አት-ተሕሪም:6)*

የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.)

“እያንዳንዳችሁ እረኞች ናችሁ። ከምትጠብቁት ነገር ትጠየቃላችሁ።” ብለዋል።

## ተቅዋ ያለውን ሰው አላህ መውጫ ያደርግለታል

አቡ ዘር እንደተናገሩት አንድ እለት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“ሰዎች ቢያውቁትና ተግባራዊ ቢያደርጉት መድህን የሚያገኙበትን አንቀጽ አውቃለሁ።”

“ይህ አንቀጽ የትኛው ነው? የአላህ መልእክተኛ ሆይ!” ተብለው ሲጠየቁ የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ አነበቡ፡-

﴿ وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّهُۥ مَخۡرَجٗا ٢ ﴾ الطلاق: ٢

*“...አላህንም የሚፈራ ሰው ለእርሱ መውጫን ያደርግለታል።” (አጥ-ጦላቅ:2)*

## የሰው መመዘኛው ተቅዋ ነው

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقۡنَٰكُم مِّن ذَكَرٖ وَأُنثَىٰ وَجَعَلۡنَٰكُمۡ شُعُوبٗا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓاْۚ إِنَّ أَكۡرَمَكُمۡ عِندَ ٱللَّهِ أَتۡقَىٰكُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٞ ١٣ ﴾ الحجرات: ١٣

*"እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤ እንድትተዋወቁም ጉሣዎችና ነገዶች አደረግናችሁ:: አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው::" (አል-ሑጁራት:13)*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አቡ ዘርን እንዲህ ብለውታል "ነጭ ሰው በጥቁር ሰው ላይ የበላይነት የለውም አላህን በመፍራት ቢሆን እንጂ::" (አህመድ)

## የተቅዋ መገለጫው ምንድን ነው?

ነቢዩ ኢሣ (ዐ.ሰ.) ተቅዋን (አላህን መፍራትን) አስመልክተው ባማረ ሁኔታ እንደሚከተለው ማለታቸው ተጠቅሷል፡- "አንድ ሰው ወደ እርሳቸው መጣና እንዲህ አላቸው፡- "የደግነት መምህር ሆይ! አምላክን እንዴት ልፈራው እችላለሁ?" እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡- "ይህ ቀላል ነው:: አምላክህን ከልብህ ውደድ:: ለሰዎችም አቅምህ የቻለውን ያክል መልካም አድርግ:: ለአዳም ዘር ሁሉ ሃዘኔታና ርህራሄን አሳይ::" ከዚያም ቀጠል አድርገው እንዲህ አሉ፡- "ሰዎች ባንተ ላይ እንዲያደርጉብህ የማትፈልገውን ነገር አንተም በእነርሱ ላይ አታድርግ:: ያን ጊዜ በአምላክ ፊት ፈሪሃ ያለህ ትሆናለህ::" (አህመድ)

## የተቅዋን ፈተና ማለፍ

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በሕይወት በነበሩ ጊዜ ሰዎች ከእርሳቸው አጠገብ ሲሆኑ ድምፃቸውን ዝቅ ማድረጋቸው ለአላህ የነበራቸውን ፍራቻ (ተቅዋ) እንደሚያሳይ የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ ይገልፃል፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَغُضُّونَ أَصۡوَٰتَهُمۡ عِندَ رَسُولِ ٱللَّهِ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ ٱمۡتَحَنَ ٱللَّهُ قُلُوبَهُمۡ لِلتَّقۡوَىٰۚ لَهُم مَّغۡفِرَةٞ وَأَجۡرٌ عَظِيمٌ ٣ ﴾ الحجرات: ٣

*"እነዚያ በአላህ መልእክተኛ ዘንድ ድምፆቻቸውን ዝቅ የሚያደርጉ እነዚህ እነዚያ አላህ ልቦቻቸውን ለፍርሃት የፈተናቸው ናቸው። ለእነርሱም ምሕረትና ታላቅ ምንዳ አልላቸው።" (አል-ሑጁራት፡ 3)*

የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ማክበርና ለእርሳቸው ትሁት መሆን ለአላህ ፍርሃት (ተቅዋ) የቀረበ ድርጊት ነበር ማለት ነው።

## ተቅዋን ልበሱት

﴿ يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ قَدۡ أَنزَلۡنَا عَلَيۡكُمۡ لِبَاسٗا يُوَٰرِي سَوۡءَٰتِكُمۡ وَرِيشٗاۖ وَلِبَاسُ ٱلتَّقۡوَىٰ ذَٰلِكَ خَيۡرٞۚ ﴾

*"የአደም ልጆች ሆይ! ሃፍረተ ገላችሁን የሚሸሽግን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በእናንተ ላይ አወረድን። አላህን የመፍራትም ልብስ ይህ የተሻለ ነው።..." (አል-አዕራፍ፡26)*

አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ - ኢማም አቡ ሐኒፋ ከልብሳቸው ላይ አነስተኛ የሆነችን ጉድፍ ለማስለቀቅ ሲጣጣሩ ታዩ። ከተከታዮቻቸው የተወሰኑት ይህን ድርጊት አስፈላጊ አድርገው አልቆጠሩትም። ስለሆነም እንዲህ አሏቸው፡-

"ኢማም ሆይ! በእርስዎ መዝሃብ እንደተማርነው ይህች አነስተኛ ጉድፍ ሶላት ከመስገድ አታግድዎትም። ታዲያ ይህን ያክል መድከምዎ ለምንድን ነው?" ኢማሙ እንዲህ በማለት መልስ ሰጧቸው፡-

"ያ ኢስላማዊ ሕግ ሲሆን ይህ ግን ተቅዋ ነው።"

ይህ የኢማሙና የመሰሎቻቸው አቋም ከሚከተለው የቁርአን አንቀጽ ድጋፍ ያገኛል፡-

﴿ فَٱسۡتَقِمۡ كَمَآ أُمِرۡتَ وَمَن تَابَ مَعَكَ ﴾ هود: ١١٢

*"እንደታዘዝከውም ቀጥ በል፡፡ ከአንተ ጋር ያመኑትም (ቀጥ ይበሉ)..." (ሁድ፡112)*

## ከስንቅም ሁሉ በላጩ ተቅዋ ነው

አንድ ሰው ለአላህ ያለው ፍቅርና እውቀት በጨመረ ቁጥር ለእርሱ ያለው ፍርሃት (ተቅዋ) የዚያኑ ያክል ይጨምራል፡፡ ሁላችንም ብንሆን እዚህ ደረጃ እንድንደርስ ነው የሚፈለገው፡፡ አላህ በቁርአኑ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

﴿ لَن يَنَالَ ٱللَّهَ لُحُومُهَا وَلَا دِمَآؤُهَا وَلَٰكِن يَنَالُهُ ٱلتَّقۡوَىٰ مِنكُمۡۚ ﴾ الحج: ٣٧

*"አላህን ሥጋዎቿም ደሞቿም ፈጽሞ አይደርሰውም፡፡ ግና ከእናንተ የሆነው ፍራቻ ይደርሰዋል፡፡.." (አል-ሐጅ፡37)*

ጀላሉዲን ሩሚ እንዲህ ይላሉ፡-

"ወዳጄ ሆይ! ፍየሏን ራሷን እንጂ ጥላዋን ለማረድ አትድከም!"

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَمَّنۡ هُوَ قَٰنِتٌ ءَانَآءَ ٱلَّيۡلِ سَاجِدٗا وَقَآئِمٗا يَحۡذَرُ ٱلۡأٓخِرَةَ وَيَرۡجُواْ رَحۡمَةَ رَبِّهِۦۗ قُلۡ هَلۡ يَسۡتَوِي ٱلَّذِينَ يَعۡلَمُونَ وَٱلَّذِينَ لَا يَعۡلَمُونَۗ إِنَّمَا يَتَذَكَّرُ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ٩ ﴾ الزمر: ٩

*"እርሱ የመጨረሻይቱን ዓለም (ቅጣት) የሚፈራ የጌታውንም ችሮታ የሚከጅል ሲሆን በሌሊት ሰዓቶች ሰጋጅና ቋሚ ሆኖ ለጌታው የሚግገዛ ሰው (እንደ ተስፋ ቢሱ ከሃዲ ነውን? እነዚያ የሚያውቁና እነዚያ*

*የማያውቁ ይስተካከላሉን? በላቸው። የሚገነዘቡት ባለ አእምሮዎቹ ብቻ ናቸው።" (አዝ-ዙመር:9)*

**እውቀትን መፈለጋችን እንዳለ ሆኖ ከሥራ ጋር ልናቆራኘው ግድ ነው። ካልሆነ ሥራ የጐደለው እውቀት ከሚከተለው ሐዲስ ከተጠቀሰው ማስጠንቀቂያ ጋር መመሳሰሉ አይቀሬ ነውና ወዮልን!**

**"እነዚያ እውቀታቸውን እንጂ ተቅዋቸውን (ለአላህ ያላቸውን ፍራቻ) ያልጨመሩ ከአላህ ራሳቸውን ያርቃሉ።"**

**ለዚህም ነው አላህ የመጪውን ዓለም ማለቂያ የሌለው የመከራ ቁልል እናመልጥ ዘንድ ተቅዋን እንድንሰንቅ በቀጣዩ የቁርአን አንቀጽ የሚመክረን:-**

﴿ وَتَزَوَّدُوا۟ فَإِنَّ خَيْرَ ٱلزَّادِ ٱلتَّقْوَىٰ ۚ وَٱتَّقُونِ يَـٰٓأُو۟لِى ٱلْأَلْبَـٰبِ ﴿١٩٧﴾ ﴾ البقرة: ١٩٧

*"...ተሰነቁም ከስንቅም ሁሉ በላጬ ጥንቃቄ (ተቅዋ) ነው። የአእምሮዎች ባለቤቶች ሆይ! ፍሩኝ።" (አል-በቀራህ:197)*

## ተፈጸመ